አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ (አማርኛን  በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤት በአስረኛ  ክፍል (ተተኳሪነት)

በ

ሙሉነሽ ሀዶሮ

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መስከረም 21/2016 ዓ/ም

# በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ (አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል (ተተኳሪነት)

በ

ሙሉነሽ ሀዶሮ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት

ክፍል የሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮሚዩንኬሽን ኮሌጅ

የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

የጥናቱ አማካሪ

ዶክተር አማኑኤል አለማየሁ

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መስከረም 21/2016 ዓ/ም

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

"በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ(አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት"በሚል ርዕስ በተግባራዊ ስነ-ልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በሙሉነሽ ሀዶሮ ኃይለማሪያም የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራት እና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ……………………………………..…..ፊርማ………………ቀን………………………

ፈታኝ ……………………………...............ፊርማ………………ቀን…………………………

ፈታኝ…………………………………………..ፊርማ………………ቀን…………………………

## ማረጋገጫ

"በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ (አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት"በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር በተግባራዊ ስነ-ልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም:- ሙሉነሽ ሀዶሮ ኃይለማሪያም

ፊርማ..............................

ቀን............................

# ምስጋና


ከሁሉ አስቀድሜ ይህንን ጥናት ጀምሬ እስክጨርስ ድረስ እውቀት ለሰጠኝ እና ለረዳኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰው፡፡

ይህን የጥናቱ ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ፣ረቂቁንና የመጨረሻውን ጽሁፍ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሚሁራዊ አስተያት በመስጠት ጥናቱ በዚህ መልኩ ተጠናቆ እስኪ ቀርብ ድረስ አቅጣጫ በማመልከት፣ ረቂቁን ያለመሰልቸት በማንበብ፣በማረም፣አስፈላጊውን እርማትና ማስተካከያ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተር አማኑኤል አለማየሁ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርበለሁ፡፡ለመልካም ምክራቸውና ትህትናቸው የተለየ አክብሮት አለኝ፡፡

በቅድመ ሙከራ ጥናቱና በዋናው ጥናት የትግበራ ሂደት ዘወትር ከአጠገቤ በመሆን በጥናታዊ ሥራው የትግበራ ሂደት ላይ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉልኝ የጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን፤ለመምህር አበራ ገብሬ፣ለመምህርት ሜሮን ወ/ገብረኤል እና ለመምህርት ሰርካለም ሳታናው በተለይም በጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ ማሳሰቢያዎችን በመስጠት፣በትብብር በማስተማር፣በመፈተን፣ክፍሎችን በማመቻቸት፣በማረም የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት እስከ መጨረሻው ከጐኔ ላልተለዩኝ ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡በቁሳቁስ፣ተማሪዎችን በማስተባበር፣መማርያ ክፍሎችን ለጥናቱ በምመች ሁኔታ በማስተካከል ሁለንተናዊ ድጋፍ ለደረጉልኝ ለጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት ለሁሉ እና በተላይ ለርዕሰ መምህር አቶ አፈወርቅ አማኑኤል እና ለአስተዳደር ምክትል ርዕሰ መምህርት ወ/ሮ ደስታ ጭርቆ ልባዊ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

በመጨረሻም ለባለቤቴ መምህር ይስሐቅ ጎአ ሙያዊና ሞራላዊ ድጋፌ በማድረግ ለዚህ ላበቃኝ እና ሁለንተናዊ ድጋፌ ለደረገኝ ለወንድም ገዛሀኝ ሀዶሮ፣ አይዞሽ በማለት ከጐኑ ላልተለያችሁኝ ለቤተሰቦቼ በሙሉ ላደረጋችሁልኝ ማነቃቃትና ትብብር ከፍተኛ ምስጋና አቅርቤያለሁ፡፡

## ማውጫ

ማረጋገጫ ........ iii

ምስጋና ........ iv

አጠቃሎ ........ x

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 5

የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 6

1.5. የጥናቱ መላምት ........ 6

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7

1.7 የጥናቱ ወሰን ........ 7

1.8 የጥናቱ ውስንነት ........ 8

1.9. የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ ........ 8

ምዕራፍ ሁለት ........ 9

2.1.መግቢያ ........ 9

2.2. ከመጻፍ ትምህርት ጋር የተያያዙ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች ........ 9

2.2.1. የባህሪያው ንድፈ ሀሳብ ........ 9

2.2.2. የአእምሮታዊያን ንድፈ ሀሳብ ........ 10

2.2.3. የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ........ 10

2.3. የጽህፈት ክሂል ምንነት ........ 11

2.4. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ ........ 12

2.5. የጽህፈት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆች ........ 13

2.5.1 ውጤት ላይ ያተኮረ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ ........ 14

2.5.2 ሂደታዊ አቀራረብ ........ 17

2.5.3. ውጤት ውሂደት አቀራረብ ........ 19

2.6. መጻፍ ለምን አዳጋች ይሆናል? ........ 20

2.6.1. ሥነ-ልቦናዊ ችግር ........ 20

2.6.2. ሠዋሰዋዊ ችግር ........ 20

2.6.3. የግንዛቤ ችግር ........ 20
2.7. የትብብር መማር ምንነት ........ 21
2.8. የትብብር መማር ጠቀሜታ ........ 23
2.8.1. የአካዳሚካል ጥቅም ........ 23
2.8.2. ፈጠራ እንዲጨምር ያደርጋል ........ 23
2.8.3. ስነ አእምሮአዊ ጥቅም ........ 24
2.8.4. ማህበራዊ ጠቀሜታ ........ 24
2.8.5. መምህራን የሚያገኙት ጥቅም ........ 24
2.9. በትብብር መማር መሰረታዊ መርሆች ........ 24
2.9.1. አዎንታዊ ግንኙነት ........ 25
2.9.2. የቡድን አባል ተጠያቂነት ........ 25
2.9.3. ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ ........ 26
2.9.4. ማህበራዊ ክህሎታቸውን በአግባቡ መጠቀም መቻል ........ 26
2.9.5 ቡድናዊ ሂደት ........ 27
**2.10. በትብብር መማር ሂደት የመምህራን ሚና** ........ 28
**2.11. በትብብር መማር ማስተማር ወቅት የተማሪዎች ሚና** ........ 29
**2.12. ቀደምት ሥራዎች ቅኝት** ........ 30
ምዕራፍ ሶስት ........ 32
**3.የጥናቱ ዘዴ** ........ 32
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 32
3.2 የመረጃ ምንጮች ........ 32
3.3 የናሙና አመራረጥ ........ 32
3.3.1. ትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 32
3.3.2 .የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 33
3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ ........ 33
3.3.4. የመምህራን አመራረጥ ........ 34
**3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች** ........ 34
3.4.1. ፈተና ........ 34
**3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ** ........ 35
**3.6 የሙከራ ጥናቱ አተገባበር ሂደት** ........ 36
3.6.1 የተሰጠው ስልጠና ........ 36
3.6.2 የቡድን አደረጃጀት ........ 36

3.6.3. ሚና መከፋፈልና የስራ ድርሻን መግለፅ ....... 37
3.6.4 የክፍል ውስጥ አተገባበር ....... 37
3.6.5 የግልና የቡድን ፅብረቃ ....... 38
**3.7 የቅድመ እና ድህረ ፈተና አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት** ....... 39
**3.8 የጽሁፍ መጠይቅ አተናተን ዘዴ** ....... 39
ምዕራፍ አራት ....... 40
**4.የውጤት ትንተናና ማብራሪያ** ....... 40
4.1.የውጤት ትንተና ....... 40
4.1.1. የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና ትንተና ....... 40
4.1.2. የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና ትንተና ....... 42
4.1.3 የጽሁፍ መጠየቅ ውጤት ትንተና ....... 45
**4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ** ....... 49
ምዕራፍ አምስት ....... 52
**5. የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያና አስተያየት** ....... 52
5.1.ማጠቃለያ ....... 52
5.2..መደምደሚያ ....... 54
5.3.የመፊትሔ ሀሳብ ....... 55
ዋቢዎች ....... 56
አባሪዎች ....... 61
**አባሪ 1** ....... 61
**አባሪ 2** ....... 64
መመሪያ አንድ ....... 64
መመሪያ ሦስት ....... 65
መመሪያ አምስት ....... 66
**አባሪ 3** ....... 67
**አባሪ 4** ....... 70
**አባሪ 5** ....... 73
**አባሪ 6** ....... 76
**አባሪ 8** ....... 82
**አባሪ 9** ....... 88
**አባሪ 10** ....... 98
**አባሪ 11** ....... 100

**አባሪ 12** ........ 111
**አባሪ 13** ........ 114
*መመሪያ አንድ* ........ 114
*መመሪያ ሁለት፡* ........ 114
*መመሪያ ሦስት* ........ 115
*መመሪያ አምስት* ........ 116

## ማውጫ

ገጽ

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ 4.1 ፡-ከነፃ ናሙና አንፃር በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ያለ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት፣........................................47

ሠንጠረዥ 4.2፡-ከነፃ ናሙና አንፃር በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ያለ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት፣...........................................48

ሠንጠረዥ 4.3፡- ከጥንድ ናሙና አንጻር የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎ መካከል ያሳየው አማካይ ውጤት ልዩነት፣......................................49

ሠንጠረዥ 4.4፡- ከጥንድ ናሙና አንጻር የሙከራ ቡድኑ በቅደምና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያሳየው አማካይ ውጤት ልዩነት ..........................................................50

ሠንጠረዥ 4.5፡- በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተማሪዎች የመምህራን አስተያየት ንጽጽራዊ ትንተና...........................................................................52

# አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳርነት በመፈተሽ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው።ዓላማውንም ለማሳካት ጥናቱ የተከተለው ሙከራዊ ምርምር ሲሆን ከመተንተኛ ዘዴዎች አንጻር ደግሞ መጠናዊ ምርምርን ተከትሏል።የጥናቱ ተሳታፊዎችም በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 416 ሲሆኑ ከእነዚህም ለጥናቱ ናሙናነት በYemane(1977) ፎርሙላ ተጠቅሜ የመረጥኳቸው ተማሪዎች ብዛት 203 ናቸው:: ከነኚህም መካከል 156 ተማሪዎች ወላይተኛ አፍ-ፈት ሲሆኑ የቀሩት 47 ተማሪዎች አማርኛ አፍ-ፈት ናቸው።አማርኛ አፍ-ፈት የሆኑት የ47ቱ ተማሪዎች የፈተና ውጤት ከጥናቱ ውጪ ተደርጓል።በዚህ መሰረት 156 ተማሪዎችን በጥናቱ ለማሳተፍ አስቤ ነበር።ሆኖም ከ156 ወላይተኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች መካከል 8 ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተናውን ባለመፈተናቸው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው ከጥናት ውጪ ተደርጓል።የተመረጡ ተማሪዎች በሁለት ቡድን ተመድበው በቁጥጥር ቡድኑ 74 እንደዚሁም በሙከራ ቡድኑ 74 በአጠቃላይ የ148 ተማሪዎች የፈተና ውጤት የጥናቱ ናሙና በመምረጥ ሙከራዊ ጥናቱ ተካሄዷል።ቀጥሎም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በትብብራዊ መማር ዘዴን ለመተግበር የተዘጋጀላቸውን የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለተከታታይ አምስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ክፍሌ ጊዜ ከተማሩ በኋላ ድህረ ፈተና ተሰጥቷል።ውጤቱም በድምዳሜያዊ ገላጭ ስታቲስቲክ በቲ-ቴስት(ቲ= -3.78) የp ዋጋ(0.001) ሆኗል። በአጠቃላይ በሁለቱ ፈተናዎች ያለው የውጤት ልዩነት በጉልህነት ደረጃ ሲታይ፣ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አሳይቷል።የፈተና ውጤት የሚያሳየው በትብብራዊ መማር የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ሚና እንዳለው በዚህ ጥናት ተረጋግጧል። የትንተናው ውጤት እንዳሚያመለክተውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ ውጤት አስመዝግበዋል።ገላጭ መረጃው እንደሚያመለክተው የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 52.81 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 59.23 ነው።በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት 6.42 ሆኗል።ይህም ውጤት ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።በመሆኑም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ትብብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ እንደሁነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

በትብብር መማር ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች አብረው ሰርተው የጋራ የሆነ አጥጋቢ ምላሽ የሚያገኙበት ነው፡፡በትብብር መማርን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ለአብነት ያክል የተወሰኑትን መመልከት ይቻላል፡፡ Johnson & Johnson (1999) በትብብር መማር የሚባለው የአነስተኛ ቡድን ተማሪዎች አንድ ላይ በመስራት የራሳቸውንና የሌሎችን መማር ሁኔታ የሚያሻሽሉበት (የሚያሳድጉበት) እንደሆነ ሲገልፅ Ricrages jack and Rodgers,Theodor, (2003) በበኩላቸው ከሁለት እስከ አራት አባላት ያለው ቡድን የተሻለ ስራ ይሰራ ዘንድ መምህሩ የተለያዩ በትብብራዊ መማሪያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡Slavin(1987) ሲገልፁ በትብብር መማር የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትንሽ ቡድን በማቀናጀት እርስ በርስ በመበረታታት አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ሲገልፁ ተመሳሳይ Kagan&Kagan (2009) በትብብር መማር ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ እንደ ሆነ በመግለፅ የተለያዩ የትምህርት ዓይነት ያላቸው ግንዛቤ ለማሻሻል ልዩ ልዩ የመማር ተግባራትን የሚያከናውንበት ነው ብለዋል፡፡

ይህንን ሲያብራሩ እያንዳንዱ የቡድን አባል ያወቁትን ነገር እርስ በርስ በመከፋፈል በመረዳዳት ቡድናቸውን ስኬታማ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥረው የጋራ አረዳድ እስኪኖራቸው ድረስ በአንድነት አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ሌላው ስለ ትብብር መማር ብያኔ የሰጡት Johnson and Johnson (2009) ሲሆን ራሳቸውን እንደ አንድ የቡድን አባል አድርገው የሚቆጥሩ ተማሪዎች አብረው በመሆን ለጋራ ውጤት መሳካት በትብብር እና በመረዳዳት የሚሰሩበት ነው፤ሲሉ ተመሳሳይ Johnson and Johnson and smith(1988) አነስተኛ ቡድን ተማሪዎች የጋራ አላማቸውን (ግባቸውን) ሊያሳኩ የሚችሉት ሁሉም የቡድን አባላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሲወጡ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡ Rita Rani (2009) በበኩላቸው በትብብር መማር ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች አብረው ሰርተው የጋራ የሆነ አጥጋቢ ምላሽ የሚያገኙበት ነው፡፡ጥሩ የሆነ ስራ ከሰሩ በጋራ የሚሸለሙበት ከተጠበቀው በታች ከሰሩ ደግሞ የሚቆጩበት ነው

Lita rani(2009) ስለ ትብብር መማር ጠቀሜታ ሲገልፁ የተማሪዎች በጥልቀት ማሰብን ያጎለብታል፣አካባቢን በደንብ ለመረዳት ያስችላል፣የደካማ ተማሪዎችንም አቅም ከፍ ያደርጋል፣ እንደ አንድ የመማሪያ ዘዴ አማራጭ በመሆን ያገለግላል ይላሉ፡፡Richard & Renday (2002) የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ በትብብር መማር ያለውን ፋይዳ ሲያስቀምጡ ተማሪዎች የተለያዩ

ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ዘና ብለው መወያየት እንዲችሉ ማድረግ፣ችግሮችን ተወያይተው እንዲፈቱ ማስቻል፣ጥልቅ የሆነ የመስራት ፍላጎት እንዲኖራቸው እና በአጭር ጊዜ እየተነጋገሩ ብዙ ጥያቄዎችን መስራት ይችላሉ ብለዋል፡፡አለማየሁ (2009) በበኩላቸው Veenman(2000) Kagan(2007) እና Jollife (2007) በመጥቀስ እንደገለፁት በትብብር መማር የተማሪዎችን የተሻለ የመማር ማህበራዊ ክህሎትን፣ ስነልቦናዊ እድገትን አዕምሮአዊ ክህሎትን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡በአጠቃላይ ምሁራን ስለ ትብብር መማር ጠቀሜታ የገለፁትን ሀሳብ የሚያጠንክር ሌሎች በዝርዝር በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

ትብብራዊ መማር ምንነትን በተመለለከተ በርካታ ምሁራን ጻሀፍዎች በተለያየ ወቅት ብያኔያቸውን ብሰጡም የተሰነዘሩትም ብያኔዎች ተቀራራብና ወደ አንድ አቅጣጫ የሚመሩ ናቸው፡፡ (Richards and Rodgers(2001) Olson and Kagan(1992)ን በመጥቀስ እንደገለጹት በትብብር መማር ቡድናዊ የተግባር አፈጻጸም ነው ብለው ይገልጻሉ፡፡ዋነው መለያው ተማሪዎች በተመደቡበት ቡዱን ውስጥ ሆነው መረጃን በመለዋወጣቸውና መደጋገፋቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ሁሉም አባላት በተሰጣቸው ተግባራት ተጠያቂ በመሆን ከሌሎች አባላት ጋር ለመማር የሚያነሳሳ አቀራረብ ነው፡፡

የመጻፍ ችሎታ በባህሪው ተደጋጋሚ ልምምድን የሚፈልግ ሲሆን ውጤታማ መሆን የሚቻለው ግን በትብብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡መጻፍን በትብብራዊ ዘዴ በማስተማር ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ደግሞ Nunan (1992፡153) ይገልጻሉ፡፡ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታን በትብብር መማራቸው በአጠቃላይ ትምህርቱን ውጤታማ በማድረግ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የውይይት፣የስምምነትና የመረዳዳት ችሎታቸውን ማሳደግ የመጻፍ ትምህርትን የማሳደግ ድርሻ አለው፡፡

አብዛኞቹ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች እንዳስቀመጡት የተማሪዎች መማር ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የሚችለው በትብብር መማር መሰረታዊ መርህ የሆነውን አዎንታዊ አመለካከትን መደጋገፍ ነው፡፡ "ሁሉም ለአንድ፣አንድ ለሁሉም" የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ (ስሜት)ተማሪዎች ሲያዳብሩ ነውAkhtar et al (2012) በመማር ማስተማር ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በትብብር እንዲሰሩ ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነ ተማሪዎች በትምህርትና በማህበራዊ እሴታቸው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡በትብብር በሚማሩ ቡድኖች የሚወያዩትና በመከራከር በትምህርት ክፍለ ጊዜው የሚጠቀሙበትን መሳሪያዎች ፅንሰ ሀሳቦችን መረዳታቸውን መግለፅ ይችላሉ፡፡በተጨማሪም እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ እውነቶችን ለማስጨበጥ ይችላሉ፡፡

Slavin & Cooper (1999) ሀሳባቸውን እንደአስቀመጡት በትብብር መማር አላማው ተማሪዎች በትምህርታቸው ያላቸውን ስኬታማነት ከፍ እንዲል ማድረግ ነው፡፡ይህም የሚሆነው እርስ በርሳቸው ለመወያየት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመፍጠር እንዲማሩበት ማድረግና በማነጋገር የላቀ ውጤት ለማምጣት ለማበረታታት ነው፡፡

Johnson & Johnson (2009) እንደጠቀሱት በትብብር መማር የፈጠራ ሀሳብን ያጎለብታል፡፡ ተማሪዎች በነፃነት በደስታ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማድረግ፣አዳዲስ ፈጠረ በማምጣት በራሳቸው መፍትሄ እንዲሰጡ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቡድን ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ወቅት ከውድድር መንፈስ በመላቀቅ የራሳቸውን ሆነ የሌሎችን የቡድን ሀሳብ በማድነቅ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡

በትብብር መማር በተማሪዎች ዘንድ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሀሳባቸውን የመለዋወጥና በዚህ ላይም የተማሪውን በራስ የመተማመን የማክበር ስሜቱን ይገነባዋል፡፡በትምህርትም ክፍለ ጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች ስለሚሰጡት መልስ ለማሰብ ጊዜ ሳይሰጣቸው በብዙ ተማሪዎች ጥያቄ እንዲመልሱ ስማቸው ይጠራል፡፡በትብብር መማሩ ደህንነቱን የጠበቀ ስለሆነ የተጠየቁትን ጥያቄ በሁሉም ተማሪዎች ፊት መልስ ለመስጠት ይበረታታሉ፡፡

የቡድን አባላት ተጠያቂነት ማለት እያንዳንዱ የቡድን አባል ሌላው በሚሰራው ሥራ ላይ ሳይተማመን የየራሳቸውን ድርሻ በማከናወን፣ሌሎች የቡድን አባላት ድርሻቸውን እዲወጡ በማድረግ ሀላፊነታቸውን መወጣት የሚያመለክት ነው Jolifk(2007)፡፡ ይህን አስመልክቶ አለማየሁ(2009)እንደ ተናገሩት እያንዳንዱ የቡድን አባላት አባልነታቸው ያለውን ሀላፊነት አምነው የራሳቸውን የስራ ድርሻ በመወጣት ሌሎች አባላት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ አለባቸው፤ለቡድኑ ውጤታማ መሆን ወይም መውደቅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተጠያቂ ናቸው፤ ሲገመገሙ የአጠቃላይ የቡድኑን ውጤት ለመስጠት በግል ይገመግማሉ፤የቡድኑ አባላት ትምህርታቸውን በተሳትፎ መሰረታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ አለበት፤በቡድኑ ትክክለኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ተማሪዎች የስራ ሚና በጥቂቶች ላይ ተምኖ ሌሎች ነፃ የሚሆኑበት አጋጣሚ በማስቀረት ለቡድኑ ስራ ስኬት ሁሉም በተሳትፎ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ብለዋል፡፡ Slavian(1996) በበኩላቸው እንደገለፁት በትብብር መማር ወቅት የቡድንና የግለሰብ ሀላፊነት አፅኖት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የቡድኑ አባላት ለጋራ አላማቸው የጋራ ጥረት ማድረግ አለባቸው ፡፡ ለቡድኑ ውጤት የሚሰጠው እያንዳንዱ ተማሪ ስራ ከተገመገመ በኃላ ነው በመጨረሻም

ተጨማሪ እርዳታ የሚፈልግ ካለ ሊያውቅ እየታይባቸው መሆኑን ተገንዚበዋለች፡፡በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ ለመግለጽ የተለያዩ የሙከራ ተግባራት በሚሰጥበታ ወቅት በትክክል መግለጽ ስቸገሩ ይስተዋላል፡፡ከዚህ መነሻነት አጥኚዋ በዚህ ጥናት ትኩረት የሰጠችው በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና መይችላል፡፡በትብብር መማር ወቅት እያንዳንዱ የቡድን አባል መሳተፍን ለማወቅ መምህሩ ቀደም ብሎ የሰጣቸውን ተግባር መልሰው እንዲሰሩ በማድረግ በግል ይገመግማቸዋል፡፡ተማሪዎችም የግል ክትትል እንዳለ ካወቁ የበለጠ ጥረት በማድረግ ስራዎችን እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል Johnson& Johnson(1999)እንደገለፁት የቡድኑና የአባል ተጠያቂነት የማወቂያ መንገድ አንዱ ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ያሉትን ሌሎች ተማሪዎች እንዲያግዙ በማድረግ ነው ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምሁራን ከሰጡት ሀሳብ በመነሳት በትብብር መማር የምንለው የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በላቸው ውጤት መነሻነት፤ ከፍተኛ፣መካከለኛ እና ዝቅተኛ ብሎ በመክፈል በአነስተኛ ቡድን ውስጥ በማዋቀር ለጋራ ውጤት በመነሳት እርስ በርስ በመተጋገዝ፣ በመረዳዳት እንዲማሩ የሚያደርግ ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በበርካታ ተመራማሪዎች ዘንድ ትኩረት እያገኘ ከመጡት የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ትብብራዊ መማር መሆኑን ከላይ ከቀረቡ ገለጻዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡አጥኚዋ ከሚታስተምረው ከጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሁኔታ ሲትመለከት ተማሪዎች በመምህር መሪነት ብቻ የማስተማር ስነ ዘዴ ከመማራቸው የተነሳ በመጻፍ ችሎታ ላይ ሰፊ ውስንነት መኖሩን በመፈተሽ መመርመር ነው፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በመማር ማስተማር ክንውን ውስጥ ባለው የማያቋርጥ ሀደት ውስጥ እውቀትና የእውቀት ምንጮች፣የተማሪዎች ፍላጎትና ግንኙነት፣የፖሊሲ ምህዳር እና ሌሎችም የዕለት ተዕለት የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ መሆናቸው ይታዋቃል፡፡በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በየጊዜው በትምህርቱ ዘርፍ የምከሰቱ ለውጦችን ተገንዝበው የመማር ማስተማር ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን መዘጋጀት ሙያው ስነ-ምግባር የሚፈቅደው ተግባር ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጣቸው አጠቃላይ ዓላማዎች መካከል አንዱ፤ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ጠብቀው ድርሰት፣ደብዳቤ፣ሪፖርት መጻፍ እንዲችሉ ማድረግ መሆኑን በትምህርት ሚኒስቴር በ1994 ዓ.ም.ከተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ከዘጣነኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል መርሃ ትምህርት መገንዘብ ይቻላል፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ርዕስ ጥናትና ምርምር ለማድረግ መነሻ

ምክንያት የሆነኝ ከረጅም ጊዜ ከማስተማር ልምደ ያየሁት ተማሪዎች አንቀጽ፣ደብዳቤ፣ አስተዋጽኦ፣ድርሰት፣አሳጥሮ እንዲጽፉ ወዘተ... በሚጠየቁበት ጊዜ የሚጽፉት ጽሁፍ የሃሳብ ተያያዥነት ጉድለት፣የሰዋሰው ስህተት፣መደበኛ ቋንቋ ያለመጠቀም፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ያለመጠቀም እና የመሳሰሉት ስህተቶችን ሲፈጽሙ ስላስተዋኩት ተማሪዎችን ከዚህ ችግር ለማውጣት በትብብር መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ጥናትና ምርምር ባደርግ ችግሩ ይፈታል ብየ ስላመንኩት መነሻ ችግር አድርገዋለሁ፡፡

በሌላ በኩል የመጻፍ ችሎታን በትብብራዊ ዘዴ በማስተማር አበረታች የሆኑ ውጤቶች መገኘታቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ከነኚህም ጥናቶች መካከል ለምሳሌ የNunan(1992)ን መጥቀስ ይቻላል፡፡እኚህ ሰው በሶስተኛ እና በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ትምህርት ላይ ባካሄዱት ጥናት ተማሪዎቹ በትብብር በመማራቸው በመጻፍ ክህሎታቸው ከፍተኛ መሻሻል ታይቶባቸዋል፡፡

ይህ ጥናት የመጻፍ ትምህርትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ ከላይ ከተጠቀሱት ቀደምት ስራዎች ጋር የመፍትሔ ሀሳብ ለማፈላለግ ቢመስልም፤ትብብራዊ መማር ያለው ጠቀሜታ አስመልክቶ ወጥና ቀዳሚ ስራ መሆኑ፣ጥናቱ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ በወላይተኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ፣ጥናቱ የተካሄደበት አከባቢ፣ጥናቱ ያተከረበት የክፍል ደረጃና ሙከራዊ ጥናት መሆኑ ደግሞ  የሚለይባቸው ጎኖች ናቸው፡፡ መምህራን ተማሪዎች በትብብር እንዲማሩ በማድረግ የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን በመስጠት እና በማረም የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን አጥኚዋ ተገንዚበዋለች፡፡ከዚህም በመነሳት በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት የጽህፈት ትምህርት በትብብር መማርና በግል መማር ያለው የውጤት ልዩነት በማመዛዘን በትብብር መማር ላይ ትኩረት ለማስጠት ካላት ፍላጎት የተነሳ ይህንን ጥናት ልታጠና ተነሳሳች፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### *1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ*

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትብብራዊ መማር  የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ በጋቼኖ 2[ተኛ] ደረጃ ትምህርት ቤት በ10[ኛ] ክፍል ተተኳርነት በመፈተሽ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ነው፡፡በዚህም አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

### *1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች*

1.የመጻፍ ችሎታ ማሻሻልን በተመለከተ በትብብራዊ መማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ ማየት፣

2. በትብብራዊ መማር ምክንያት በተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ ላይ የሚታየዉ ለውጥ ከመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች አንጻር ምን እንደሚመስሉ ማየት፣

3.ትብብራዊ መማር ያለው አስተዋፅኦ ተማሪዎችን በቅድመና በድህረ ሚዘና በመፈተሽ በስመዘገቡት ወጤት መሰረት በማድረግ የመጻፍ ችሎታ ተሻሽሎ ማየት፡-

### **1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች**

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው፡፡ጥናቱን ውጤታማ ለማድረግ ይረዳው ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መናሻ አድርጌዋለሁ፡-በትብብራዊ ማስተማር ስነ ዘዴ በመጠቀም በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ የሚታየው ለውጥ ከመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች አንፃር ምን ይመስላል? በትብብር መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ከማሻሻል ረገድ ለተማሪዎች ምን ግንዛቤ ይኖራቸው ይሁን?ትብብራዊ የመማር ማስተማር ስነ ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ከማሻሻል አንጻር ያለው ሚና ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ጥናቱን ለማጠቃለል ነው፡፡

### **1.5. የጥናቱ መላምት**

በጥናቱ መነሻ ችግር ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሆኑና በጥናቱ መጨረሻ ሊረጋገጡ የሚችሉ የጥናቱ መላምቶች የሚከተሉ ናቸው፡፡

I. የመጻፍ ችሎታን በትብብር በተማሩና መምህር መራሽ በተማሩ ቡድኖች መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡

II. የመጻፍ ችሎታን በትብብር የተማረው ቡድን እድገት አሳይቷል፡፡

III. የመጻፍ ችሎታን በትብብራዊ የመጻፍ ዘዴ በተማረው ቡድን፣የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት ከመጻፍ ንዑሳን ክፍሎች አንጻር ልዩነት ታይቷል፡፡

IV. የመጻፍ ችሎታን በትብብራዊ መማር እና በመምህር መራሽ ስነ-ዘዴ በተማረው ቡድን በትብብር መማር በመጻፍ ችሎታ ላይ መሻሻል አሳይቷዋል፡፡

### 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች መካከል በጥናቱ ውጤት መሠረት መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻል አንጻር ትብብራዊ የመሰተማር ዘዴ መጠቀም የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ ዋነኛ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ አድርጎ ሊጠቀሙ ይችላሉ።መጽሀፍ አዘጋጆች የተማሪ መማሪያ ሆነ የመምህሩ መምርያ ሲያዘጋጁ ትብብራዊ መማር  የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ  ያለው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ በማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ወቅት ዘዴውን ከመጻፍ ክሂል አንጻር እንዴት አድርገው እንደሚያዘጋጁና የክፍል ውስጥ ተግባራትን እንዴት እንደሚያቀርቡ በትምህርታዊ አካሄድ ሊጠቀሙ ይችላሉ። በተመሳሳይ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሄዱ ተመራማሪዎች በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ለወደፊት ምርምር ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የመነሻ ሀሳብ (ጠቀሜታ) ይሰጣል።በአጠቃላይ የዚህ ጥናት መከናወን ለጥናቱ አቢይ ዓላማ ወይም በጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ስር ለተነሱት ጥቄዎች መልስ በመስጠት በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ዕድገት ላይ ለሚከናወኑ ቀጣይ ተግባራት የራሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል።

### 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በትብብራዊ መማር አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋነቋ የሚማሩ በወላይትኛ አፈ-ፈት ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታውን በማሳደግ አንቀጽ፣ደብዳቤ፣አስተዋጽኦ ድርሰት፣አሳጥሮ እንዲጽፉ ወዘተ…  ያለውን ሚና መፈተሽ ነው።ጥናቱ የተካሄደው በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ ካሉት ትምህርት ቤቶች መካከል በጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ሲሆን ትኩረቱም  በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ  የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ  ያለውን ሚና መፈተሽ በ10ኛ ክፍል ተተኳርነትን ነው።በመሆኑም ከመሰረታዊ የቋንቋ ክሂል ትምህርቶች (ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ) መካከል በመጻፍ ክሂል ትምህርት ላይ ያተኩራል። ከዚህም በተጨማሪ ከአሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ ስር የሚካተቱ በርካታ የማስተማሪያ ዘዴዎች ቢኖሩም ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው።

### 1.8 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የተካሄደው ከጊዜ እና ከአቅም ውስንነት አንፃር  በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ ከሚገኝ ከአምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጋቼኖ ከፍተኛ 2^ተኛ^ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በቂ ጊዜ በመስጠትና ተገቢ የናሙና አወሳሰድ ስልት በመከተል ትምህርት ቤቱ በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተከትሎ የተመረጠ በመሆኑ የተሸለ ተመራጭነት ያለው ሆኖ ቢገኝም በአንጻሩም በተወሰኑ ክፍሎች ብቻ የተደረገ በመሆኑ ለሁሉ ይረዳል የሚል የመጨረሻ ሊባል የሚችል ድሚዳሜ ላይ መድረስ ባለማስቻሉ ይህም ከጥናቱ ገደብ አንጻር የተከሰተ ውስንነት ነው፡፡

የዚህን ጥናት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቂዎች ማዘጋጀት፣ የጥናቱን አላማዎች መንደፍ፣ የጥናቱን ተሳታፊዎች መምረጥ ተገቢ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመምረጥና ተገቢ የመረጃ መተንተኛ ስልቶችን በመጠቀም የጥናቱን ውጤት መተንተንና ማብራራት ዋና ዋና የተከናወኑ ተግባራት ቢሆንም ሁሉንም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ተሳታፊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ቢከናወኑም ይህ ጥናት ከተለያዩ  ውስንነቶች ግን ሙሉ በሙሉ ነጻ ሊሆን አይችልም፡፡ይህ ጥናት በአስረኛ ክፍል ላይ ብቻ የተካሄደ በመሆኑ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አለመዳሰሱ ውስንነት ነው፡፡

### 1.9. የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ

ትብብራዊ መማር፡- ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር ባላቸው በሥርዓት በተደራጁ ቡድኖች በመሆን አንድን የትምህርት ግብ ለማሳካት በጋራ በመሆን እየተደጋገፉ የሚማሩበት ዘዴ  ነው፡፡

መላምት፡- አንድ ምርምር ከተከሄደ በኂላ ሊረጋገጥ የሚችል ወይም ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ውጤት ነው፡፡

መጻፍ ክሂል፡-ሀሳብን በተመለከተ በጽህፈት የመግለጽ ብቃትን ያመለክታል፡፡

የነጻነት ደረጃ፡-ሂሳባዊ እሳቤ ሲሆን መሰረት የሚያደርጋው የጥናቱ ተሳታፊዎች

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ፅሁፎች ክለሳ

## 2.1.መግቢያ

በምዕራፍ ሁለት ስር ተዛማጅ ፅሁፎች ተከልሰዋል፡፡ትኩረት ከሚያደርግባቸው ፅሁፎች መካከል በቅድሚያ የቀረበው የመማር ንድፈ ሀሳቦችንና ትብብራዊ መማርን የሚመለከት ነው፡፡በዚህ በትብብር መጻፍ ስር በየዘመናቱ የነበሩት የመማር ንድሀሳቦች መሰራታዊ ልዩነትና ትብብራዊ መማር የትኞቹን ንድፈሀሳቦች መሰረት እንዳደረገ የራሱ ገጽታ ይዳስሳል፡፡በተላይም የትብብር መጻፍ አላባዊያን፣የትብብራዊ መማር ጠቀሜታ፣የመጻፍ ክሂልና የማስተማርያ ስልቶች፣ ትብብራዊ መማርና የመጻፍ ክሂል በየደረጃው ቀርቧል፡፡

## 2.2. ከመጻፍ ትምህርት ጋር የተያያዙ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች

የመማር ንድፈ ሀሳቦች የአንድ ጀምበር ውጤቶች አይደሉም፡፡በየወቅቱ የሚነሱ ምሁራን ካላቸው ግንዛቤ በመነሳት የሚሰነዝሯቸው የመማር ምንነትና የማስተማር ዘዴዎች ጥርቅም ውጤቶች ናቸው፡፡ በቀጣይም በመማር ዙርያ ከሚነሱት ንድፈ ሀሳቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የባህርያዊ ንድፈ ሀሳብ፣የአእምሮታዊያን ንድፊ እና የምህበራዊ ግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ ሲሆን በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡እንደዚሁም ከንድፈሀሳቦች መካከል ደግሞ ለትብብራዊ መማር መሰረት የሆኑት ተዳስሰዋል፡፡

### 2.2.1. የባህሪያው ንድፈ ሀሳብ

የባህያውያን ንድፈ ሀሳብ በ20ኛው መቶ ክፍለዘመን መጀመርያዎቹ አመታት በjohnB.Watson ጠንሳሽነት እንድሁም በእነ Thomdike,Tolman,Guthrie,Hull,andSkinner ተከታታያነት የጎለበተ ንድፈ ሀሳብ እንደሆነ Brown(2007)የስረዳሉ፡፡ የባህያውያን እምነት መማር ግልፅ የሆነ እና የሚታይ የባህር ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ይህም ባህር የምዳብረው ተከታታይነት ባለው ቅስቀሳ እና ምላሽ ነው፡፡በመሆኑም ተማሪው አንድን መረጃ ያያል፤ይተገብራል፤እንደ አፈጻጸሙ አዋንታው ወይም አሉታዊ ምላሽ ያገኛል፡፡በዚህም ምክንያት አዲስ ልምድ ያደራጃል ወይም የባህር ለውጥ ያመጣል፡፡

### 2.2.2. የአእምሮታዊያን ንድፈ ሀሳብ

ይህ የመማር ንድፈ ሀሳብ ሳይንሳዊ ገጽታን የተላበሰና በስነሰብ፣በስነልሳንና በስነልቦና ሳይንስ ተመራማርዎች መስተጋብራዊ ጥምረት የተፈጠረ አዲስ የጥናት መስክ እንደሆነ Chinn(2011:53)ያስረዳሉ፡፡እንደኛሁ ሰው ገለጸ የአእምዊ ስነ ልቦና የመማር ንድፈሀሳብ የተጀመረው በ1950ዎቹ ውስጥ ነው፡፡ለዚህም ንድፈ ሀሳብ መጀመር በምክንያትነት የምጠቀሰው የባህራዊያን ስነልቦና አራማጆች ይከተሉት የነበረውም ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በዋነኛነት ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ችሎታ ላይ ነው በማንኛም የመጻፍ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ተግባቦታዊ ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው ንድፈሀሳቡ ይገልጻል፡፡

በመሆኑም አእምሮታዊያን በንድፈሀሳብ ዓላማ እና አንባቢው ወይም አድማጩ ከግምት ውስጥ በማስገባት የመጻፍ ትምህርት ሂደት መከናወን እንዳለበት ይጠቁማል፡፡በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ለጓደኛ ዳብደቤ መጻፍ፣ የሥራ ማመልከቻ መጻፍ እና የመሳሳሉትን የመጻፍ ተግባራት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲለማመዱ ዕድል ይፈጥራል፡፡በአጠቃላይ በዚህ ንድፈሀሳብ መሰረት ተማሪዎች የሚጽፉት ለመምህራቸው ለማሳየት ሳይሆን ለእውነተኛ ዓላማ እና ለእውነተኛ አድማጭ፣አንባቢ ይሆናል፡

### 2.2.3. የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ

የማህበራዊ ግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ መማር በመምህሩ አመንጪነትና በተማሪው ተቀባይነት የምከናወን ህደት ነው የምለውን የባህርያዊያንን የመማር ንድፈ ሀሳብ በመቃወም መማር በመምህሩ አመቻቺነት፣በተማሪው ጥረት ተግባራዊ የምደረግ ህደት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ንድፈሀሳብ በመጽፍ ትምህርት አውድ ውስጥ የላቀ ድርሻ አለው፡፡በዚህ ነድፈሀሳብ ላይ ተመስርቶ የሚያስተምር መምህር የመጻፍ ትምህርት ከማህበራዊ እና ከድስኩር አውዶች ጋር በማስተሳሰር የትምህርቱን ሂደት ሊያውቅ ይገባል፡፡በማበራዊ ግንባታዊያን ንድፈሀሳ በመምህሩ ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ ብቻ ሳይሆን ውጤት ላይ በመመስረት የትምህርቱን ሂደት ሊያከናውን ይገባል Zimmerman (1993)፡፡በውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የመጻፍ ውጤቶች ላይ በመመስረት የተረዱትን ትርጉም እየፈጠሩ እና እያደራጁ ይሄዳሉ፡፡በሂዳታዊ አቀራረብ ዳግሞ ተማሪዎች እርስበርስ እየተደጋገፉ እና ሀሳብ እየተለዋወጡ የመጻፍ ትምህርታቸውን ያከናውናሉ፡፡

ይህም ንድፈሀሳብ የመጻፍ ትምህርት የውህደተ ባህል ሞዴል እናሥነ-ልቦናዊ ውህደትን የተከተለ መሆን እንዳለበት ያስረዳል፡፡ተማሪው ወይም ጸሐፊው ከተለሚዷዊ ቋንቋ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርገው ተራክቦ ተነሳሽነቱ፣አመለካከቱእና መሰል ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታዎቹ ላይ ተጽዕኖ እንዲኖር ስለሚያደርግ ለውጤታማነቱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡በአጠቃላይ የማህበራዊ ግንባታውያን አተያይ ተማሪዎች በአካባቢያቸው አውድ ላይ ተመስርተው እርስ በርስ የሚፈጥሯቸው የሀሳብ ልውውጦች ውይይቶች የመጻፍ ክሂላቸው እየተሻሸለ እንዲሄድ ጉልህ ሚና እንዳለው ይገጻል፡፡

እንደ Brown(2007)የግንባትዊያን ንደፈ ሀሳብ የቅርብ ጊዜ ግኝት ነው፡፡የዚህ ንድፈሀሳብ አራመጆች መካከል Piajet እና vigotsky በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡የዚህ ንደፈ ሀሳብ አራማጆች ስለ መማር በዋነኛነት የምማነሱት ጉዳይ የሰው ልጅ ከነበረው ዳራዊ እውቀት በመነሳት ስለሚኖርበት አለም ለማዋቅ በምያደርገው ጥረታ ምንነቷን በመረዳት አድስ እውቀት በመገንባት አእምሮውን ያሳድጋል የምል ነው፡፡

## 2.3. የጽህፈት ክሂል ምንነት

የጽህፈት ክሂል ምንነት በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተገለጹ ሀሳቦችን እናገኛለን፡፡ከዚህ መካከል Widdowson(1987፡57)፣Harmer(1991:16) እና Raimes(1983፡5) ጽህፈት በእይታዊ ምልክቶች በመታገዝ ሰዎች ሀሳብን የሚለዋወጡበትና የእርስ በእርስ መስተጋብር የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያነው፡፡ጽህፈት በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተገኘን ዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መረጃን መቀበያ በእይታዊ ምልክቶች ቀርፆ ማቆያ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም ጽህፈት ገጠመኞችን ለመመዝገብ፣ የተለያዩ ጽሁፎችን (ደብዳቤ፣ዘገባ፣ማስታወሻ) ለመጻፍ፣ለማሰብና ለመማር የሚረዳ የቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ክሂል ነው፡፡Trakka(1990:2) እና Hadre (1988:5) እንደ Rivers(1981:291-294) እና Nunan (1989:36) አገላለጽ ማንኛውም ሰው ቋንቋ እንዴት መጻፍ እንዳለበት ለማወቅ የግድ መማር ይኖርበታል፡፡ Raimes (1983፣14) በበኩላቸው ቀደም ተከተላቸውን የጠበቁና እርስበእርሳቸው ቁርኝት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮችን በማመንጨት ሃሳብን በጽሁፍ መግለፅ የሚያስችል ክሂል እንደሆነ ያስረዳሉ Nunan(1989:36)Bell and Bumaby(1984)፡፡እንደ ጻሀፍው፣የጽህፈት ክሂል በአንድ ጊዜ የጽሁፍን ይዘት፣የአጻጻፍ ስልት፣የአረፍተ ነገር አወቃቀሩን የቃላት ምርጫ፣ሥርዓተ ነጥብ፣ የሀሳብ አንድነት፣ ግጥምጥምነትን፣ ተከታታይነትን ወዘተ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ከማሰብ ጋር የተያያዘ ውስብስብ ተግባር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

## 2.4. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ

የጽህፈት ትምህርት ተቀዳሚ አላማ ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት ሀሳባቸውን በተቃና መንገድ በመግለጽ ጽሁፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡እንደ Raimes(1983፣4-7)ገለጻ ተማሪዎች ጽህፈትን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ዓረፍተ ነገሮችን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ ይገባቸዋል በማለት ገልጻዋቸው የሚያካትቷቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡እነሱም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት እና ገጽ ለገጽ ተረክበውም ሃሳብን በጽሁፍ ለመግለጽ፣ዕውቀትን ለማግኘት፣ከእለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየትና በቋንቋው የሚጻፍ የጽሁፍ ሥራዎች በተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ማስቻል ናቸው፡፡ በተጨማሪም ምሁሩ ጽህፈትን መማር ሁለት ዓላማዎች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡አንደኛው ጽህፈትን በዓብነት በማስተማር የጽሁፍ ተግባቦታዊ ክሂሎች፣ርተዕነት (Fluency) እና ትክክለኛነት (Accuracy) ማለማመድ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የታለሚውን ቋንቋ ሥነ-ልሳናዊ ክህሎች ማለትም የቃላት፣የሰዋሰው ወዘተ ችሎታ ማስተማር ነው፡፡እንደ Brandy (1994, 135) አገላለጽ የጽህፈትን ትምህርት ዓላማ ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታው አኳያም ሊታይ ይችላል፡፡

ጽህፈትን መማር ለግለሰቡ አመለካከቱን ለመግለጽና ለመደገፍ፣አእምሯዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉ ሰነዶችን ለመመርመር ሲያግዘው ለማህበረሰቡም የጽሁፍ ቋንቋ ቅርጽ ለመያዝ፣የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎችን ልዩ ልዩ መረጃ ለማጠናከር ያገለግላል፡፡ Heaton(1991,138) በበኩላቸው ጽህፈትን መማር የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክህሎችን (ተገቢነት ያላቸው ዐረፍ ተነገሮችን የመጻፍ፣ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ለአገልግሎት የማዋል፣ተቀባይነት ያለውን ሃሳብ የመምረጥ፣የማመንጨትና አስፋፍቶ የማቅረብ፣ተፈላጊውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ አጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣የዓረፍተ ነገር እና አንቀጽ አወቃቀር ሥርዓትን ጠብቆ መጻፍ፣ የተለመደ እና መደበኛ ቋንቋን መጠቀም ወዘተ)ለማዳበር ይረዳል ይላሉ፡፡ ጠቅለል ባለ አገላለጽ የጽህፈት ትምህርት ዓላማዎች የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋሰው ዕውቀትን በማጠናከር በጽሁፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን ማለማመድ ወዘተ ናቸው፡፡

ከዚህ ባሻገር የመማሩ ዓላማ ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ማስገኘቱና ለጽሁፍ ተግባቦት አስፈላጊ የሆኑትን ክሂሎች ለማዳበር ማገዙ ተጠቃሽ ነጥቦች ሲሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጪ የሚሰሩ የጽህፈ ትምህርት

ተግባራዊ ድርሻቸው ጉልህ ነው።የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከታለሚው ቋንቋ የሚጠበቁትን ክህሎች እና ዕውቀቶች ማስጨበጥ ነው።

የጽህፈ ትክሂል መልመጃዎችም የራሳቸው የሆኑ ዓላማዎች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ።አንደኛው ኣላማ የተማሪዎችን ቋንቋ እውቀት ማለትም የቃላትና የሰዋሰው ችሎታ ማጠንከር ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ተማሪዎችን ተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት መልመጃዎች ዓላማ የተማሪዎችን የቃላትና ሰዋሰው እውቀትን በማጠናከር በጽሑፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል ነው።ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግር መግለጽ እንደሚችሉ ሁሉ በአእምሮአቸው የሚመላለሱትን ሀሳቦች በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸውን መዳበር አለበቸው።ይህም ከሚያዳምጡት እና ከሚያነቡት ተነስተው የሚረዷቸውን ሀሳቦች መዝግቦ ለመያዝ ይጠቅማቸዋል።በሂደቱም የቋንቋውን ምልክቶች ከመለየት ባሻገር ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን እንዲያውቁ ያግዛቸዋል።

## 2.5. የጽህፈት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆች

ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ የመግለጽ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ መምህሩ የጽህፈትን ክሂል በሚያዳብሩ እና ሰዋሰዋዊ የቃላት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህርቱን ማቅረብ እና በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆች ማስታወስ ተገቢ ነው (Attkin 1996:11)።የመጻፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የሚለማመዱበት መሆን አለበት።በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋሰውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት የጽሁፍ ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው።በክፍል ውስጥ የሚተገበሩ መልመጃዎች አስደሳችና የሚያነሳሱ ዓላማ ያላቸው የተማሪዎች የቋንቋ ደረጃና ልምዳቸውን ያገናዘበ፣ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ የሚያስችል፣በውይይትና በቡድን ለመጻፍ ምቹ የሆነ፣ግልጽ መማሪያዎች ያሉትና ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣እንዲያረቁንና እንዲከልሱ የሚያበረታታ እንዲሆን ያስፈልጋል። (Attlcins 1996:11)በጽህፈት ክሂል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል Raime(1983:5-10) Richards(1990፣106)Byme(1992:21)Nunan(1989፣36)ውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ፣ ወሂደት አቀራረብ እና ውህደት አቀራረብ በማለት ገልጸዋል።

### 2.5.1 ውጤት ላይ ያተኮረ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ

ይህ ዘዴ ከጽሁፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች የመጀመሪያው ሲሆን የሚያተኩረውም ተማሪዎች በጻፉት የመጨረሻ ሥራ ላይ ነው፡፡ ዓላማው ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የጽህፈት ትምህርት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑ የጻፏቸው ነገሮች ከሰዋሰው፣ ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ከሀሳብ ቅንጅት፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ከግልጽነት ወዘተ አኳያ ይገመግምሉ፡፡ በሌላ በኩል Ricards (1990:106) በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች በተለያዩ አንቀጾችና ጽሁፎች የማዋቀር ቅንብር ስልት ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ይመራቸዋል ይላሉ፡፡ ምክንያቱንም ሲገልጹ የዘዴው ትኩረት ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ጽሁፍ እንዲጽፉ ማስቻል ስለሆነ የተፈለገውን የጽሁፍ ቅርጽ እንዲያጠኑ በማድረግ ወደ ፊት ታዘው በሚጽፉት ነገር ላይ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋቸዋል ይላሉ፡ ፡ እንዲሁም አተገባበሩን ተማሪዎች ሞዴል ዓረፍተ ነገርን ደግመው እንዲጽፉ የሚጋብዝ መልመጃ መስጠት እንዳንድ ጊዜም ከአንድ ነገር ቅርፅ ወደ ሌላ አይነት ዓረፍተ ነገር ቅርፅ የመቀየር ተግባራትን ለማከናወን የሚጋብዝ መልመጃ በመስጠት የሚተገበር መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ዋናው ትኩረቱ በሰዋሰው፣ በቅርጽና በሥርዓተ ነጥብ ከመሆኑም ባሻገር ተማሪዎችን ስህተት የመፍጠር አጋጣሚ እንዲያገኙ ጥረት በማድረግ ልዩ ሥፍራ ይሰጣል፡፡

ውጤት ላይ ባተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የሚገኝ ተግባራት ውስን ጽህፈት (Controlled writing)መር ጽህፈት (Guided writing)እና ነፃ ጽህፈት(Free writing)በመባል በሦስት ያከፈላሉ(Richordes 1990;107) ስለዚህ የጽህፈት ተግባራት ሲገለጹ በወጥነት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ መልመጃዎች ሁል ጊዜ የሚጀመሩበት በውስን ጽህፈት መልመጃ ነው፡፡ከዚም ቀስበቀስ ወደ ነጻ የመጽፍ ክሂል መልመጃ ያመራሉ በማለት ገልጸዋል፡፡

### ሀ. ውስን ጽህፈት

የውስን ጽህፈት መልመድ በአብዛኛው በጀማሪ ተማሪዎች ለሚካሄድ የጽህፈት ትምህርት የሚቀርብና ተማሪዎች ወደ መር ጽህፈት ከመሸጋገራቸው በፊት የሚለማመዱበት የመጀመሪያ መልመድ ነው፡፡ውስን ጽህፈት ደረጃ ተማሪዎች ሥራቸውን የሚሰሩት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በአግባቡ በመከተል ነው፡፡ የክንውኑ ዓላማም ከስህተት የጸዳ ዓረፍተ ነገር ወይም አነስተኛ ጽሁፍን እንዲጽፉ ለተማሪዎች እድል መስጠት ነው፡፡ በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ውስጥ የጽህፈት መልመድ ዓላማው ስህተት በማስወገድ ላይ መሆኑንና ለመማር ማስተማር

የሚቀርቡት መልመጃዎች ማሰብንና ፈጠራን የሚጠይቁ ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል(mcdonouge) and (Shaw 1973፣178) እና (Harmer 1991፣109)

### ለ. መር ጽህፈት

ይህ የጽህፈት ደረጃ ተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ወደ ነጻ የጽህፈት መልመድ የሚያሸጋግር ድልድይ ነው፡፡እንደ pincas(1982፣126) አገላለጽ በመር የጽህፈት መልመጃ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ሀሳብ የመጨመር ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም ከውስን የጽህፈት መልመጃ ይልቅ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተሸለ ነፃነት አላቸው፡፡

ነፃነቱም ግን በነፃ ጽህፈት ጊዜ ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ሞዴል ይሰጣቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል Raimes (1983) መር የጽህፈት መልመድ ቁጥጥር ከውስን ጽህፈት ያነሰ የሚሆነው የሚሰጣቸው ጽህፈት ቅርፅና ይዘት ሙሉ ለሙሉ ለተማሪዎች ስለ ማይቀርብላቸው ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በመር ጽህፈት ጊዜ ተማሪዎች አንድ የተጀመረውን ውጥን ታሪክ፣ ደብዳቤ አንቀጽ ወዘተ እንዲያሚሉ የሚታዘዙ መሆኑ ነው፡፡ የሚጨምሩት ሀሳብ ግን በጅምር ከቀረበው የአንቀጽ ሀሳብ ጋር የሚስማማ መሆን ይኖርበታል፡፡ እነዚህ የጽህፈት ተግባራት ለተማሪዎች መነሻ የሚሆን ፍንጭ በመስጠት የራሳቸውን ሀሳብ አክለው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ የሚያለማምድ ነው፡፡ (Raimes 1983፤103) የሚቀርቡት ተግባራት

- በሰንጠረዥ የሚቀርቡ ሀሳቦችን ወደ ጽሁፍ መቀየር
- በጅምር የቀሩ ጽሁፎችን (ውጥን ታሪኮችን፣ደብዳቤዎች ቅርጾችን ወዘተ) መጨረስ
- የተዘጋጀ ቢጋር ተጠቅሞ አንቀጽ መጻፍ
- የቀረቡትን ነገሮች በማወዳደርና በማነጻጸር በጽሁፍ መግለጽ እና
- ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለጥያቄዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መነሻ አድርጎአጭር ታሪክ
- መጻፍ የሚሉ ይገኙበታል (Attkins 1996፣11)፡፡

### ሐ- ነፃ ጽህፈት

ነፃ ጽህፈት መልመድ ከመር የጽህፈት መልመድ ቀጥሎ የሚመጣ በውጤት ላይ ያተኮረ የአቀራረብ ዘዴ የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡ ይህ የጽህፈት መልመድ ከመር መልመድም ይሁን ከውስን መላመጃዎች የበለጠ ለተማሪዎች ሰፊ እውነትን ይሰጣል፡፡pineas(1982፡106) እንደ

ሚገልጹት ነጻ የጽህፈት መልመድ በተማሪዎች የሚሰጣቸው መልመድ ርዕስ ወይንም በመረጡት ሀሳብ በራሳቸው የሚያከናውኑት መልመድ ነው፡፡ተማሪዎች ጽሁፍን የሚጽፉት ከራሳቸው አፍልቀው ሲሆን በሚጽፉት ነገር ላይም የሚደረገው ቁጥጥር የላላ ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ የነጻ ጽህፈት መልመድ ትኩረት የሚሰጠው ሁሉንም ነገር እንዲጽፉ ሳይሆን የተማሩትን ለመጻፍ ብቻ ነው፡፡ተማሪዎች በውስንና በመር የጽህፈት መልመጃ ያገኙትን እውቀትና ልምድ በማቀናጀት ራሳቸውን ችለው መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡በነጻ የፅህፈት ትምህርት መልመድ ምንም እንኳን ተማሪዎች በውስንና በመር የጽህፈት መልመጃዎች የተማሩትን እንዲችሉ ቢደረግም ሀሳቡን የሚያቀናጁት በራሳቸው ስለሆነ ሰፊ ነጻነት አላቸው፡፡እንደ Raimes (1983፣7) አገላለጻ ደግሞ ነጻ ጽህፈት ለሰዋሰዋዊ አጠቃቀም፣ለሥርዓተ አጻጻፍ እንዲሁም ለትክክለኛነት ትኩረት የሚሰጥ ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የመግለፅ እድል አላቸው፡፡በውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች Richards(1990፣112)፣Murry (1980)ን ጠቅሰው ይህ ዘዴ የተማሪዎች የመጨረሻ የጽህፈት ሥራ ውጤት አንዱ የአጻጻፋቸውን ሂደት እንደሚያሳይ ይገልጻሉ፡፡በአሁኑ ጊዜ ስለጽህፈት ትምህርት የሚያጠኑ ምሁራንም በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ፅህፈትን ለማስተማር ችግር እንዳለበት ያመለክታል፡፡ምክንያቱ ሲገልጹ ዘዴው የሚያተኩረው አንዱ የጽህፈት ተግባር‹‹እንዴት ሆኖ ተጠናቋል›› የሚለውን እንጂ ጽሁፍ አንድን ለመጻፍ ‹‹ምን ዓይነት አካሄድ እንከተል›› የሚለውን አያመለክትም በማለት ያብራራሉ፡፡በተጨማሪም ይህ ዘዴ በተጻፈው ነገር ትክክለኛነት ላይ ግምት አለው፡፡በዚህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪው የጽሁፍ ቅርጾችን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት ነው፡፡ይሁን እንጂ ይህ ውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው የጽሁፍ ቅርጾች እንዴት ማደራጀት እናዳለበት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው በራሱ መንገድ ሀሳብ አፍልቆ አደራጅቶ የራሱን ጽሁፍ እንዴት መጻፍ እንደሚችል አይገልጽም በማለት ይተቻሉ፡፡በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴን አስመልክቶ pincas (1982፣24) እንደሚገልጹት በዚህ ዘዴ ተማሪው የሚያከናውነው በመምህሩ አድርግ ተብሎ የታዘዘውን ብቻ በመሆኑ የፈጣሪነት ባህሪይው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፡፡ በሌላ በኩል Raims (1983፣17)በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች እንዴት እና ለምን እንደሚጽፉ ከማሳየት ይልቅ የጽሁፍ ቅርፆችንና የሰዋሰው ህጎችን ተከትለው እንዲጽፉ የሚገፋፉ ነው፡፡ውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ በሂደታዊ ክሂል ዋጋ

አይሰጥም፡፡በመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ዋና ትኩረትም ጽሁፍ በሚዘጋጅበት ሂደት ላይ ሳይሆን ተጠናቆ በሚቀርበው ሥራ ላይ ከመሆኑም ባሻገር ውጤቱም የሚለካው ከትክክለኛነት አንጻር ነው (Badger and Goodith good)፡፡

### 2.5.2 ሂደታዊ አቀራረብ

‹‹ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ Raims (1983፣10) ላይ በአሁኑ ጊዜ የጽህፈት ትምህርት በውጤት ላይ ካተኮረ አቀራረብ ይልቅ ወደ ሂደት ተኮር የመለወጥ አዝማሚያ እያሳየ መጥቷል፡፡በሂደት ተኮር ተማሪዎች የሚጽፉበትን ተግባርና ተደራሲያንን ከማሰብ አልፈው እንዴት አድርጌ እጽፈዋለው እንዴትስ እድርጌ እጀምረዋለው፡፡›› የሚሉትን ጥያቄዎች ማሰብ ይኖርባቸዋል፡፡የዚህ አቀራረብ ትኩረት በመጻፍ በተደረሰበት ውጤት ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ለመጻፍ በሚያልፉባቸው ሂደቶች ላይ ነው፡፡ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሚያተኩረው ተማሪው አንድን የጽህፈት ተግባር እንዴት አድርጐ ጀምሮ ከዚያም እንዴት አድርጐ አቀናጅቶ በራሱ መጻፍ ይችላል በሚለው ላይ ነው፡፡በመሆኑም ይህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪ መራሽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ምክንያቱም ትልቁን ሚና የሚጫወተው ተማሪ ነውና፡፡ Richards (1990፡111) በሂደታዊ አቀራረብ የመምህሩ ሚና በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ማመቻቸት ነው፡፡

መምህራን ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ እየተንቀሳቀሱ በማየት ተማሪዎችን ያበረታታሉ፡፡ በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ጽሁፍ ለመጻፍ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የተግባር ደረጃዎች እንዳሉ Hedge (1988፣15) እና Richards 1990፣118) ይገልጻሉ፡፡እነዚህ ምሁራን የጠቀሷቸው የተለያዩ ደረጃዎችና በሂደታዊ አቀራረብ የጽህፈት ትምህርት ተግባራት በሂደት ለማሳየት የቀረቡ ሲሆን ይዘውት የተነሱት መሰረታዊ ሀሳብም ከሞላጎደል ተመሳሳይ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ Richards (1990108) በሦስት ደረጃ ከፍለው የሚያስቀምጧቸው የዘዴው አቀራረብ ስልቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### ሀ. ቅድመ ጽህፈት

ይህ ደረጃ በሂደት ተኮር ውስጥ ካሉት የጽህፈት ትምህርት አተገባበር የመጀመሪያው ነው፡፡ ቅድመ ጽህፈት ሊያካትታቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል የሚጽፉበትን ርዕስ መምረጥ፣ስለ ርዕስ ማሰብ፣ተደራሲያንን መመልከትና ለምን ዓላማና ተግባር እንደሚጽፉ ማወቅ ይገባቸዋል (Richards1990፣109)፡፡ተማሪው መረጃ ለመሰብሰብ፣አንባቢውን ለመገመት፣ዓላማውን

ለመወሰንና የመጀመሪያን ድረፍትን ለማቀድ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ቅድመ ጽህፈት ለመጻፍ የሚያስችል ሀሳብ የሚሰበሰብበት ጊዜ ነው፡፡አንድ ጽሁፍ ከመጻፉ በፊት ለሚጻፍበት ርዕስ ጉዳይ ይታሰባል፣ርዕሱ ምን ዓይነት ስፋትና ጥልቀት አለው? ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦችስ ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ የሚፈለግበትና አእምሮ ጓዳ የሚፈተሸበት ጊዜ ነው፡፡ይህ ደረጃ ድንገት በአዕምሮ የሚመጣ ማንኛውም ሃሳብ የሚሰበሰብበት ወቅት ነው፡፡እነዚህን የተለያዩ መረጃዎች ለመሰብሰብ ከሚያስችሉ ነገሮች መካከል አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## ለ. የጽህፈት ጊዜ

ይህ ከሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አተገባበር ዘዴዎች መካከል ሁለተኛው ደረጃ ነው፡፡የጽህፈት ጊዜ ሀሳብን በወረቀት ላይ በረቂቅ መልክ ማስፈርን ይመለከታል፡፡ደረጃውም ትክክለኛ የጽህፈት ተግባር የሚጀምርበት ሲሆን ተማሪው በቅድመ ጽህፈት ደረጃ የሰበሰባቸውን ሀሳቦችን በረቂቅ መልክ ወረቀት ላይ የሚያሰፍሩበት ጊዜ ነው፡፡ተማሪው በተጨማሪም ሀሳቦችን አብራርቶ ግልጽ በሆነና አሻሚነት በሌለው ቋንቋ የሚሰፍርበት ለጽሁፍ ቅርጽ በራሱ የሚፈጥርበት ደረጃ ነው፡፡ (Richards 1990፣109)እንደ Hedre (1988፣11) ገለጻ በዚህ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት በርካታ ናቸው፡፡ለአብነት ያህል ማቀድ፣ ማርቀቅ፣መከለስ፣ ደግሞ ማቀድ ይጠቀሳሉ፡፡ በመከለስ ደረጃም ከሚካሄዱት ክንውኖች ቅድሚያ የሚሰጠው የይዘት ትክክለኛነት ነው፡፡ተማሪዎች የተጻፈውን መገምገምና የሚጨመሩ ወይንም የሚቀነሱ ሀሳቦች ካሉማስተካከያ ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የመጀመሪያውን ረቂቅ ሲጽፉ መግለጽ በፈለጉት ይዘት ላይ ማተኮር አለባቸው፡፡

## ሐ. ድህረ ጽህፈት

ይህ ደረጃ ከሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አተገባበር መካከል የመጨረሻው ነው፡፡ድህረ ጽህፈት ወይንም ማቃናት የተጻፈውን ነገር የሚገመግምበትና በጽሁፍ አማካኝነት ለማስተላለፍ የተፈለገው ነገር በትክክል እንዲተላለፍ የመጨረሻ ማስተካከያ የሚደረግበት ነው፡፡ተማሪው መልእክቱን ቅርጹንና አናባቢውን የሚያመነጭበት ግልጽነቱን የሚገመግምበትና ጽሁፉን ደግሞ በማንበብ ለአናባቢው በሚመች መልኩ መቅረቡን የሚያረጋግጥበት የክንውን ደራጃ ነው(Richards 1990፣109) ድህረ ጽህፈትን አስመልክቶ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ድህረ ጽህፈት በቅድመ እና በጽህፈት ጊዜ የተሰበሰቡትና የተረቀቁት ሀሳቦች ተገቢነት

የሚገመገምበት ደረጃ ነው፡፡በአጠቃላይ ተማሪው ያረቀቃቸውን ሀሳቦች ከመግለጽ እና ከአንባቢው አኳያ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት መቅረብያ ለመቅረቡን የሚመረምርበት ነው፡፡ በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ አስተያየት Attkins (1996፣120) ዘዴውን አስመልክተው‹‹ሂደታዊ የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ድክመት ሙሉ ለሙሉ ነጻ ጽህፈትን ተጠቅሞ ተግባራዊ ማድረግ የተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ ያዳብራል ብሎ መገመት ነው››ይላሉ፡፡ Horowitz (1986፣445)በበኩላቸው ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት የሚከተላቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ይህም በአንጻሩ ሂደቱ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆችን እንዲጽፉ የሚሰጠው ትኩረት ሁል ጊዜ ለሚጽፉት ድርሰት ብቁ እያደረጋቸውም በብጤ እርማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱም ተማሪዎች ስለራሳቸው ችሎታ ያላቸው ግምት የተሳሳተ እንዲሆን ያደርጋቸዋል ለማለት ይተቻሉ፡፡

### 2.5.3. ውጤት ውሂደት አቀራረብ

ይህ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በስፋት አገልግሎት ላይ የዋሉትን በውጤት ላይ ያተኮሩና ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረቦችን በማጣመር የቀረበ ዘዴ ነው፡፡እነዚህ ዘዴዎች በተናጠል ውጤታማ ባለመሆናቸው ክፍተታቸውን ለመሙላት የቀረበ ነው፡፡የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለውጤትም ሆነ ለሂደት እኩል ትኩረት መስጠት እናዳለበት ያምናል፡ ፡የተማሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችን ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል ፡፡በተጨማሪም የተማሪዎች ጽህፈት ልምምድ የተወሰነ አዓማ እና ግብ ሊኖረው ይገባል የሚል የአሰራር መርህ ያለው ነው (Dyer1996፣312)Horowitz (1986፣447) እንደገለጽት ሁለቱን አጣምሮ በስራ ላይ ያዋለው ውጤት ውሂደት ዘዴ በኋላ ተግባር ተኮር (Task based) ተብሎ እንደዳበረም ይገልጻሉ፡፡አያይዘውም ይህ ዘዴ አንባቢን መሰረትአድርጎ በተለይ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ ሆኖ እንደተገኘ ያስረዳሉ፡፡እንደ Raimes (1983፣11) ገለጻ በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በተናጠል ሚተገበሩ አይደሉም፡፡የክፍል ውስጥ በአንድ ጊዜ ብቻ ተመስርቶ (ሌሎች ዘዴዎችን ሳያካትት) ጽህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ ነው፡፡ለምሳሌ በሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ የሚያስተምር መምህር ከተማሪዎች አቅም እና ፍላጎት አንጻር እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ዘዴዎች ጠቀሜታዎች ናቸው፡፡የጽህፈትትምህርትአቀራረብ አንድን ዘዴ ብቻ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ከሁሉም ዘዴዎች የተወጣጣ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጹት የምሁራን ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው አንድን ዘዴ ብቻ ተጠቅሞ ማስተማር እንደ ማይቻልና የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች የተለያየ የማስተማሪያ ስልቶች ቢኖራቸውም በክፍል ውስጥ ባላቸው አተገባበር የተደጋገፊነት ባህርይ ስላላቸው በስብጥር እንደ ሚቀርቡ ነው፡፡

## 2.6. መጻፍ ለምን አዳጋች ይሆናል?

መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣የሀሳብ ፍሰትን፣የቃለት አመራረጥን እና የአገላለፅ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ስለዚህ ብዙዎች እንደ ሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ሆኖም ግን የመፃፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለፃል፡፡መፃፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት Byme(1988) ሲያስረዱ ሦስት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፡-እነሱም ስነልቦናዊ ችግር፣ሰዋሰዋዊ ችግር እና ግንዛቤያዊ ችግር ናቸው ብሎ ተንትኑል፡፡

### 2.6.1. ሥነ-ልቦናዊ ችግር

መፃፍ ከንግግር የበለጠ ስነልቦናዊ ጫና ያሳድራል Byme (1997፤4) እንደሚያስረዱት ንግግር ተፈጥሯዊ፣በየትኛውም ሁኔታ እና አጋጣሚ የምንጠቀመው የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ውስጥ ስንናገር ስህተት ብንፈጽም ከአድማጭ እርማት እናገኛለን፣ ሀሳባችንን በፅሁፍ ስንገልጽ ግን ያለምንም እገዛና ያለምንም ማስተካከያ በራሳችን የምንወጣው ተግባር ይሆናል፡፡ይህ ደግሞ የስነ-ልቦና ጫና ስለሚያደርግ መፃፍን አስቸጋሪ ያደርገ ነው፡፡

### 2.6.2. ሠዋሰዋዊ ችግር

እንደ Bxme (1997፤4-5) ገለፃ በንግግር ወቅት ገለፃ ስናደርግ አድማጭ ንግግራችን እንዲቀጥል ያግዘናል፡፡ንግግራችን ላይ ችግር ቢፈጠር እየደጋገምን ወደ ኃላ እየተመላለስን አስተካክለን መቀጠል እንችላለን፡፡በፅሀፈት ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ እድሎች አይኖሩም ተግባቦታችን በራሳችን ችሎታና እውቀት ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡በራሳችን የቃላት ምርጫ፣ ራሳችን የቃላት መዋቅር አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይጠበቅብናል፡፡ከዚህ ሂደት በኃላ የፃፍነው ፅሁፍ በአንባቢ ይተረጎማል፡፡ይህ ደግሞ ሌላው ፅህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርግ ነገር ነው፡፡

### 2.6.3. የግንዛቤ ችግር

እንደቀደሙት ሁሉ በዚህም ጊዜ ንግግር መልዕክት ለማስተላለፍያ ለምንም አጋዥ፣ያለምንም አስገዳጅነት በራሳችን ፍላጎትና ባሻን ጊዜ የምንጠቀመው መግባቢያ ነው፡፡ይህ ደግሞ ምንም አይነት ትምህርትና እውቀት አያስፈልገውም፡፡ መፃፍ ግን በመደበኛ መንገድ የምንማረው የራሱ

ህግና ስርዓት ያለው መግባቢያ ነው፡፡የቋንቋውን የፅህፈት ህግ በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ የቋንቋው የፅህፈት ህግ ብቻ ሳይሆን ሃሳባችንን በፅሁፍ እንዴት መግለፅ እንዳለብንና ከአንባቢያችን ጋር ያለምንም ችግር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ይኖርብናል፡፡ይህ ሶስተኛው የመፃፍን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርገው ሂደት ነው በማለት (Bym1997፣5) አብራርተዋል፡፡እንደ ተስፋዬ (1981፣62) አገላለፅ ፅህፈት የሀሳብ አቀነባበርን የሀሳብ አደራደርን የቃላት አመራረጥና የአገላለፅንም ስልት የሚጠይቅ ነው፡፡ደብዳቤዎች፣የድርሰት ጭብጥ፣ ሪፖርት ወ.ዘ.ተ ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች ሲሆኑ እነዚህን ለመፃፍ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ደረጃ በደረጃ ለመለማመጃ የሚሆን መልመጃዎች በመክተት የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ይቻላል፡፡

### 2.7. የትብብር መማር ምንነት

በትብብር መማር አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ለአብነት ያክል የተወሰኑትን ስንመለከት Johnson & Johnson (1999) በትብብር መማር የሚባለው የአነስተኛ ቡድን ተማሪዎች አንድ ላይ በመስራት የራሳቸውንና የሌሎችን መማር ሁኔታ የሚያሻሽሉበት (የሚያሳድጉበት) እንደሆነ ሲገልፅ Ricrages &Rodgers (2003) በበኩላቸው ከሁለት እስከ አራት አባላት ያለው ቡድን የተሻለ ስራ ይሰራ ዘንድ መምህሩ የተለያዩ የትብብራዊ መማሪያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡Slavin (1987) ሲገልፁ በትብብር መማር የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትንሽ ቡድን በማቀናጀት እርስ በርስ በመበረታታት አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ሲገልፁ ተመሳሳይ Kagan&Kagan (2009)በትብብር መማር ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ እንደ ሆነ በመግለፅ የተለያዩ የትምህርት ዓይነት ያላቸው ግንዛቤ ለማሻሻል ልዩልዩ የመማር ተግባራትን የሚያከናውንበት ነው ብለዋል፡፡

ይህንን ሲያብራሩ እያንዳንዱ የቡድን አባል ያወቁትን ነገር እርስ በርስ በመከፋፈል በመረዳዳት ቡድናቸውን ስኬታማ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ አረዳድ እስኪኖራቸው ድረስ በጋራ አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ሌላው ስለትብብር መማር ብያኔ የሰጡት Johnson and Johnson (2009) ሲሆን ራሳቸውን እንደ አንድ የቡድን አባል አድርገው የሚቆጥሩ ተማሪዎች አብረው በመሆን ለጋራ ውጤት መሳካት በትብብር እና በመረዳዳት የሚሰሩበት ነው ሲሉ ተመሳሳይ Johnson and Johnson and smith1988 አነስተኛ ቡድን ተማሪዎች የጋራ አላማቸውን (ግባቸውን) ሊያሳኩ የሚችሉት ሁሉም የቡድን አባላት የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት ሲወጡ ነው በማለት አብራርተዋል Rita Rani (2009) በበኩላቸው በትብብር መማር ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች አብረው ሰርተው

የጋራ የሆነ አጥጋቢ ምላሽ የሚያገኙበት ነው፡፡ጥሩ የሆነ ስራ ከስሩ በጋራ የሚሸለሙበት ከተጠበቀው በታች ከስሩ ደግሞ የሚቆጩበት ነው ይላሉ፡፡አያይዘውም ያለውን ጠቀሜታ ሲገልፁ የሚማሩበት የትምህርት ይዘት እንዲገነዘቡ ያነቃቃቸዋል፡፡እርስ በርስ ተወዳዳሪ መንፈስ ተገልፀው በመተሳሰብ ለጋራ ጥቅም በጋራ ይሰራሉ፡፡በትብብር መማር ተማሪዎች ማህበራዊ ክህሎቶቻቸውን የሚያሳድጉበት የእርሰ በርስ የመረዳዳት መንፈስ ማዳበር በቡድናቸው ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የማስተማሪ ዘዴ ነው፡፡ይህን አስመልክተው Johnson and Johnson Monson (2012) እንዳስቀመጡት በትብብር መማር በአዲስ የማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት በንቃት እንዲገነዘቡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ነው፡፡እንዲሁም መማር ማህበራዊ እንደመሆኑ መጠን ተግባሩን ለመፈፀም ተማሪዎች በትብብር እንዲሰሩ በማድረግ የእረሰ በርስ ግንኙነታቸውን አዎንታዊ እንዲሆን፣ችሎታቸውን ብቃታቸውን በማሳደግ ተፈጥሮ ባደለቻቸው ስጦታ ላይ እንዲነሳሱ የሚያደርግ ነው ብለው Knight (2009) እንደገለፁት በትብብር መማር ተግባር ከመምህራን ይልቅ በተማሪዎች በበላይነት የሚከናወን ሲሆን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተማማሩ የቀረበውን ትምህርት ይዘት ይሸፍናሉ፡፡

በዚህ ወቅት ተጠቃሚ የሆነውን ማህበራዊ ክህሎቶቻቸውን እያሳደጉ ይሄዳሉ፡፡በተመሳሳይ Cheong (2010) እንደ ተናገሩት በትብብር መማር በራሱ የእርስ በርስ የመግባባትን ክህሎት ማዳበሩ እንደ ትምህርት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡በቡድን ውስጥ ማህበራዊ ክህሎትን ማሳደግ ተማሪዎች ጥራት ያለውን ተግባር በጋራ ሆነው እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምሁራን ከሰጡት ሀሳብ በመነሳት በትብብር መማር የምንለው የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ባላቸው ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ከፍተኛ፣መካከለኛ እና ዝቅተኛ ብሎ በመክፈል በአነስተኛ ቡድን ውስጥ በማዋቀር ለጋራ ውጤት በመነሳት እርስ በርስ በመተጋገዝ፣ በመረዳዳት እንዲማሩ የሚያደርግ ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡በተጨማሪም በትብብር መማር ወቅት ተማሪዎች በቡድን ውስጥ በመሆን የተለየዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እርስ በርስ በመረዳዳት እና በመደጋገፍ የራሳቸውን መማር ሁኔታ በማሳደግ የሌሎችም እንዲያድግ ማድረግ፤አብረው በሚሰሩበት ጊዜ የአስተሳሰባቸው አድማስ ከመስፋቱ በተጨማሪም ማህበራዊ ክሂሎታቸውም እያደገ ይሄዳል፡፡

## 2.8. የትብብር መማር ጠቀሜታ

Lita rani (2009) ስለ ትብብር መማር ጠቀሜታ ሲገልፁ የተማሪዎች በጥልቀት ማሰብን ያጎለብታል፣አካባቢን በደንብ ለመረዳት ያስችላል፣የደካማ ተማሪዎችንም አቅም ከፍያደርጋል፣ እንደ አንድ የመማሪያ ዘዴ አማራጭ በመሆን ያገለግላል ይላሉ፡፡Richard & Renday (2002) የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ በትብብር መማር ያለውን ፋይዳ ሲያስቀምጡ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ዘናብለው መወያየት እንዲችሉ ማድረግ፣ችግሮችን ተወያይተው እንዲፈቱ ማስቻል፣ጥልቅ የሆነ የመስራት ፍላጎት እንዲኖራቸው እና በአጭር ጊዜ እየተነጋገሩ ብዙ ጥያቄዎችን መስራት ይችላሉ ብለዋል፡፡አለማየሁ (2009) በበኩላቸው Veenman (2000) Kagan (2007) እና Jollife (2007) በመጥቀስ እንደገለፁት በትብብር መማር የተማሪዎችን የተሻለ የመማር ማህበራዊ ክህሎትን፣ስነልቦናዊ እድገትን አዕምሮአዊ ክህሎትን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡በአጠቃላይ ምሁራን ስለ ትብብር መማር ጠቀሜታ የገለፁትን ሀሳብ የሚያጠንክር ሌሎች በዝርዝር በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

### 2.8.1. የአካዳሚካል ጥቅም

አብዛኞቹ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች እንዳስቀመጡት የተማሪዎች መማር ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የሚችለው በትብብር መማር መሰረታዊ መርህ የሆነውን አወንታዊ መደጋገፍ፡፡ "ሁሉም ለአንድ፣አንድ ለሁሉም" የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ (ስሜት)ተማሪዎች ሲያዳብሩ ነው Akhtar et al (2012)በመማር ማስተማር ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በትብብር እንዲሰሩ ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነ ተማሪዎች በትምህርትና በማህበራዊ እሴታቸው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡በትብብር በሚማሩ ቡድኖች የሚወያዩትና በመከራከር በትምህርት ክፍለ ጊዜው የሚጠቀሙበትን መሳሪያዎች ፅንሰ ሀሳቦችን መረዳታቸውን መግለፅ ይችላሉ፡፡በተጨማሪም እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ እውነቶችን ለማስጨበጥ ይችላሉ፡፡Slavin & Cooper (1999) ሀሳባቸውን እንደአስቀመጡት በትብብር መማር አላማው ተማሪዎች በትምህርታቸው ያላቸውን ስኬታማነት ከፍ እንዲልማድረግ ነው፡፡ይህም የሚሆነው እረሰ በርሳቸው ለመወያየት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመፍጠር እንዲማሩበት ማድረግና በማነጋገር የላቀ ውጤት ለማምጣት ለማበረታታት ነው፡፡

### 2.8.2. ፈጠራ እንዲጨምር ያደርጋል

Johnson & Johnson (2009) እንደጠቀሱት በትብብር መማር የፈጠራ ሀሳብን ያጎለብታል ተማሪዎች በነፃነት በደስታ ሀሳባቸውን እንገልፁ ማድረግ አዲስ ለተፈጠረ ችግር በራሳቸው መፍትሄ እንዲሰጡ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቡድን ውስጥ አብረው በሚሰሩበት

ወቅት ከውድድር መንፈስ በመላቀቅ የራሳቸውን ሆነ የሌሎችን የቡድን ሀሳብ በማድነቅ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡

### 2.8.3. ስነ አእምሮአዊ ጥቅም

በትብብር መማር በተማሪዎች ዘንድ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሀሳባቸውን የመለዋወጥና በዚህ ላይም የተማረውን በራስ የመተማመን የማክበር ስሜቱን ይገነባዋል፡፡በትምህርትም ክፍለ ጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች ስለሚሰጡት መልስ ለማሰብ ጊዜ ሳይሰጣቸው በብዙ ተማሪዎች ጥያቄ እንዲመልሱ ስማቸው ይጠራል፡፡በትብብር መማሩ ደህንነቱ የጠበቀ ስለሆነ የተጠየቁትን ጥያቄ በሁሉም ፊት Johnson &Johnson (2009) መልስ ለመስጠት ይቀርባሉ፡፡

### 2.8.4. ማህበራዊ ጠቀሜታ

በትብብር መማር ዋነኛው ጥቅሙ ማህበራዊ ክህሎት ማስተሳሰሩ ነው፡፡ የወዳጅነትና የመቀራረብ መንፈስ በመፍጠር የቡድኑ አባላት አዲስ ማህበራዊ ክህሎት እንዲኖራቸው ያደርጋል Johnson & Johnson (2009) በትብብር መማር ጊዜ ተማሪዎች የተለዩ አመለካከቶችን እንዲቀበሉ የሌሎችን ሀሳብና ስሜት በጥልቀት እንዲረዱ ሌሎችንም ሁኔታዎችን ለማወቅ ፍላጎት ይኖራቸዋል Stahi (1994) ስለዚህ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ ይመጣ ዘንድ የማህበራዊ ክህሎት ትምህርት እንዲሰጥ እንደ ማንኛውም የትምህርት ዓይነት በተለየ ዘዴ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

### 2.8.5. መምህራን የሚያገኙት ጥቅም

በትብብር መማር ወቅት መምህራን እና ተማሪዎች ክህሎታቸውን ለመገምገም የቡድኑ አስተዋፅኦ ለመፈተሽ ሀላፊነት ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ተማሪዎች በቡድን ስራ ላይ እያሉየትምህርቱን የአካዳሚክ እና ማህበራዊ አቅጣጫዎችን በተመለከተ ቡድን እንዴት እንደሚሰሩ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን መረጃ መሰብሰብና መለዋወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ከቡድኑ ጋር መለዋወጥ የሚያካሄደው በትምህርት ክፍለ ጊዜና በኃላ ሊሆን ይችላል፡፡በተወሰነ የትምህርት ይዘት ላይ ተማሪው ስላለው ችሎታና ስሜት የማወቅ ፍላጎት ላላቸው መምህራን የቀጥታ ምርመራ ለማድረግ ጠቃሚ መሳሪያ ነው (Isaacs, 2008)

## 2.9. በትብብር መማር መሰረታዊ መርሆች

በትብብር መማር ዓላማው ከግብ ሊደርስ የሚችለው ተማሪዎችን በቡድን በማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን አምስቱን የትብብር መማር መርሆች የምንላቸው አዎንታዊ ግንኙነት (Positive Inter

dependence) ፣የቡድን አባል ተጠያቂነት (Indivdual Group accountability) ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ (Face to Face interaction) ማህበራዊ ክህሎት (Approprate use of Social skill) እና የቡድን ስራ ሂደት መገምገም (Group processing) ሥርዓት ባለው መንገድ በወጉ ሲተገበሩ ነው Johnson & johanson (1999) ፣Johnson & Johnson (2009) በዚህ ሀሳብ አለማየሁ (2009) Johnson& Johnson(1999) Gillies& Ashman (2003) ይስማማሉ፡፡መርሆችም እንደ ሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 2.9.1. አዎንታዊ ግንኙነት

የመጀመሪያና ዋናው የትብብር መማር መርህ ሲሆን ተማሪዎች በተቧደኑበት ቡድን በሚማሩበት ይዘት ላይ ያላቸው አመኔታ በጋራ በመሆን እርስ በርስ በመደጋገፍ በመረዳዳት፣ የድራሻቸውን በመወጣት፣ያላወቁትን ነገር በግላቸው ጥረት በማወቅ ያገኙትን እውቀትና ክህሎት ለሌሎች በማካፈል ጥሩ ውጤት የሚያመጡበት ነው መምህሩም ከክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ከየቡድኖቹ የሚሰጠውን ተግባር ላይ የአዎንታዊ ግንኙነት መርህ የሆነውን "አብሮ መስራት ወይም ማዳመጥን" የሚለው አመለካከት ተማሪዎች ከውስጣቸው አስርፀው እንዲሰሩ ማድረግ አለበት፡፡Johnson Johnson (1999) Johnson & Johnson (2009)ይህ ማለት እያንዳንዱ የቡድን አባላት ለሚማሩት ትምህርት የጋራ የሆነ ጥሩ ውጤት ማምጣት ወይም ደግሞ መውደቅ ነው፡፡የአንድ ተማሪ ማወቅ ወይም ውጤታማ መሆን ለሌሎች ቡድን አባላት እንደ ማወቅ ወይም ውጤታማ እንደመሆን ይቆጠራል፡፡ውድቀታችውም የጋራ ነው፡፡በቡድን የተዋቀሩ ተማሪዎች ሁለት ሀላፊነት አለባቸው፡፡የመጀመሪያው በዕለቱ የቀረበው የትምህርት ይዘት መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች የቡድን አባላት እነሱ የተረዱትን ያህል እንዲረዱ ማድረግ፡፡ይህ ሊሆን የሚችለው Gillis and Asheman (2003) እንደገለፁት በትብብር መማር ውስጥ ያሉት የቡድን አባላት ድርሻቸውን መወጣት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የቡድን አባላት መስራት እንዲችሉ በማድረግ ነው፡፡በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አስደሳች ይሆንላቸዋል፡፡ትምህርቱም ይገባቸዋል አቅማቸውን በማሳደግ ከሌሎች ተባብሮ የመስራት እር ስበርስ የመደጋገፍ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡

### 2.9.2. የቡድን አባል ተጠያቂነት

የቡድን አባላት ተጠያቂነት ማለት እያንዳንዱ የቡድን አባል ሌላው በሚሰራው ሥራ ላይ ሳይተማመን የየራሳቸውን ድርሻ በማከናወን፣ሌሎች የቡድን አባላት ድርሻቸውን እዲወጡ በማድረግ ሀላፊነታቸውን መወጣት የሚያመለክት ነው Jolifk(2007) ይህን አስመልክቶ አለማየሁ(2009)እንደ ተናገሩት እያንዳንዱ የቡድን አባላት አባልነታቸው ያለውን ሀላፊነት

አምነው የራሳቸውን የስራ ድርሻ በመወጣት ሌሎች አባላት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ አለባቸው።ለቡድኑ ውጤታማ መሆን ወይም መውደቅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተጠያቂ ናቸው፡ ፡ ሲገመገሙ የአጠቃላይ የቡድኑን ውጤት ለመስጠት በግል ይገመገማሉ።የቡድኑአባላት ትምህርታቸውን በተሳትፎ መሰረታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ አለበት።በቡድኑ ትክክለኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ተማሪዎች የስራ ሚና በጥቂቶች ላይ ተምኖ ሌሎች ነፃ የሚሆኑበት አጋጣሚ በማስቀረት ለቡድኑ ስራ ስኬት ሁሉም በተሳትፎ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ብለዋል። Slavian (1996) በበኩላቸው እንደገለፁት በትብብር መማር ወቅት የቡድንና የግለሰብ ሀላፊነት አፅኖት ሊሰጠው ይገባል የቡድኑ አባላት ለጋራ አላማቸው የጋራ ጥረት ማድረግ አለባቸው ። ለቡድኑ ውጤት የሚሰጠው እያንዳንዱ ተማሪ ስራ ከተገመገመ በኃላ ነው በመጨረሻም ተጨማሪ እርዳታ የሚፈልግ ካለ ሊያውቅ ይችላል ።በትብብር መማር ወቅት እያንዳንዱ የቡድን አባል መሳተፍን ለማወቅ መምህሩ ቀደም ብሎ የሰጣቸውን ተግባር መልሰው እንዲሰሩ በማድረግ በግል ይገመግማቸዋል።ተማሪዎችም የግል ክትትል እንዳለ ካወቁ የበለጠ ጥረት በማድረግ ስራዎችን እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል Johnson& Johnson(1999)እንደገለፁት የቡድኑና የአባል ተጠያቂነት የማወቂያ መንገድ አንዱ ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ያሉትን ሌሎች ተማሪዎች እንዲያግዙ በማድረግ ነው ብለዋል።

### 2.9.3. ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ

ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ ተማሪዎች በመቀራረብ እውነተኛን ሥራ አብረው በተነሳሽነት አንዱ የአንዱን የመማር ሁኔታ ከፍ በማድረግ በመረዳዳትና በመደጋገፍ እንዱሁም በመበረታታት እንዲማሩ የማድረግ ነው Johnson & Johnson (1999) በቡድን መካከል አዎንታዊ መደጋገፍ ካለ መወያየት ይኖራል።በውይይቱ ጊዜ ተቀራርቦ የጋራ ስራን ለማከናወን እያንዳንዱ የቡድን አባል የራሱን እውቀት ተሞክሮ ክህሎትን ስለሚያካፍል የርስበርስ የመደማመጥና የመቻቻል ተግባቦታቸው ይዳብራል።የተሻለ ውጤት ለማምጣት ሲሉ የተሰጣቸውን የቤትስራ (ተግባር) በጋራ ለመስራት በየጊዜው እየተገናኙመወያየት ስለ ሚጠበቀው በጋራ መስራት እንደ ግዴታ ወስደው ተነጋግረው ስራቸውን ያከናውናሉ።በየጊዜው በመገኘት በሰሩ ቁጥር በመካከላቸው ያለው መስተጋብር ይጠነክራል።

### 2.9.4. ማህበራዊ ክህሎታቸውን በአግባቡ መጠቀም መቻል

በትብብር መማር መሰረታዊ ነገር ሲሆን ተማሪዎች በትብብር መማር ክፍል ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ሰዓት ከሚማሩት ትምህርት እውቀት በተጨማሪ የራሳቸውን እና የቡድናቸውን ማህበራዊ ክሂሎት ሊያደብሩ ይችላሉ።ክህሎቶቻቸውን የሚያሳድጉት የቡድናቸውንና

የራሳቸውን የጋራ ዓላማ ለማሳካት እርስ በርሳቸው ተገናኝተው በመደጋገፍና በመረዳዳት በሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡ ከሌላ የቡድን አባላት ጋርም ሆነ ከራሳቸው ቡድን ጋር ያዳበሩትን እውቀት በሚሰጣቸውና ስራ ላይ እንዳስፈላጊነቱ የመጠቀም ልምዳቸው ያዳብርላቸዋል፡፡ ስራቸውን ተባብረው ያከናውኑ ዘንድ ከአባላቱ የሚጠበቀውን Gillis& Asheman(2003) እንደገለፁት እርስ በርስ መተዋወቅ መፈላለግ መደጋገፍና በግል ተግባብቶ መስራት ብቻ ሳይሆን ተወያይቶ ችግሮችን መፍታትም የሌሎች ሀሳብ መቀበል የራስን አስተያየት መስጠትና አለመግባባቶችን በጋራ መፍታት ይጠበቅባቸዋል Johnson& Johnson (2009)በማለት እንዳስቀመጡት በትብብር መማር በውድድር እና በግል ከመማር የበለጠ ውስብስብ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎችን በህብረት እንዲሰሩ የመሳብ ሀይል ስላለው ነው፡፡ቡድኑ ተማሪዎች አብረው በሚሰሩበት ወቅት አመራርነትን፣ ውሳኔ መስጠትን፣ የንግግር ክህሎትን ማወቅና ግጭቶች ሲፈጠሩ በምን መንገድ መፍታት እንዳለባቸው ማወቅን ይማሩበታል ፡፡ይህ ደግሞ ቡድኑ ለረጅም ጊዜ በስኬት አብሮ እንዲቆይ ያደርገዋል በማለት አብራርተዋል፡፡

### 2.9.5 ቡድናዊ ሂደት

በተወሰኑ ጊዜያት የቡድን አባላት የቡድኑን የመማር ሂደት ቆምብለው በመገምገም ጥንካሬና ድክመታቸውን መለየት፣ከድክመታቸው እየተማሩ ቀጣይ የቡድኑ መማር ሂደታቸውን ማሻሻል የሚችሉበት ነው፡፡ይህንን አስመልክተው አለማየሁ(2009፣40-41 እንደገለፁት የቡድን መማር ውጤት የተሳካ እንደሆነ የቡድኑ አባላት በቋሚነት ቡድናቸው እንዴት እንደሚማሩ ውጤትና መጠን በዝርዝር መመዘን አለበት፡፡እንዲሁም ዓላማው ለማሳካት ቀጥሎ ምን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ለይተው ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡በዚህ የግምገማ ሂደት ውስጥ አባላት ለመማሩ ያደረጉት አስተዋፅኦ ይገመገማል፤ገለፅም ይንፀባረቃል፡፡ይህ ደግሞ አባላቱ እንዴት ይሰሩ እንደነበር ለመረዳት ዕድል ይሰጣል፡፡በቡድን ተዋቅረው ሲሰሩ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በየጊዜው እያሻሻሉ እንዲሄዱ ማሻሻያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ለዚህም Johnson&Johnson(2009)የሰጧቸው መፍትሄዎች፡-በመካከላቸው መስተጋብር ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤በቡድን ስራቸው እየተሸሻሉ መምጣታቸውን ማረጋገጥ ውጤታቸው ይሻሻል ዘንድ ሁል ጊዜ ክትትል ማድረግና በክፍል ውስጥ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፤አንድ የቡድን ስራ ለማከናወን ሰዓት መወሰንና የወሰደውን ሰዓት ማወቅ፤ከስራ በኃላ እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት፤ የትብብር መማር ቡድን መምህራን ተማሪዎችን በልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ አቧድነው ከሚያስቀምጡ በተለየ መልኩ ትልቅ ትኩረት የሚሻ የማስተማሪያ

ዘዴ ነው፡፡ተማሪዎች በቡድን በቡድን አድርጎ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ከላይ መምህራን ለተማሪዎች ግልፅ በሆነ መንገድ በመናገር እንዲተገብሩት የተለያዩ ድርጊቶችን በማድረግ መከታተል አለባቸው፡፡ተማሪዎችም የቡድናቸውንና የራሳቸውን መማር ሁኔታ ከፍ ለማድረግ እርስ በርስ በመደጋገፍ ለሚሰጣቸው ተግባር እራሳቸውንና ሌሎችን የቡድን አባላት መሳተፋቸውን በማረጋገጥ ሀላፊነታቸውን መወጣት መምህራንም በትብብር መማር ወቅት ሁሉም ሳይሆን ከቀረ ግን የትብብር መማር መርህ በሚገባ ሁኔታ የተተገበረ አልተተገበረም፡፡

## 2.10. በትብብር መማር ሂደት የመምህራን ሚና

በትብብር መማር ሂደት የመምህራን ሚና ከልማዳዊ የቡድን ማስተማር (Traditional group Teaching) ከሚኖረው ሚና የተለየ ነው፡፡በትብብር መማር ወቅት የመምህራን ሚናቸው ብቸኛ የእውቀት ምንጭ በመሆን እውቀትን ለተማሪው ማስተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎቹ በራሳቸው ጥረት እውቀታቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታ መፍጠር ነው፤አለማየሁ (2009፣21) እንደሚገልፁት ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርቱን በግልፅ ከማቅረብ ባሻገር ተማሪዎች በበርካታ ተግባራት እንዲሳተፉ በመምህሩ ታቅዶ የሚተገበር ዘዴ ነው፡፡ተማሪዎች በውይይ፣በክርክር፣በመፃፍ፣ ችግሮችን በመፍታት ደረጃ ያለው የአስተሳሰብ ባለቤት እንዲሆኑ የሚደረግበት አቀራረብ ነው፡፡በትንሽ ቡድን በመደራጀት የየእለት ተሞክሮዎችን መመዘንና ማቅረብን ገለፃ ማድረግ፣ትምህርትን በድራማ መልክ ማቅረብ፣በጨዋታመልክ መማርን ያጠቃልላል፡፡ይህ የሚያመለክተው ተማሪ ተኮር አቀራረብ መምህሩ ብቸኛ የእውቀት ምንጭ ነኝ በሚል ሀሳብ በመላቀቅ ተማሪዎች በራሳቸው ጥርት በመምህሩ ታቅዶ በተዘጋጀው ትምህርት በመመርመር እንዲማሩ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡የመምህሩም ተግባር ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መማር እንዳለባቸው መንገድ መጠቆም ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡ከተማሪ ተኮር አቀራረብ አንዱ የሆነው ትብብራዊ መማርን የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች መምህሩ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ትምህርታቸውን እንዲማሩ ማድረግ ነው፡፡በሂደቱም ላይ ተማሪዎቹ ትርጉም ያለው ስራ እንዲሰሩ መምህሩ ተግባሩን በጥንቃቄ በመንደፍ እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ማስቀመጥ ለተማሪዎች መንገር አለበት፡፡ከዚህም በተጨማሪ በስራው ላይ ተግባር እንዲሳካ ለማመቻቸት እና የመማር ሁኔታን ለመቆጣጠር ከቡድን ቡድን እየተዘዋወረ ማየት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ለተማሪዎች የተለያዩ መልስ እየሰጠ የቡድኑን ተግባር ይፈትሻል (ይመዝናል) ይህ ደግሞ የቡድን አባላት ወደ ጋራ አላማቸው ለማምራት ትምህርታቸውን በንቃት እንዲማሩ ያደርጋቸዋል Ogunleye (2011)፡፡

## 2.11. በትብብር መማር ማስተማር ወቅት የተማሪዎች ሚና

በትምህርት አለም የሚገኙ አብዛኞቹ መምህራን ስለ ቡድን ስራ ያላቸው አመለካከት እየተቀየረ መጥቷል፡፡ተማሪዎችን ዝም ብለው የቡድን ስራ/ፕሮጀክት /እንዲሰሩ ከማድረግ ይልቅ መምህሩ እያንዳንዱን ተማሪ በራሱ ሚና እንዲወጣ ሚናዎችን ከፋፍሎ እስከ መስጠት ይደርሳል፡፡ የቡድኑ ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካት ሲሉ በህብረት ሆነው አብረው ይሰራሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የትምህርት ቃሉም በትብብር መማር እየተባለ ይጠራል፡፡አለማየሁ (2009፣89-90) በትብብር መማር ቡድን ውስጥ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ የቡድኑ አባላት ከሌሎች ሚናዎች በተጨማሪ የስራ ክፍፍል ማድረግ እና ድልድላቸውን አስቀምጠዋል፡፡የስራ ዝርዝሩም የቡድን መሪ፣ዘጋቢ፣ተመልካችና ተቆጣጣሪ ናቸው ብለዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የተሻለ የስራ ዝርዝር ካለ መጨመር እንደሚችል ገልፀዋል ሁሉም በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡የቡድን መሪ፡በቡድኑ ውጤታማነት ሃላፊነት አለበት፣የቡድኑአባላት ከተግባራቸው እንዳይዘናጉና ዘወር እንዳይሉ ያደርጋል፣ለመምህሩ ለቡድኑ አባለት እያወያየ ድራሻቸውን ያከፋፍላል፤የሚሰሩት ስራ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተጓዘ መሆኑን ይቆጣጠራል፤አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ተግባራት ለቡድኑ አባላት ይሰጣል፡፡ዘጋቢ፡የቡድኑን የእለት ተግባራት ማስታወሻ ይወስዳል፤የሰሩትን የስራ ውጤት ሌሎችን በማስተባበር ለመምህሩና ለክፍሉ ተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉበት መንገድ ያደራጃል፡፡ለዚህም ስራው የሚሆነውን ፋይል ሌሎች የቡድን አባላት የሚያቀርቡት ግብአት መሰረት ያዘጋጃል፡፡ተመልካች፡- በተመልካችነት የተመረጠው ደግሞ ሁሉም የቡድን አባላት በእኩልነት መሳተፋቸውን፣እኩል የመናገር እድል መኖሩን ጥቂቶች አስተዋፅኦ አድርገው የተቀሩት አድማጭ ብቻ እንዳይሆኑ ተሳትፎአቸው ከፍ እንዲል በአዎንታዊ መንገድ ያነቃቃል በቡድን አባላት መካከል የሚደረጉ ተግባቦቶች ከንትርክ የፀዳና አንዱ በሌላው ላይ የሚያቀርበው አስተያየት አዎንታዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ተቆጣጣሪ የቡድኑ አባልት ሁሉም በንቃት መሳተፋቸውን፣ለመማር መትጋታቸው የተማሩትን ትምህርት በሚገባ መረዳታቸውን ያረጋግጣል አለማየሁ (2009፣69) ከገለፁት በተጨሪ Johonson Et al (1991) በትብብር መማር ወቅት የተማሪዎች ኃላፊነት ብለው ያስቀመጡት እንደ ሚከተለው ናቸው፡፡ማጠቃለያ ሰጪ፡ከቡድኑ ስራ የተገኙት መፍትሄዎችን መደምደሚያ ወይም መልሶች በአጭር በአጭሩ ተፅፈው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ፡፡አብራሪ፡- ለውይይት የቀረቡ ፅንሰ ሀሳቦችን

ከቀደመ እውቀት ጋር ተዛምዶ እንዲቀርብ ያደርጋል በማለት ገልፀዋል፡፡ሌሎች የተማሪ ሚናዎች አለማየሁ (2009፣68-69) እንደ ሚከተለው ይዘረዝሩታል፡፡

- ተማሪዎች አዎንታዊ ግንኙነታቸው መደጋገፋቸውን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ የአንድ ሰው ወይም የቡድን ብቻ አድራገው እንዳይሆን መከላከል የሌሎችን አስተዋጽኦ ማበረታታት ተነሳሽነት እንዲኖርማድረግ  ይኖርባቸዋል፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ትምህርቱን በሚገባ የተረዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል
- ሁሉም ተማሪዎች አለመጣመዳቸውን መቆጣጠር ግዴታቸው መሆን አለበት፡፡ለቡድን አባላት በሚሰማ መጠን ብቻ መናገር ከቡድን አባላቱ የሚወጣ ድምፅ ሌሎች ቡድኖችን እንዳይረብሽ መጠንቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.12. ቀደምት ሥራዎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች በአንድ አምስት የቡድን አደረጃጀት ነት ምርካ በተመለከተ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተሰሩ ጥናቶች ናቸው፡፡ብርሀኔ (2005) የአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት ለመፃፍ ክሂል ማዳበር ያለው ሚና ሙከራዊ ጥናት በበአዲስ አበባ በቦሌ ክፍለ ከተማ በማርች 8 የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤትበ7ተኛ ክፍል ተተኳርነት "በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን አላማውም በአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀትና በተለምዶአዊ (በግል) ማስተማር ስልት ለመጻፍ ክሂል መዳበር የቱ ውጤታማ እንደሆነ ማሳየት ነው፡፡የጥናቱም ዘዴ መጠናዊ ምርምርን የተከተለ ሲሆን ተማሪዎቹ በሙከራዊ እና በቁጥጥር ቡድን በመለየት ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት መረጃው ተሰብስቦ በአሃዛዊ የመተንተን ስልት ተተንትኗል በአንድ ለአምስት የተማሩ ተማሪዎች በችሎታ ተሰባጥረው በመደራጀት የተማሩ ሲሆን በተለምዶአዊ ወይም በግል የተማሩት ደግሞ በግላቸው መጻፍን እየተማሩ ሁለቱም ለአንድ ወር እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ በጥናቱም የተገኘው ውጤት ለመጻፍ መሰረታዊ በሆነ ርዕሰ ጉዳዮች በተለምዶአዊ ጋር ሲነጻጸር የአንድ ለአምስት አደረጃጀት የተሸለ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በተለምዶአዊ አደረጃጀት ከተማሩት መካከል በቃላት ምርጫም አጠቃቀም በአንድ ለአምት ከተማሩት የተሸለ ውጤት እንዳላቸው ውጤቱ አመልክቷል፡፡አብይ (2015)"አንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት በአቻ የሚመራ (peer-led learning) ለመጻፍ ክሂል ማዳበር ያለው ሚና"በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል ጥናቱም የተካሄደው በባህር ዳርዩኒቨርሲቲ በእንግሊዘኛ

ትምህርት ክፍል ነው።ዓላማውም በአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት (በአቻ የሚመራ) ትምህርት ከግል ከመማር የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የቱ የተሸለ እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው። የጥናቱ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች በማቅረብ ቃለ መጠይቅ ለመምህራን በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል።ተማሪዎችም በግልና በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ተከፍለው እንዲማሩ ተደርጓል።በጥናቱም የተገኘው ውጤትም የሚያመለክተው የአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ከፍ ሊያደርግ እንደቻለ አረጋግጧል፡እነዚህ ጥናቶች በአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት ሀሳብ ማነሳታቸው ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ቢለያይም በተወሰነ መልኩ ደግሞ ይመሳሰላል ይህም ተማሪዎችን በቁጥጥር እና በሙከራዊ ቡድን ከፍሎ ሙከራዊ ቡድንን በአንድ ለአምስት በማደራጀት የቁጥጥር ቡድንን በግል (በተለምዶ) በማድረግ በሁለቱም ተመሳሳይ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ የሰዋሰው እውቀትና የመፃፍ ክሂል ችሎታ በተማሪዎች ዘንድ ለውጥ ማምጣቱን መገምገም የሚል ነው።በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል።

እነዚህ ጥናቶች በአንድ ለአምስት የቡድን አደረጃጀት ሀሳብ ማንሳታቸው ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ብለያይም በተወሰነ መልኩ ደግሞ ይመሳሰላል።ይህም ተማሪዎችን በቁጥጥርና በሙከረዊ ቡድን ከፍለው ሙከራዊ ቡድንን በአንድ ለአምስት በማደራጀት የቁጥጥር ቡድንን በግል በማድረግ በሁለቱም ተመሳሳይ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅመው የሰዋሰው እውቀትና የመጻፍ ክህል ችሎታ በተማሪዎች ዘንድ ለውጥ ማምጣቱን መገምገም የሚል ነው።በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል።ይህ ጥናት የሚያተኩረው ግምገማ ላይ ሳይሆን በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና በአስረኛ ክፍል ተተኳርነት በጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የጥናቱ ንድፍ፣ የመረጃ ምንጮች አመራረጥ የናሙና ዘዴ አመራረጥ፣መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነት እና ሂደቱ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

በርካታ የምርምር አይነቶች ቢኖሩም ይህ ጥናት የተከተለው ሙከራዊ የምርምር ስልትን ነው፡፡ ከመረጃ መተንተኛ አንጻር መጠናዊ ምርምርን ተከትሏል፡፡መጠናዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ያለው(2009) መጠናዊ ምርምር መጠንን ገላጭ፣የመረጃዎቹ አይነት በቁጥር የሚገለፁ፣መረጃዎቹ የሚተነተኑት በስታቲስቲካዊ ዘዴ እንደሆነና በአብዛኛው መላምትን ተመርኩዞ የሚካሄድ የምርምር አይነት ነው በማለት አስቀምጠዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ተመራማሪዋ በመረጠችው ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ ያነሳችውን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት የሚያደርግ የምርምር አይነት ነው በማለት ገልፀውታል፡፡

ከላይ ከቀረበዉ ሃሳብ በመነሳት መጠናዊ ምርምር መረጃዎችን በስታቲስቲካዊ ዘዴ የሚያቀርብና መላምትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ለዚህ ጥናት አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ለጥናቱ ተመርጧል፡፡የዚህ ጥናት ውጤትም መጠናዊ በሆነ መንገድ በቲ-ቴስት በማነፃፀር በገላጭ ስታቲስቲክስ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ይህ ጥናትም ሁለት ተጠኚ ቡድኖችን የያዘና የሁለቱ ቡድኖች ቅድመና ድህረ (ልምምድ) ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅን ተግባራዊ ያደረገ ነው፡፡

### 3.2 የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጮች በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ዳሞት ጋሌ ወረዳ ውስጥ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጋቼኖ ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓመተ ምህረት በአስረኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች እና የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡፡

### 3.3 የናሙና አመራረጥ

#### 3.3.1. ትምህርት ቤት አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በወላይታ ዞን ዳሞት ጋሌ ወረዳ ውስጥ ካሉት ከአምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለጥናቱ የተመረጠው ጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡በዚህ ትምህርት ቤት እንደ ሌሎችም ትምህርት ቤቶች ሁሉ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለወላተኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች ይሰጣል፡፡ትምህርት ቤቱ የተመረጠው በአመቺ ንሞና ስልት አጥኚዋ ተጠቅማ ነው፡፡ያለው(2006) እንደሚያስረዱት አንድ ተመራማሪ ጥናቱ በቅርብ ባገኘው ለማካሄድ አመቺ የሆኑለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ማድረግ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ከዚህም በመነሳት ከላይ የተጠቀሰው ትምህርት ቤት ለጥናቱ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ አስቀድማ ያለችበትና አሁንም እየሠራች ያለችበት ትምህርት ቤት በመሆኑ መረጃዎችን በተሳካ መንገድ ለመሰብሰብ አመቺነቱ የላቀ መሆኑን በማመን ነው፡፡

### 3.3.2 .የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያት ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በትብብር መማር የመጻፍ ችሎታን እንዲያደብሩ ለማሳየት አጥኚዋ አስረኛ ክፍል ስለምታስተምር ትክክለኛ መረጃ በቅርበት ለማግኘትና ለመሰብሰብ ታስበው በአመቺ ንሞና አመራረጥ ተመርጧል፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ

ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት ከዘጣነኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሲሆን ጥናቱ ያተኮረው አስረኛ ክፍል በትብብር መማር የመጻፍ ችሎታ ያለውን ሚና መፈተሽ ላይ ነው፡፡በጥናቱ የተካተቱት በ2015 ዓ.ም በአስረኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡በዚህ መሰረት በጋቼኖ ሁከተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 416 ሲሆኑ ከእነዚህ ለጥናቱ ናሙናነት በYemane(1977)ፎሩሙላ ተጠቅሜ የመረጥኳቸው ተማሪዎች ብዛት 203 ናቸው፡፡

n= ከጠቅላላ የተመረጠ ናሙና

N=ጠቅላላ ያለው ብዛት

e=ስህተት(0.05)

$$n=\frac{N}{(1+N(e)2)}$$

በዚሁ መሰረት 203 ተማሪዎችን በጥናቱ ለማሳተፍ ታስቦ ነበር፡፡ከነኚህም መካከል 156 ተማሪዎች በወላይተኛ አፍ-ፈት ናቸው፡፡የቀሩት 47 ተማሪዎች አማርኛ አፍ-ፈት ናቸው፡፡ አማርኛ አፍ-ፈት የሆኑት የ47ቱ ተማሪዎች የፈተና ውጤት ከጥናቱ ውጭ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት 156 ተማሪዎችን በጥናቱ ለማሳተፍ ታስቦ ነበር፡፡ሆኖም ከ156 ወላይተኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች መካከል 8 ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተናውን ባለመፈተናቸው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው ከጥናት ውጭ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በቁጥጥር ቡድኑ 74 እንደዚሁም በሙከራ ቡድኑ 74 በአጠቃላይ የ148 ተማሪዎች የፈተና ውጤት የጥናቱ ናሙና ሆኗል፡፡

ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና የጥናቱን አስተማማኝነትና ተገቢነት ለመጠበቅ የተማሪዎችን ቁጥር መወሰን የግድ ነው፡፡በዚህም ምክንያት ሁሉንም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ተሳታፊ ማድረግ አልተቻለም፡፡የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ተጠኚ ለማድረግ በመጀመሪያ ሁሉንም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የችሎታ ስብጥር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ስብጥሩም ከተረጋገጠ በኋላ የመማሪያ ክፍሎችን ዕጣ ውስጥ

በማስገባት በቀላል ዕድል ሠጪ ናሙና ዘዴ መሰረት በትምህርት ቤቱ ውስጥ አስረኛ ክፍል ከሚገኙ ስምንት ምድቦች ውስጥ ተመርጠዋል፡፡በሁለቱ ቡድን በሙከራ ቡድንና ቁጥጥር ቡድን/experimental and control group/በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የትኛው ምድብ ሙከራዊ ወይም የትኛው ደግሞ የቁጥጥር ምድብ ይሁን? የሚለውን ለመወሰን ሁለቱን ምድቦች የመጻፍ ችሎታ ቅድመ ትምህርት ፈተና ከወሰዱ በኋላ በቀላል እጣ ናሙና ዘዴ አማካኝነት 10ኛ(E-H) የቁጥጥር ቡድን 10ኛ( A-D ) የሙከራ ቡድን እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት ለአምስት ሳምንት በሳምንት ሁለት ቀን በየቀኑ ለአንድ ሠዓት ከ23/03/2015 እስከ 30/04/ 2015 ዓ.ም በትብብር መማር ማስተማር ዘዴና በግል መማር ዘዴ ሁለቱም ቡድኖች ማለትም የቁጥጥር ቡድኑና ሙከራዊ ጥናት ቡድኑ በሌላ መምህር ማስተማር እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም የጥናቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ቁጥጥር የሚደረግባቸውና ሙከራዊ ጥናት የሚደረግባቸው ሁለቱም ቡድኖች የተማሩት መፅሀፍ ተመሳሳይ የፅህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን የያዘ ነው፡፡በተጨማሪም ለሚያስተምረው መምህር የስልጠና ማንዋል ተዘጋጅቶ ስለ ትብብራዊ መማር ማስተማር ሚና አተገበባር በአጥኚዋ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

#### 3.3.4. የመምህራን አመራረጥ

ለናሙና ከተመረጠው ጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አስረኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአጠቃላይ ሶስት ሲሆኑ ከሶስት መምህራን ናሙና መርጦ መውሰድ ስነ-ዘዴ (Yemane (1977) sampling Technique) ፎርሙላ በመጠቀም በጥናቱ እንዲሳተፉ ሶስትንም መምህራን መርጬ ወስጄዋለሁ፡፡ምክንቱም በየማነ ፎርሙላ ናሙና ስሰራ ብዛቱ ባነሰ ቁጥሩ ያው ራሱን ያመጣል፡፡በዚህ መሰረት በትምህርት ቤት ያሉ ሶስትንም መምህራን ለጥናቱ ተጠቅመዋለው፡፡

### 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ አገልግሎት ከተማሪዎች እና ከመምህራን የሚገኙትን መረጃዎች ለመሰብሰብ ነው፡፡አጥኚዋ ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅማለች፡፡

#### 3.4.1. ፈተና

መረጃ ለመሰብሰብ ከሚያግዙ በርካታ ዘዴዎች መካከል ፈተናዎች ጉልህ ስፍራ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ፈተናዎች በተለያዩ መልኮች ተዘጋጅተው በጥንቃቄ ተቀናጅተው አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላሉ፡፡በዚህም ጥናት ፈተና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ዓላማውም የጥናቱን ተሳታፊዎች የመፃፍ ችሎታ በዚህም መሰረት የቅድመ ትምህርት ፈተናና የድህረ ትምህርት ፈተና ተዘጋጂተዋል፡፡

##### *3.4.1.1. ቅድመት ትምህርት ፈተና*

በዚህ ጥናት የቅድመ ትምህርት ፈተና የሚሰጠው በሙከራዊ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድን መካከል ያለውን የውጤት ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡ ፡በዚህም መሠረት የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ አምስት መመሪያዎችን የያዘ ፈተና

ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡፡ከመመሪያ አንድ እስከ ሶስት አንቀጽን በተመለከተ 60% ይዟል፣መመሪያ አራት ደብዳቤን በሚመለከት 20% ይዟል፣መመሪያ አምስት አሳጥሮ መጻፍን በተመለከተ 20% ይዟል፡፡ፈተናውም የታረመው ከ100% ነው፡፡

#### *3.4.1.2. ድህረ ትምህርት ፈተና*

የጥናቱ ተሳታፊዎች የጽህፈት ክሂልን በተመለከተ የተዘጋጀውን የማስተማሪያ ፅሁፍ ለአምስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን በየቀኑ ለአንድ ሰዓት ከተማሩ በኃላ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር በተመሳሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ በሶስት መምህራን ተሰጥቷል፡፡ድህረ ትምህርት ፈተና የተሰጠበት ዋነኛ አላማ የሙከራ ቡድን በትብብራዊ መማር ማስተማር አማካኝነት ከተማሩ በኂላ ዘዴው በሙከራው ቡድን ውስጥ በተካተቱ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ መሻሻል መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የፈተናውን External validity (ውጫዊ ተገቢነትን ለመቆጣጣር እንዲያስችለን የሚሳተፉት አባላት የተለያ የችሎታ ስብጥር ያላቸው መሆኑ በናሙና አመራረጥ ወቅት ትኩረት ተሰጥቷል፡፡እንዲሁም የድህረ ትምህርት ፈተናው ባህሪና መቼ እንደሚፈተኑ ተማሪዎች እንዲያውቁ ተደርጓል፡፡ከዚህ ጐን ለጐን ጥናት እንደሚደረግባቸው ሁለቱ ቡድኖች እንዲያውቁ የሚደረግበት ስልት ተቀይሷል፡፡እንዲሁም Test validity (የፈተናዎች አስተማማኝነት) ለመቆጣጣር ከአጥኚዋ በተመረጡ መምህራን እንዲፈትኑ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹም ከዚህ በፊት ያልተፈተኑት መሆናቸው ተረጋግጦ ተሰጥቷል፡፡

### 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት ፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ የጥናቱ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው የማጣራት ሥራ ከተከናወነ በኂላ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመለካትና ስለ ትብብራዊ መማር ዘዴ ያላቸውን ችሎታ ለመፈተሽ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶችን በማነፃፀር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (t-test) ቀመር አማካኝነት መረጃዎችንም በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተሰልተው ቀርበዋል፡፡የቅድመ ትምህርት ፈተና የተሰጠው ተማሪዎች ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን እውቀት ለመፈተሽ ነው፡፡በአንጻሩም ድህረ ትምህርት ፈተና የተሰጠበት ምክንያት ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኂላ ያመጡትን ለውጥ ለመፈተሽ ነው፡ ፡ቅድመ ትምህርት ፈተና ከተሰጠ በኂላ ለተከታታይ ለአምስት ሳምታት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ለትምህርቱ የተመደው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኂላ ተማሪዎች በቀረበው ትምህርት ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለመለካት ድህረ ትምህረት ፈተና እንዲሰጥ ተደረጓል፡፡እንዲሁም አጥኚዋ ተማሪዎች ስለ ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ለማሻል ያለው ሚና ለመፈተሽ የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ አድርጋለች፡፡

## 3.6 የሙከራ ጥናቱ አተገባበር ሂደት

ይህ ሙከራዊ ጥናት የተከተለው የምርምር ስልት ሙከራዊ የምርምር ስልት ሲሆን ከመረጃ መተንተኛ አንፃር ደግሞ መጠናዊ ምርምር ተከትሏል፡፡በመሆኑም ሙከራዊ ጥናቱ የተከተላቸው የአተገባበር ሂደቶች እንደ ሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.6.1 የተሰጠው ስልጠና

አጥኚዋ በተመረጠዉ በጋቼና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመገኘት ሙከራዊ ጥናት ከማድረጓ በፊት ሙከራ ቡድን የሚያስተምር መምህራን ስለሚያስፈልጋቸው አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ጉዳዩን አስረድታ ይሁንታ አገኘች፡፡በትብብራዊ መማር እንዲሁ ዝም ብሎ መተግበር ስለማይቻል መምህራን ትብብራዊ መማር ማስተማርን እንዲጠቀሙ ስለ ምንነቱና አተገባብሩ በቂ ስልጠና መውሠድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ (በOunnan1992፣Johonson&Johnaso (1999) በመሆኑም ትብብራዊ መማርና አተገባበሩን በተመለከተ ስድስት ሰዓታትን የፈጀ ስልጠና ለሁለት መምህራን ተሠጥቷል፡፡የማሰልጠኛ ማንዋሉ የተዘጋጀው አጥኚዋ ትብብራዊ መማርን አስመልክታ ተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ ውስጥ ከዘረዘረቻቸው ይዘቶች በመነሳትና ርዕስ ጉዳዩን አስመልክቶ Johnson & Johnson (1990) ሌሎች የመስኩ ምሁራን የጻፏቸውን መርሆችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የስልጠናው ማንዋል ስድስት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን በማንዋሉ ውስጥ የተካተቱት የስልጠናው ዋና ዋና ይዘቶች የትብብራዊ መማር ምንነት፣የትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች፣ትብብራዊ መማር ስልቶች፣በትብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና፣ ትብብራዊ መማርና ማስተማር በተለምዶ (ቡድን) መማር መካከል ያለው ልዩነት የሚሉ ሀሳቦችና የተማሪዎች የግልና የቡድን ፅብረቃ ማድረጊያ ቅፆች ወዘተ ተካተውበታል፡፡ የስልጠናው ማንዋል የተዘጋጀው በአጥኚዋ ነው፡፡

ለስልጠናው የተመደበ ጊዜ ስድስት ሰዓታት ቢሆንም ስልጠናው የወሰደው ጊዜ ሁለት ሰምንት ነው፡፡መምህርቷ ስልጠናውን የሚሰጡት በትርፍ ጊዜያቸው በመሆኑ ከማስተማሪያ ሠዓት ውጭ የሆነ ሰዓት ስለ ሚያስፈልጋት ነው፡፡መምህራኖቹ ስልጠናውን ከመጀመራቸው በፊት በማሠልጠኛ ማንዋል ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ማንዋሉን ቀድሞ መስጠት ያስፈለገው መምህራኖች ቀድመው ተዘጋጅተው እንደመጡና የተለያዩ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ በማሰብ ነው፡፡

### 3.6.2 የቡድን አደረጃጀት

ለመምህራኖች ስልጠና ከተሠጠቸው በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የተማሪዎችን ደረጃ ለማወቅ ለሙከራ ለሚሳተፉት ተማሪዎች የፅህፈት ክሂል ቅድመ ትምህርት ፈተና መስጠት ነው፡፡ ከዚያም ቅድመ ትምህርት ፈተናው ከታረመ በኋላ ምድቦች የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተብለው በዕጣ ከተለዩ በኋላ በሙከራ ቡድን የተካተቱት ተማሪ በውጤታቸው መሠረት በቡድን በቡድን እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ቡድን አስር አስር አባላት እንዲይዝ በማድረግ ስብጥራዊ በሆነ መንገድ እንዲዋቀር ተደረገዋል፡፡የቡድን አባላቱ አስር

እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት  አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ቡድኑን በሁለት አባላት ለማጣመር ይረዳል፡፡

### 3.6.3. ሚና መከፋፈልና የስራ ድርሻን መግለፅ

ዓለማየሁ (2009) በትብብራዊ መማር ቡድን ውስጥ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ የቡድን አባላት ከሌሎች ሚናዎች በተጨማሪ የስራ ክፍፍል ማድረግ እንዳለባቸው አስቀምጠዋል፡፤ በዚህም መሠረት ሚና ማከፋፈል አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም በውስጡ አስር አስር አባላትን የያዘ ቡድን ከተዋቀረ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ ሚና እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡በትብብረዊ መማር ለእያንዳንዱ ቡድን አባል የተለያዩ ሚናዎችን ማከፋፈል ትብብራዊ መማርን በቡድን ከመማር እንዲለይ ከሚያደርጉት ባህሪያት አንዱ ነው፡፡በትብብራዊ ቡድን ውስጥ ያሉ አባላት የተዋቀሩት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲቀያየሩ ተደርገው ነው፡፡ምክንያቱም በትብብር ተግባር ወቅት እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ የተለያዩ ሀላፊነቶች እንዲጋሩ ለማድረግ ነው፡፡በመሆኑም ሚናዎቹን በመቀያየር ተማሪዎች በመካከላቸው የሚና ተደጋጋፊነት እንዲኖር ያስችላል፡፡ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሚና ማከፋፈል የተሠጣቸው ኃላፊነት ምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ ያስችላል፡፡ ሚናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

የቡድን መሪ፡-በቡድኑ ውጤታማነት ሀላፊነት አለበት፡፡የቡድን አባላትን ከተግባራቸው እንዳይዘናጉ ያደርጋል፡፡ለመምህሩ ለቡድን አባላት እያወያየ ድርሻቸውን ያከፋፍላል፡፡በሚሠሩት ስራ በትክክልለኛ አቅጣጫ እየተጓዘ መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ተግባራት ለቡድኑ አባላት ይሠጣል፡፡

ዘጋቢ፦የቡድን የዕለት ተግባራት ማስታወሻ ይወስዳል፣ የሠሩትን የስራ ውጤት ሌሎችን በማስተባበር ለመምህሩና ለክፍል ተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉበት መንገድ ያደራጃል፡፡በዚህም ለስራው የሚሆነው ፋይል ሌሎች የቡድን አባላት የሚያቀርቡት ግባዓት ያዘጋጃል፡፡

ተመልካች፦በተመልካችነት የተመረጠው ደግሞ ሁሉም የቡድን አባላት በእኩልነት መሳተፋቸውን፣ እኩል  የመናገር እድል መኖሩን ጥቂቶች አሰታዋፅኦ አድርገው የተቀሩት አድማጭ ብቻ እንዳይሆኑ  ተሳትፎአቸው ከፍ እንዲል በአዎንታዊ መንገድ ያነቃቃል፣ በቡድን አባላት መካከል የሚደረጉ      ተግባቦቶች ከንትርክ የፀዳና አንዱ በሌለው ላይ የሚያቀርበውን አስተያየት አዎንታዊ መሆኑን  ያረጋግጣል፡፡ተቆጣጣሪ፦የቡድን አባላት ሁሉም በንቃት መሳተፋቸውን፣ለመማር መትጋታቸውን የተማሩትን ትምህርት በሚገባ መረዳታቸውን ያረጋግጣል፡፡አለማየሁ (2009፣89) ከገለፁት በተጨማሪ (Johnson eta(1991)) በትብብ መማር ወቅት የተማሪዎች ሀላፊነት ብለው ያስቀመጡት እንደሚከተለው  ናቸው፡፡ማጠቃለያ ሰጪ፦ከቡድኑ ስራ የተገኙት መፍትሄ፣ደምደሚያ ወይም መልሶችን በአጭር በአጭር ተፅፈው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡አብራሪ፦ለውይይቱ የቀረቡ ፅንሠ ሀሳቦችን ከቀደመ ዕውቀት ጋር ተዛምዶ እንዲቀርብ ያደርጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

### 3.6.4 የክፍል ውስጥ አተገባበር

ቡድኖች ከተዋቀሩ በኋላ ዋናው ተግባር መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፅህፈት ክሂል መልመጃዎች መሠረት አተገባበሩን መጀመር ነው፡፡በዚህም መሠረት ለዚህ ጥናት ሥራ ላይ

የዋለውን የማስተማር ይዘት ለማዘጋጀት ቅድሚያ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ተግባራት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ይህንንም ተግባር ማከናወን ለክፍል ደረጃው ለአስረኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ተመጣጣኝ ተግባራትን ለማዘጋጀት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ የቁጥጥር ቡድኑንም ሆነ የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር ከመማሪያ መፅሀፍ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ አጋዥ መፅሀፍትን የአዲሡን ስርዓት ትምህርት መሠረት አድርጋ አዘጋጅታለች፡፡

መምህርቷ እነዚህን የፅህፈት ተግባራት በሙከራ ቡድን ውስጥ ለተካተቱ ተማሪዎች በምታስተምርበት ጊዜ እንዲትተገብር የተደረገው አስቀድሞ በተመራማሪዋ በተዘጋጀላት የትብብራዊ መማር የትምህርት ዕቅድ አማካኝነት ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የፅህፈት ትምህርት በትብብራዊ መማር ዘዴ እንዲቀርብ የተደረገው ራሡን የቻለ የትብብራዊ መማር የትምህርት ዕቅድ ተዘጋጅቶለት ነው፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት በመተባበር መማር ስኬታማ የሚሆነው ሁለት እጅግ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡እነሱም ተማሪዎች በንቃትና በሙሉ ተሳትፎ ለመማር ዝግጁ ሲሆኑና መምህሩ የትምህርት ዕቅዱን ከዚሁ አንፃር ሲቃኝ ሲያቅድና ተማሪዎችን ላቀደው ትምህርት በተገቢው ለመማር ሲያዘጋጃቸው ነው፡፡በመተባበር መማር በዚሁ መንገድ ከታቀደና ከተተገበረ በተማሪዎች ላይ የውጤት መሻሻል ሊታይ ይችላል፡፡ ተማሪዎች ሌሎችን የመረዳት ክህሎታቸው ይጨምራል አለማየሁ(2009)፡፡

የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት በመምህር ተኮርና በመተባበር መማር የትምህርት አቀራረብ አንድ አይነት አይደለም፡፡በትብብራዊ መማር አቀራረብ ውስጥም ቢሆን አንድ ዓይነት የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ሊኖር አይችልም፡፡እንደ መምህሩ የማስተማር ፍልስፍና እና ዓላማ ሊለያይ ይችላል፡፡የትብብራዊ መማር የትምህርት ዕቅድን በተመለከተ አለማየሁ (2009) ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚዋ የትምህርት ዕቅዱን ያዘጋጀችው ዓለማየሁ (2009፣ 104) መሠረት በማድረግ ነው ዕቅዱም የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆችን የተከተለ ሲሆን ትምህርታዊ ዓላማዎችን፣ትብብራዊ ዓላማዎችን፣በትብብር መማር ጊዜ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያትን፣ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ሚናዎችን፣ ግለሠባዊ ተጠያቂነትና አዎንታዊ ተደጋጋፊነትን፣እንዲሁም የስኬት መስፈርቶችን አካቶ የያዘና የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በትብብራዊ ቡድናቸው አማካኝነት ሚናዎችን ተከፋፍለው እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው፡፡በዚህም መሠረት ሙከራዊ ቡድኑ በትብብራዊ መማር አማካይነት በተዘጋጀው የትምህርት ዕቅድ ሲማሩ በቅጥጥር ቡድን  የሚማሩት ደግሞ መምህር ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ በዘጋጀችው የትምህርት ዕቅድ የሚማሩ ናቸው፡፡

### 3.6.5 የግልና የቡድን ፅብረቃ

በትብብራዊ ተግባር መጨረሻ ላይ በሙከራ ቡድን የተሳተፉት ተማሪዎች የመገምገሚያ ነጥቦችን የያዘና እያንዳንዱ ተማሪ በቡድን ሥራው ወቅት የነበረውን ግላዊ ተሳትፎ እንዲያንፀበርቁ የሚያስችል ትብብራዊ መማር በሚተገበርበት ጊዜ ተማሪዎች ከትግበራው በኋላ ስለስራቸው ሁኔታ እንዲያንፀባርቁ ማድረግ የትብብራዊ መማር አንድ አካል ነው Nunan (1997)፡፡ ይህ የመገምገሚያ ቅፅ እያንዳንዱ ተማሪ በትብብራዊ መማር ጊዜ የነበረውን ጠናካራና ደካማ ጎን እዲገነዘብ እንዲያንፀባርቁ እና ለሚቀጥለው የትብብራዊ መማር ተግባር ራሡን አርሞና ለስራው ዝግጁ አድርጎ እንዲቆይ ያስችላል፡፡

በሙከራ ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች በትብብራዊ ቡድን ውስጥ የነበራቸው ግላዊ ተሳትፎ ከመገምገም በተጨማሪ የቡድኑን አጠቃላይ ጠንካራና ደካማ ጎን እንደ አንድ ቡድን ሆኖ መገምገምና ማንፀባረቅም ሌላው መከወን ያለበትተግባር ነው፡፡በመሆኑም የቡድኑ አባላት በአንድ ላይ ሆነው ትክክለኛነት እና አስተማማኝነት በአንድ የጥናት ሥነ-ዘዴ ውስጥ ሰፊ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሰረተዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡እራሳቸውን እንዲገመግሙና እንዲያንፀባርቁ የሚያስችል አምስት ነጥቦችን የያዘ የቡድኑ ጠንካራና ደካማ ጎን መገምገሚያ ቅፅ ከእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ማለቂያ ላይ ለእያንዳንዱ ቡድን እንዲታደል ተደርጓል፡፡

## 3.7 የቅድመ እና ድህረ ፈተና አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት

አስተማማኝነት ማለት አንድ ባህሪ ወይም ነገር በአንድ መለኪያ በመጠቀም በተደጋጋሚ በመለካት የሚገኝ የውጤት ወይም የልኬት ተመሳሳይነት፣ቋሚነት፣ወጥነትን ወይም አይለወጤነትን የሚያመለክት ሲሆን ትክክለኛነት ዳግሞ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ በተቃና፣በተሟላና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዳስቻለ የሚያመለክት ነው ያለው(2009፣202፣231)፡፡ Heaton (1990 159) እንደ ሚገልጹት ትክክለኛነት ማለት አንድ ፈተና የታሰበውን ዓላማ በሚፈለገው መልኩ ሊለካ የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥበት ነው፡፡

## 3.8 የጽሁፍ መጠይቅ አተናተን ዘዴ

በጥናቱ የሙከራ ቡድን ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም እያንዳንዱ መላሽ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች አንጻር ሁሉም መላሾች የሰጡት ምላሽ ተደመረ፡፡በመጨረሻም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ለቀረቡት አማራጭ መልሶች የሁሉም መላሾች መልስ እየተደመረ በመቶኛ እየተሰላ ተለየ፡፡በዚህ መልክ የተገኘውን ውጤት የበለጠ ለማጠናከር በቀጣይም ጥያቄዎቹ ከያዟቸው አራት ይዘቶች አንጻር በspss እትም 20 መሰረት የጋራ አማካይ(mean)ገላጭ ዉጤታቸው በpeat(2001)መሰረት በባለ አምስት እስከል የውጤት መግለጫ ቀመር የተገኘው ውጤት ከ2.5 በታች ከሆነ ዝቅተኛ፣ከ2.5-3.5 ከሆነ መካከለኛና ከ3.5 በላይ ከሆነ ከፍተኛ በማለት ተተንትኗል፡፡በዚሁ መሰረት በመቶኛ(%) በተናጠል የተተነተኑት ጥያቄዎች በማጠቃለያነት እንደገና እንደ ይዘታቸው በተገለጸው ስሌት ታይቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1.የውጤት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ መረጃዎች በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ ተሰብሰበዋል፡፡ መረጃዎችም ከተቀመጡበት ዓላማዎች አንጻር ለመተንተን ጥረት ተደረጓል፡፡ ዓላማዎችም የሚያተኩሩት የመጻፍ ችሎታን በተመለከተ በትብብራዊ መማር ዘዴና በግል መማር ዘዴ መካከል የታየው የተማሪዎች ውጤት ምን እንደሚመስል መመርመርና እንዲሁም በትብብራዊ መማር ዘዴ ተማሪዎች ምን አስተያየት እንዳላችው ማየት የሚሉ የጥናቱን ዓላማዎችን መሰረት ያደረጉ ከፈተናና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

በዚህም መሠረት ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ለመመርመር በቅድሚያ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና ያላቸውን የመጻፍ ችሎታ እና ያመጡት ፈተና ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዠ 1 ቀርቧል፡፡

#### 4.1.1. የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና ትንተና

ሠንጠረዥ 4.1 ፡-ከነፃ ናሙና አንፃር በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ያለ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት፣

| ቡድን | ናሙና (በ) | አማካይ ውጤት (m) | መደበኛ ልዩነት (SD) | መደበኛ ልዩነት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ(በባለሁለ ትጫፍ)sig(2tailled) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | 74 | 51.70 | 14.62 | 0.67081 | 0.25 | 146 | 0.80 |
| ሙከራ | 74 | 50.88 | 14.36 | 0.69985 | | | |

በሠንጠረዥ 4.1.የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያላቸውን አማካይ ውጤት ያሳያል፡፡በሠንጠረዡ ላይ ከሰፈረው ከገላጭ ስታቲስክስ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥሩ ቡድን የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት 51.70 ሲሆን የሙከራ ቡድን የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ 50.88 ነው፡፡ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከትምህርት በፊት የመጻፍ ችሎታቸው ተቀራራቢ ደረጃ ላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡እንዲሁም ከቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድን መደበኛ ልዩነት 14.62 ሲሆን የሙከራ ቡድን መደበኛ ልዩነት ደግሞ 14.36 ነው፡፡በመሆኑም አማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ልዩነታቸውን በስታቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለት አማካይ ውጤታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ ውጤቱ በ146 የነፃነት ደረጃ የቲ= -0.25 የpዋጋ=.0.80 ሆኗል፡፡ይህ በመጻፍ ችሎታ ረገድ በሁለት ቡድኖች አማካዮች መካከል ስታስቲክስ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ምክንያቱም የp ዋጋ 0.80 ነው፡፡በዚህም መሠረት በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታቸው የጎላ ልዩነት 0.05 መጠን የጉልህነት ደረጃ አለመኖሩን ከታወቀ በኋላ የሙከራዊ ቡድን በትብብራዊ መማር ዘዴ የቁጥጥር ቡድን ደግሞ በግል የመማር ዘዴ ሲማሩ ቆይተው ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል፡፡

### 4.1.2. የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና ትንተና

ሠንጠረዥ 4.2፦ ከነፃ ናሙና አንፃር በቁጥጥር ቡድንና በሙከራ ቡድን መካከል ያለ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት፣

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ውጤት(m) | መደበኛ ልዩነት(S.D) | መደበኛ የስህተት መጠን | የቲ-ዋጋ (ቲ) | የነፃነት ደረጃ(DF) | የጉልህነት ደረጃ(በባለሁለት ጫፍ sig(2tailled) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | 74 | 51.216 | 13.78 | 0.67120 | -6.238 | 146 | 0.002 |
| ሙከራዊ | 74 | 57.30 | 11.69 | 0.70743 | | | |

በሠንጠረዥ 4.2 እንደቀረበው በድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የሙከራዊ ቡድን አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድን አማካይ ውጤት በ6.084 በልጦ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ሙከራዊ ቡድን ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 57.30 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ያስመዘገበው ደግሞ 51.216 ነው፡፡ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው የሙከራ ቡድን በድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱን ነው፡፡ይህ ደግሞ በሁለቱም ቡድኖች መካከል በመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት መደበኛ ልዩነት በሚታይበት ጊዜ የቁጥጥር ቡድን 13.78 ሲሆን ሙከራዊ ቡድን ደግሞ 11.69 ነው፡፡አማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስለላው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል ልዩነታቸውን በስታቲስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱም አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት አማካኝነት ተሰልቶ ውጤቱ (ቲ = -6.238 ,p=0.002) ሆኗል፡፡ይህም በቡድኖቹ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ መካከል በስታቲስቲክስ የጎላ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡ምክንያቱም የተገኘው የpዋጋ 0.002 ሲሆን ይህም ከ0.05 አንሶ መገኘቱ ነው፡፡በመሆኑም ይህ ውጤት የሚያሳየው የሙከራ

ቡድኑ የመጻፍ ችሎታ ውጤት የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህም የሚያሳየው በትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሩት ውጤታማ መሆናቸውን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4.3 ከጥንድ ናሙና አንጻር የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያሳየው አማካይ ውጤት ልዩነት፣

| ቡድን | የፈተና ዓይነት | ናሙና (N) | አማካይ ውጤት (m) | መደበኛ ልዩነት (S.D) | መደበኛ የስህተት መጠን | የቲ ዋጋ (ቲ) | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ(በባለሁለት ጫፍ sig(2tailled) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | ቅድመ ትምህርት | 73 | 51.70 | 13.72 | 0.6308 | -3.78 | 73 | 0.05 |
| | ድህረ ትምህርት | 73 | 53.31 | 12.88 | 0.1914 | | | |

ከሠንጠረዥ 4.3. ከቀረበውም መረጃ መገንዘብ የሚቻለው በሁለቱ ፈተናዎች መካከል መጠነኛ የመጻፍ ችሎታ ልዩነት ታይቷል፡፡ገላጭ መረጃው እንደሚያመለክተው የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 51.70 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 53.31 ነው፡፡በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት 1.61 ሆኗል፡፡ይህም ማለት የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በአማካይ 1.61 ውጤት ተሻሽለዋል ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የቁጥጥር ቡድኑ የተማረበት ዘዴም ቢሆን በቆይታ ምንም አይነት ለውጥ አያመጣም ማለት እንደማይቻል ያመላክታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ለታየው ለውጥ ምክንያት ሊሆን የሚችሉ ሌሎችም ተላውጦዎች እንዳሉ መገመት ይቻላል፡፡ለምሳሌ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ፈተና በተለያየ ጊዜያት ደጋግሞ መፈተን ለታየው መጠነኛ ለውጥ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡እንደዚሁም በሁለቱ ፈተናዎች መካከል የታየው መደበኛ ልዩነት በቅድመ-ፈተና ወቅት 13.72 ሲሆን በድህረ-ፈተና ወቅት ደግሞ 12.88 ነው፡፡የድህረ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልዩነት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልዩነት 0.84ዝቅ ብሏል፡፡በሰንጠረዥ 3 የተመለከተው በቅድመ የፅሁፍ መጠይቅ እና በድህረ

የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ያለውን ልዩነት በስታቲስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማድረግ የዳግማዊ ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡በ79 የነፃነት ደረጃ (ቲ=-5.78) የpዋጋ(.001) ሆኗል፡፡በአጠቃላይበሁለቱ ፈተናዎች ያለው የውጤት ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.05 መጠን ሲታይ፣ጉልህ የሆነ ልዩነት ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4 ከጥንድ ናሙና አንጻር የሙከራ ቡድኑ በቅደምና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያሳየው አማካይ ውጤት ልዩነት

| ቡድን | የፈተና ዓይነት | ናሙና (N) | አማካይ ውጤት(m) | መደበኛ ልዩነት(SD | መደበኛየስ ህተትመጠ | የቲ ዋጋ(ቲ) | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነ ትደጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ | ቅድመ ትምህርት | 73 | 52.81 | 14.34 | 0.6308 | -6.665 | 73 | 0.001 |
| | ድህረ ትምህርት | 73 | 59.23 | 11.69 | 0.1914 | | | |

ከሰንጠረዥ 4.4 ከቀረበውም መረጀ መገንዘብ የሚቻለው በሁለቱ ፈተናዎች መካከል የመጻፍ ችሎታ ልዩነት ያመላክታል፡፡ገላጭ መረጃው እንደሚያመለክተው የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 52.81 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 59.23 ነው፡፡በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት 6.42 ሆኗል፡፡ይህም ማለት የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በአማካይ 6.42 ያህል ውጤቱ ተሻሽለው ተገኝቷል፡፡ እዚህ ላይ የቁጥጥር ቡድኑየተማረበት ዘዴም ቢሆን በቆይታ ምንም አይነት ለውጥ አያመጣም ማለት እንደማይቻል ያመላክታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ለታየው ለውጥ ምክንያት ሊሆን የሚችሉ ሌሎችም ተላውጦዎች እንዳሉ መገመት ይቻላል፡፡ለምሳሌ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ፈተና በተለያየ ጊዜያት ደጋግሞ መፈተን ለታየው መጠነኛ ለውጥ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡እንደዚሁም በሁለቱ ፈተናዎች መካከል የታየው መደበኛ ልዩነት በቅድመ-ፈተና ወቅት 14.34 ሲሆን በድህረ-ፈተና ወቅት ደግሞ 11.39 ነው፡፡የድህረ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልዩነት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልዩነት በ2.65 ዝቅ ብሏል፡፡እንደዚሁም የ(t=-6.665፣የp=0.001) ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደምቻለው በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ የውጤት ልዩነት በ0.05 መጠን የጉልህነት ደረጃ ስታይ፣በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንዳለ የp-ዋጋ ያመላክታል፡፡እዚህ ላይ የቁጥጥር ቡድንም ሆነ የሙከራ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል፡፡ሆኖም የሁለቱን ቡድኖች በቅድመ ትምህርት ፈተናዎቹና በድረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያሳዩትን ልዩነት በንጽጽር ሲታይ የሙከራ ቡድኑ በአማካይ ውጤት፣በመደበኛ ልዩነትና በp-ዋጋ በጣም የተሸለ እንደሆነ የቀረቡት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

### 4.1.3 የጽሁፍ መጠየቅ ውጤት ትንተና

ከጽሁፍ መጠየቅ የተገኘው ውጤት የጥናቱን ሶስተኛና አራተኛ ጥያቀዎችን ይመልሳሉ፡፡ ጥያቀዎቹም ትብብራዊ መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለው ተጽዕኖ ምን ይመስላል?እና በትብብራዊ የመማር ዘዴ የመጻፍ ክሂልን በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለው ተፅዕኖ ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው፡፡

ከላይ የቀረቡትን የጥናቱን ጥያቄዎች በቀጥታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ከመቅረባቸው በፊት በቅድሚያ ትብብራዊ መማር የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርቧል፡፡ይህም ሊሆን የሚችልበት ዋነኛ ምክንያት እውን ትብብራዊ መማር በሙከራ ቡድኑ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ መደረጉን ፣ተማሪዎች ስለተገነዘቡት የማስተማሪያ ዘዴ ምላሽ እየሰጡ እንደሆነ መረጋገጫ ይሆናል፡፡ጥያቀዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡

ሠንጠረዥ 4.5 በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተማሪዎችና የመምህራን አስተያየት ንጽጽራዊ ትንተና

| ተ/ቁ | በመጠየቁ የቀረበ ጽንሰ ሀሳብ | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | ትብብራዊ መማር የጽህፈት አቅሜ እንዲሻሻል አድርጎኛል | 123 | 83.1% | 25 | 16.8% | | | | |
| 2 | ትብብራዊ መማር ለሚያጋጥሙኝ የአጻጻፍ ችግሮች መፍትሄ እንዲያፈልቅ አግዞኛል | 48 | 32.4% | 93 | 62.8% | 6 | 4% | 2 | 1.3% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ትብብራዊ መማር ለራሴ ያለኝን ግምት አቅምና ለጽህፈት ችሎታ አለኝ የሚለውን መንፈስ አጠናክሮልኛል | 48 | 32.4% | 100 | 67.5% | | | | |
| 4 | ትብብራዊ መማር ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ሂደት አስቸጋሪ ነው | | | 8 | 5.4% | 20 | 13.5% | 120 | 81.1% |
| 5 | ትብብራዊ መማር በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ከግለሰባዊ ጥረት ይልቅ በቡድን ጥረት ላይ አተኩሬ እንድሰራ አደርጎኛል | 84 | 56.7% | 60 | 40.5% | 4 | 27.0% | | |
| 6 | ትብብራዊ መማር በመካከላችን ያለውን የጽህፈት ችሎታ ልዩነት በብዙ አቅጣጫ ማየት እንድችል ረድተውኛል | 89 | 60.1% | 59 | 39.8% | | | | |
| 7 | በትብብራዊ መማር ዘዴ ጽህፈትን መማር ወድጃለሁ | 59 | 39.8% | 87 | 58.7% | 2 | 1.3% | | |
| 8 | በትብብራዊ መማር ወቅት እያንዳንዱ የቡድን አባል ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል | 84 | 56.7% | 60 | 40.5% | | | | |
| 9 | የጽህፈት ችሎታን ለማሻሻል በትብብራዊ መማር ዘዴ ከመማር በግል መማር ይሻላል | | | 24 | 16.2% | 82 | 55.4% | 90 | 60.8% |
| 10 | ትብብራዊ መማር ብስለት የተሞላበት የመጻፍ ችሎታ እንዳዳብር አስችሎኛል | 93 | 62.8% | 55 | 37.2% | | | | |
| 11 | በትብብራዊ መማር ዘዴ የጽህፈት ክሂልን በቡድን በቡድን መማር ከጀመርኩ ወዲህ ሀሳቤን በጽሁፍ መግለጽ ብዙም አያስቸግረኝም፡፡ | 73 | 49.3% | 92 | 6.08% | 17 | 11.4% | | |
| 12 | ትብብራዊ መማር እርስ በርስ ያለንን ግንኙነት ከማሻሻል አንጻር አስፈላጊ | 89 | 60.1% | 59 | 39.8% | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሆኖ አግኝቻለሁ | | | | | | | | |
| 13 | ትብብራዊ መማር አንድን ሀሳብ በጽሁፍ በማስተላለፍ ሂደት ጊዜን ይሻማል | | | 26 | 17.5% | 120 | 81.0% | 2 | 1.35% |
| 14 | የጽሀፈት ችሎታን ለማሻሻል የማስተማሪያ ዘዴውን ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ | 3 | 100% | | | | | | |
| 15 | ትብብራዊ መማር ከጓደኞቼ ጋር በጽህፈት ዙሪያየተለያዩ መረጃዎችንና ልምዶችን እንዲለዋወጥ አስችሎኛል | 2 | 66.6% | 1 | 33.3% | | | | |
| 16 | ትብብራዊ መማር የተማሪዎችን የመጻፍ አቅም ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ተረድቻለሁ | 1 | 33.3% | 2 | 66.6% | | | | |
| | ጠቅላላ አማካይ | 75 | 50.14% | 48 | 32.5% | 15 | 10.1% | 10 | 7.3% |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 4.5 ውስጥ የሚገኙ በቅጥርና በመቶኛ የቀረቡ መረጃዎች የሚያመለክቱት ተማሪዎች ከዚህ በፊት ይማሩበት በነበረውና አሁን በተማሩበት (ትብብራዊ መማር)የመስተማሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ ንጽጽራዊ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የቀረበላቸውም 16 ጥያቄዎች በጥናቱ ወቅት የተማሩበት ትብብራዊ መማር በመጻፍ ችሎታቸው ላይ የመጣውን ለውጥ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም በአዎንታ ከተጠየቁት ጥያቄ መልስ ከሰጡ ተማሪዎች መካካል በአማካይ 75(50.14%) በጣም እስማማለሁ፣ 48(32.50%) እስማማላሁ ስመልሱ ቀርዎቹ 15(10.1%) አልስማማም እና 10(7.3%) በጣም አላስማማም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ከዚህ መረዳት የቻልኩት 123(83.1%) ተማሪዎችና መምህራን በምላሻቸው" ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማዎች የመጽፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው" ብለው ስመልሱ 25(16.89%) ተማሪዎችና መምህራን በምላሻቸው "በትብብራዊ ዘዴ"ከዚህ በፊት ከሚማሩት መንገድ የተለየ እንዳልሆነና፣በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል እንዳላመጣቸው ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በአሉታ ከተጠየቁት ጥያቄዎች(ጥያቄ 4፣9ና13) ትብብራዊ መማር ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ሂደት አስቸጋሪ ነው፤የጽህፈት ችሎታን ለማሻሻል በትብብራዊ መማር ዘዴ ከመማር በግል መማር ይሻላል እና ትብብራዊ መማር አንድን ሀሳብ በጽሁፍ

በማስተላለፍ ሂደት ጊዜን ይሻማል፤በማለት ለቀረቡት ጥያቄዎች ሚላሽ ስሰጡ በአማካይ 0(0%) በጣም እስማማለሁ፣4(2.7%) እስማማላሁ ብለው ስመልሱ ቀርዎቹ 74(50%) አልስማማም እና 70(47.24%) በጣም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ከዚህ መረዳት የቻልኩት 4(2.7%) ተማሪዎች በምላሻቸው "ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ሂደት አስቸጋሪ ነው፤ በትብብራዊ መማር ዘዴ ከመማር በግል መማር ይሻላል እና ትብብራዊ መማር አንድን ሀሳብ በጽሁፍ በማስተላለፍ ሂደት ጊዜን ይሻማል፤በማለት ስመልሱ ቀርዎቹ አብላጫ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በምላሻቸው 144(97.2%) ትብብራዊ መማር ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ሂደት አስቸጋሪ አይደለም፤የጽህፈት ችሎታን ለማሻሻል በትብብራዊ መማር ዘዴ መማር ይሻላል እና ትብብራዊ መማር አንድን ሀሳብ በጽሁፍ በማስተላለፍ ሂደት ጊዜን አይሻማም፤በማለት ምላሻቸውን በመስጠታቸው "ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማዎች የመጽፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው" ብለው ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ከላይ ለቀረበቡት ትብብራዊው የማስተማሪያ ዘዴ ከቀደመው የተለየ ሆኖ መቅረቡንና ትብብራዊው ዘዴ ወይስ የተለመደው ዘዴ በመጻፍ ትምህርታቸው የተሸለ ውጤታማ እንደነበር ንጽጽራዊ አስተያየት ለሚሹ ጥያቄዎች ምላሻቸውን ሰጥቷል፡፡በዚህ መሰረት የሙከራው ቡድን የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠየቅ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ የተዘጋጀው አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን አማካይ የጽሁፍ መጠየቅ ውጤት በልጦ በጉልህ ልዩነት የp ዋጋ(0.023)አሳይቷል፡፡በተገኘው መረጃ መሰረት አብዘኛቹ ተማሪዎች በሁለት ማስተማሪያ መንገዶች መካከል ልዩነት እንዳለ እንዳስተዋሉና ከተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ይልቅ ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተሸለ እንደጠቀማቸው በሰጡት ምላሽ አረጋግጨዋለሁ፡፡ይህ ምላሻቸው በጥቅሉ በ SPSS እትም 20 ተሰልቶ የተገኘው አማካይ ውጤት 3.8 ነው፡፡ይህም ውጤት ትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር ረድቶናል የሚለው ምላሻቸው ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ከተገኘው መረጃ መገንዘብ የተቻለው ሌላው አንድምታው የመስተማሪያ መንገድ የተለየ የማስተማሪያ መንገድ በመማሪያ ክፍላቸው እውን መሆኑን ነው፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና ፍተሻ መመርመር ነው፡፡በመሆኑም ዝርዝር ዓላማዎቹም ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ተማሪዎች በቅድመ እና በድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ምን አስተያየት እንዳላቸው ማየት፤የመጻፍ ችሎታን በተመለከተ በትብብራዊ መማር ዘዴና በግል መማር መካከል የታየው የተማሪዎች የቅደመ እና የድህረ ፈተና ውጤት ምን እንደ ሚመስል መመርመር ነው፡፡የነዚህን ዓላማዎች ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ በፈተና እና በጽሑፍ መጠየቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር በሙከራና በቁጥጥር ቡድን የተካተቱት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ለማወቅ በሁለቱም ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ የመጻፍ ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲወስዱ ተደረጓል፡፡ሁለቱም ቡድኖች በቅድመ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን በባዕድ ናሙና ቲ-ቲስት የተገኘውን አማካይ ውጤት(በሠንጠረዥ 1 ይመልከቱት) ይህ ደግሞ ሙከራዊ ጥናት ከመከናወኑ በፊት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን መካከል ጉልህ የሆነ የመጻፍ ችሎታ ልዩነት አለመኖሩ ሁለቱም ቡድኖች ተቀራረቢ የሆነ የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ከዚያም የቁጥጥር ቡድኑን በግል የመማር ዘዴ በመጠቀም የሙከራ ቡድኑን ደግሞ ትብብራዊ መማርን በመጠቀም ወደ ማስተማር ሥራ ተገብቷል፡፡

በሁለቱም ቡድን ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በተጠቀሱት ዘዴዎች አማካይነት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ የመጻፍ ችሎታ ፈተና እንዲወስዱ ተደረጓል፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተና እንደሚያሳየው በሙከራ ቡድኑ የተሳተፉ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት በቁጥጥር ቡድኑ ካሉ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በልጦ መገኘቱ ነው፡፡ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡በዚህም መሠረት በሁለቱም ቡድኖች መካከል በድህረ መጻፍ ፈተና

ጉልህ ልዩነት መኖሩንና የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት በልጦ መገኘቱ ነው (ሠንጠረዥ 2 ይመልከቱ)፡፡

ይህም መጻፍን በግል ከተማሩ ይልቅ በትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሩት የተሻለ ውጤት ያስመዘግቡ ይሆን የሚለውን ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን የመጻፍ ክሂል ትምህርት እርስበርስ በመረዳዳት፣በመደጋገፍ በመማራቸው ሊሆን ይችላል ብላ አጥኚዋ ትገምታለች፡፡በመሆኑም የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ትብብራዊ መማርን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር በሙከራ ቡድኑ ለተሳተፉ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ መሻሻል ማስገኘቱን ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ከፍተኛ ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ይህም የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት የበለጠ ሆኖ በስታትስቲክስ ሲታይ ቲ=-6.665 የp =ዋጋ (0.001) ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ሙከራዊ ቡድኑ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የጎላ ልዩነት እንዳለም ያሳያል፡፡በመሆኑም የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም ግኝት ትብብራዊ መማርን በክፍል ውስጥ መጠቀም ለተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ግብዓት ግልጽና ሊረዱት የሚችሉት ሊያደርግላቸው ይችላል ከሚለው ከkagan(1995)እና ከJacobs(2004) ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ምክንያቱም በትብብራዊ ቡድን ውስጥ በሚኖር የእርስ በርስ ተራክቦ ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ነገር ግልጽ እንዲ ሆንላቸውና እንዲብራራላቸው ይወያያሉ፣ይጠይቃሉ፡፡ተማሪዎች በሚወያዩበትና በሚጠይቁበት ጊዜ የተብራራ ግበዓት እንዲያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ አስፈለጊ በሆነ ጊዜ ይህንን ግብዓት አውጥተው እንዲጠቀሙበት ዕድሉን ያመቻቻል፡፡በዚህም ምክንያት በመተባበር መማር ስረጋገጥ በተግባር ሂደት የሚኖር ዲርጊትና እንቅስቃሴ በአዕምሮቸው ውስጥ ሊታወስ በሚችል መንገድ ተቀርጾ ስለሚኖር፣ይህንን በአዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ የተቀመጠ እውቀትና ክህሎት ደግሞ በተፈለገ ጊዜ ተማሪዎች አውጥተው አፍልቀው ሊጠቀሙበት ይችላሉ(አለማየሁ፣2009)፡፡

ለዚህ ግኝት አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት ተማሪዎች የተለያዩ ሚናዎችን ተከፋፍለው በመስራተቸውና እነዚህን ሚናዎች በየክፍለ ጊዜው እዲቀያየሩ በመደረጋቸው ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በእኩል ተሳትፎ እንዲያከናውኑ፣የቋንቋ ክህሎቻቸውን እንዲያጎለብቱና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አስችሏቸዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተግባር መጨረሻ በቡድን ሥራው ወቅት ስለነበራቸው ግላዊ ተሳትፎና እነሱ የተመደቡበት ቡድን ስለነበረው ጠንካራና ደካማ ጎን በተከታታይ እንዲያንጸባርቁ በመደረጋቸው ድክመቶቻቸውን እንዲያርሙ አስችሏቸዋል፡፡

በዚህ ግኝት ከድህረ ልምምድ ከመጻፍ ችሎታ የተገኛው ውጤት ጉልህ በመሆኑና ትብብራዊ መማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዳለው በማሳየት ግኝቱ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ካከሄዱ ሰዎች ማለት Ghaith(2003)ግኝት ጋር ይመሳሰላል፡፡

Karsak&orhan (2014) የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎችን በትብብርና በግል በመማር የመጻፍን ክሂል ለማዳበር የትኛው የተሻለ እንደሆነ ከ21 ተማሪዎች 12ቱን በሙከራዊ፣ 9ኙን በቁጥጥር ቡድን በመክፈል፤ሙከራዊ በድኑን በትብብራዊ መማር ቡድን፤የቁጥጥር ቡድኑን በግል በማድረግ አስተምረዋል፡፡የጥናቱም ውጤት የሚያመለክተው በትብብር መማር ቡድን የተማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸው ከፍ ብሎ መገኘቱን ነው፡፡ይህ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ለዚህ ግኝት መምጣት እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው ሌላኛው ነገር እያንዳንዱን የትብብር መማር ተግባር በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ ተማሪዎች እርስ-በርሳቸው እንዲደጋገፉና እንዲተጋገዙ ለማድረግ የግለሰባዊ ተጠያቅነትና የአዎንታዊ ተደጋጋፊነት መርህን መሰረት አድርገው ተግባራትን እንዲያከናውኑ በመደረጋቸው ነው፡፡ይህ ሁኔታም‹‹የቡድን አላማ መሳካት የሚወሰነው እያንድንዱን የቡድን አባል በቡድን ውስጥ ለመማርና የቡድኑን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርገው ጥረት ነው››ከሚለው ከJolliffe(2007፡3) ሀሳብ ጋር ይስማማል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በእያንድንዱ የትብብራዊ መማር ተግባር መጀመሪያ ላይ የስኬት መስፈርቶቹ ምንምን እንደሆኑ ስለሚነገራቸው ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ የተቀመጠላቸውን መስፈርት መሰረት አድርገው ስኬት ላይ እንዲደርሱ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያበረክቱና ውጤታማ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ውጤት ብልጫ እንዲያሳይ ያደረገው ምክንያት የትብብር መማር መሰረታዊ መርሆችየሆኑት የአዎንታዊ ተደጋጋፊነት፤ግለሰባዊ ተጠያቂነት፤የፊት ለፊት ተራክቦ፤መሰረታዊ መርሆች በሙከራ ውስጥ በተካተቱት ተማሪዎች ላይ በትክክል በመተግበራቸው ነው ብላ አጥኚዋ አምናለች፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያና አስተያየት

### 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞትጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳርነት በመፈተሽ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎችም የመጻፍ ችሎታን ማሻሻልን በተመለከተ በትብብራዊ መማር ዘዴና በግል መማር መካከል የታየው የተማሪዎች የቅድመና የድህረ ፈተና ውጤት በመገምገም፤ ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ተማሪዎች በቅድመ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቅ ምን አስተያየት እንዳላቸው በመተንተን፤በትብብራዊ መማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ የሚታየው ለውጥ ከመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎች ረገድ ምን እንደሚመስሉ በማየት፤ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከፈተናና ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትናዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ ያለው ሚና ለመፈተሽ የተማሪዎች ውጤት ምን እንደሚመስል መመርመር፣በትብብር የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ተገቢ መረጃ ከመረጃ ምንጮች ማለትም ከተማሪዎች እና ከመምህራን ሰብስቦ በመተንተን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የሙከራ ቡድን አማካይ ከቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት በ6.084 በልጦ ተገኝቷል፤ይህንን (ከሠንተረዥ 2) መመልከት ይቻላል፡፡ይህ ደግሞ የሚያሣየው በሁለቱ ቡድኖች መካከል በመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የታየው በትብብራዊ መማር ምክንያት በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ የሚታየው ለውጥ ከመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎች አንጻር የቅድመና የድህረ ፈተና ውጤቶች ተቃኝተዋል፡፡በዚህ ሙከራዊ ጥናት ውስጥ ለተማሪዎች የቀረበው ለቅድመና ለድህረ ፈተና የተዘጋጁ የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎችም፤ዐረፍተ ነገር መጻፍ፣የዐረፍተ ነገር ክፍሎቹን ቅደም ተከተል እንደገና ማደራጀት፣ጅምር ዐረፍተ ነገሮችን ማጠናቀቅ፤አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን በተገቢ ቦታቸው በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮችን ትርጉም አዘል ማድረግና ጅምር አንቀጽን ማጠናቀቅ ናቸው፡፡ንዑሳን ክሂሎቹ ከቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶቻቸው ጋር ተተንትኗል፡፡በተለምዷዊ የማስተማሪያ ዘዴ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሩ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የነበራቸውን የፈተና ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጋር ስነጻጸር የታየው መሻሻል የ0.342 አማካይ ውጤት ነው፡፡ይህ አማካይ ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በመጻፍ ችሎታ ፈተና ጉልህ ልዩነት ያለመኖርን ያሳያል፡፡

በትብብራዊ መማር አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሩ ተማሪዎች ደግሞ በቅድመ ትምህርት የነበራቸውን የፈተና ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጋር ስነጻጸር የታየው መሻሻል 6.98 አማካይ ውጤት መሆኑን አሳይቷል፡፡ይህ አማካይ ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በመጻፍ ችሎታ ፈተና ጉልህ ልዩነት መኖርን አመላክቷል፡፡በሁሉም ንዑሳን ክሂሎች የታየው የመጻፍ ችሎታ መሻሻል ውጤቱ በትብብራዊ መማር በተማሪዎች ላይ ያመጣው ውጤት ነው፡፡በመሆኑም ተለምዷዊ የማስተማር ዘዴ በመጻፍ ክሂል ንኡሳን ክሂሎች ላይ የነበረው ሚና ደካማ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የታየው የመጻፍ ችሎታ ማሻሻልን በተመለከተ በትብብራዊ መማር በተማሪዎች ላይ ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ መመርመር ነው፡፡ በሠንጠረዥ 4.5 በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተማሪዎችና የመምህራን አስተያየት ከንጽጽራዊ ትንተና መረዳት የቻልኩት 123(83.1%) ተማሪዎችና መምህራን በምላሻቸው" ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማዎች የመጽፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው" ብለው ስመልሱ 25(16.89%) ተማሪዎችና መምህራን በምላሻቸው "በትብብራዊ ማስተማር" ከዚህ በፊት ከሚማሩት መንገድ የተለየ እንዳልሆነና፣በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል እንዳላመጣቸው ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በዚህም የሙከራዊ ጥናት በቀረበው ጽሁፍ መጠየቅ በቀረበው ምላሽ በተሰበሰበው መረጃ እና በተተነተነው ውጤት ሲመለከት በትብብር መማር ውጤታማ እንዳደረጋቸው 83.1% ከጥናቱ ተሳታፍዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡በዚህም መሰረት በስታትስቲክስ ግልጽ ልዩነት በመታየቱ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

በአራተኛ ደረጃ በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ተማሪዎች በቅድመና በድህረ ፈተና ምን ግንዛቤ እንዳላቸው ማየት ሲሆን በዚህ ዙሪያ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ማየት ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በፈተና አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ መሠረት በማድረግ በትብብራዊ መማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኖ (ቲ=-3.78) ሆነዋል፡፡ በዚህም የሙከራዊ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት በመታየቱ በትብብራዊ መማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ለመሻሻል ዋነኛ ስነ ዘዴ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የተገኘ ውጤት እንደሚያሳየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድን በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለማሳየቱ ነው፡፡ነገር ግን የድህረ ፈተና ውጤት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድን ያስመዘገበው የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱን ነው፡፡በሰንጠረዥ 4.3 የተመለከተው በቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ያለውን ልዩነት በስታቲስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግማዊ ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡በ74 የነፃነት ደረጃ (ቲ= -3.78) የpዋጋ(0.001) ሆኗል፡፡በአጠቃላይ በሁለቱ ፈተናዎች ያለው የውጤት ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.05 መጠን ሲታይ፣ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡የፈተና ውጤት የሚያሳየው በትብብራዊ መማር የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ሚና እንዳለው በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

## 5.2..መደምደሚያ

ከሙከራ ጥናቱ የተገኘ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የሚከተለው መደምደሚያ ተሰጥቷል፡፡የሙከራ ጥናቱ ውጤት የሚያሳየው ከግል መማር ዘዴ ይልቅ ትብብራዊ መማር ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ተማሪ ተኮር የሆነው በትብብራዊ መማር በመጻፍ ክህል ላይ ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው በመረዳዳት፣በመወያየት፣በመጻፍ፣በመደማመጥ፣በመጠያየቅ ችግሮቻቸውን በመፍታት ከፍተኛ ደረጃ ያለው አስተሳሰብ ባለቤት እንዲሆኑ የሚያደርግ በመሆኑ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ሚና እንዳለው መረዳት ተችሏል፡፡

ትብብራዊ መማር ዘዴ ከክፍል ውስጥ ተራክቦ ወቅት በሙከራ ቡድኑ የተካተቱት ተማሪዎች በተዘጋጀላቸው ማለማመጃ ጽሁፍ ማለትም አንቀጽ መጻፍ፣ደብዳቤ መጻፍ፣ የተዘበራረቁ ሀሳቦችን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ መጻፍ፣የምንባብን ሀሳብ አሳጥሮ በመጻፍ እርስ በርሳቸው በመተራረም በመስራታቸው የመጻፍ ችሎታቸው ዳብሯል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል መንገድ ጓደኞቻቸውን መደገፍና ማበረታታት ሲችሉ እንደሆነ የትንተና ውጤቱ አረጋግጧል፡፡

በቡድን ተዋቅረው ሲሰሩ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በየጊዜው እያሻሻሉ እንዲሄዱ ማሻሻያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ተማሪዎች በቡድን በቡድን አድርጎ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ከላይ መምህራን ለተማሪዎች ግልፅ በሆነ መንገድ በመናገር እንዲተገብሩት የተለያዩ ድርጊቶችን በማድረግ መከታተል አለባቸው፡፡ተማሪዎችም የቡድናቸውንና የራሳቸውን መማር ሁኔታ ከፍ ለማድረግ እርስ በርስ በመደጋገፍ ለሚሰጣቸው ተግባር እራሳቸውንና ሌሎችን የቡድን አባላት መሳተፋቸውን በማረጋገጥ ሀላፊነታቸውን መወጣት መምህራንም በትብብር መማር ወቅት ሁሉም ሳይሆን ከቀረ ግን የትብብር መማር መርህ በሚገባ ሁኔታ የተተገበረ ሊባል አይችልም፡፡

## 5.3.የመፊትሔ ሀሳብ

| 93 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 |
| 94 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 |
| 95 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 96 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 |
| 97 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | 1 | 3 | 2 |
| 98 | 1 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 |
| 99 | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| 100 | 2 | 1 | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 2 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 101 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 3 |
| 102 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 103 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 104 | 3 | 2 | 1 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 |
| 105 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 1 |
| 106 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 1 | 4 |
| 107 | 3 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 108 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 2 |
| 109 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 |
| 110 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | 4 |
| 111 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 |
| 112 | 1 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 4 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 113 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| 114 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 115 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 116 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 |
| 117 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 |
| 118 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 |
| 119 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 |
| 120 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 |
| 121 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 |
| 122 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 |
| 123 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 |
| 124 | 4 | 4 | 4 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 2 |
| 125 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 1 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 126 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 1 | 4 |
| 127 | 3 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 128 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 2 |
| 129 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 |
| 130 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | 4 |
| 131 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 |
| 132 | 1 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 4 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 133 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 |
| 134 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 1 | 3 | 1 | 4 |
| 15 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 136 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 |
| 137 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 |
| 138 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 |
| 139 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 |
| 140 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 1 |
| 141 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 2 |
| 142 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 143 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 |
| 144 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 |
| 145 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 1 | 4 | 2 | 2 |
| 146 | 3 | 1 | 1 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 |

# አባሪ 9፡- በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተማሪዎችና የመምህራን ለማስተማር ለመምህራን ማሰልጠኛ የተዘጋጀ ማንዋል

# ክፍል አንድ

## 1.1.መግቢያ

በአማርኛ ቋንቋ ስራዓተ ትምህርት ውስጥ የማንበብና የመጻፍ ክህሎትን ለማሻሻልየ ሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ትምህርት ሚኒሲቴር በአዲሱ ትምህርት ፍኖተ ካርታ በማካተት ወዴ ትግበራ የገባንበት አመት በመሆኑ የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ መጠቀሚ አሰፈላግ ሆነዋል፡፡በዚህም በትብብራዊ መማር  የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና በከፍተኛ ደረጃ እንደምያሻሽል በግንዞበ ውስጥ በማስገባት ባለ ድርሻ አካላትን ማሰልጠን አስፈላግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

.የስልጠና ማኑዋሉ ያተከረው በትብብራዊ መማር  የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በተላይ ወላይተኛ አፍ-ፈት በሆኑ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ ትብብራዊ ማስተማር ላይ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በትብብራዊ መማር  የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ በጋቼኖ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳርነት በመፈተሽ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ስለሆነ ማኑዋሉ ይህንን አላማ ለማሳካት እንዲመች ተደርጎ ተዘጋጂቷል፡፡ ጥናቱ ሙከራዊ ጥናት እንደመሆኑ መጠን የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ለማስተማር ለተመረጡ መምህራን ስለ ትብብራዊ መማር ምንነት፣ ትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ትብብራዊ መማር መሰረታዊ መርሆች፣ትብብራዊ መማር ስልቶች፣በትብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና የትብብራዊ መማርና በግል መማር ያላቸውን ልዩነት የሚሉ ሀሳቦችና የትብብራዊ መማርና አተገባብር ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡ከዚህም የሙከራ ቡድን ትምህርቱን በትብብራዊ መማር ይመራል፡፡ይህን ጥናት የምታካሂደው ተመራማሪዋ ወደ ሙከራ ጥናት ከመግባቷ በፊት የሙከራ ቡድንና አተገባበሩ ስልጠና ሰጥቼዋለሁ፡፡

## 1.2.የማንዋሉ አስፈላጊነት

ይህ የአማርኛ ማሰልጠኛ ማንዋል ከዚህ በታች የቀረቡትን ታሳቢዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል፡፡

ሀ.ከትምህርት ዝግጂት አንጻር ለእያንዳንዱ አማርኛ መምህራን በእውቀት ላይ የተመሰረተ ሙያዊ ድጋፍ ለተማሪዎች መስጠት በሚያስችል መልኩ ድጋፍ ለመስጠት ነው፡፡

ለ.በአዲስ መልክ ተከልሶ የተዘጋጀውን አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማርና ለመደገፍ ይቻል ዘንድ ይህ ማንዋል ቅደም ተከተላዊ ይዘትን በጠበቀ መልኩ ተዘጋጂቷል፡፡

ሐ.ሥልጠና የወሰዱ መምህራን በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በቋሚነት ረጅም ጊዜ በማቆየት ይህንን ትምህርት ቤት ተኮር ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ማኑዋል በማዘጋጀት አማራጭ የማይገኝለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

መ.የአማርኛ መምህራን አድስ ተሻሽሎ በተዘጋጀው ስራዓተ ትምህርት ላይ ወጥና ቀጣይነት ባለው መልኩ መደገፍ እንድያስችል ይህንን ማንዋል ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 1.3.የማኑዋሉ ዓላማ

የዚህ ማኑዋል አጠቃላይ አላማ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚያስተምሩ መምህራን ሙያዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ እንደ መመሪያ የሚያገለግል ማኑዋል ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎችቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.3.1.ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ.በመምህራን መካከል የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት ለማጠናከር፡፡

ለ.የትምህርት ቤት ደረጃ በጋር የመስራት አቅም ባህልን ለማሳደግ አማርኛ በሚየስተምሩ መምህራን አቅም ለማጎልበት፡፡

ሐ.አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት ለሚያስተምሩ መምህራን በትብብራዊ መማር የመጻፍ ችሎታ ፣ላይ ክህሎት ለመጨመር ነው፡፡

## 1.4.ለስልጣና ተሳታፊ የቀረበ ማሳሰቢያ

ከምርምር ስነ-ምግባሮች መካከል ዋነኛው የተሳታፊውን ስምምንትና ይሁንታ ማግኘት ነው፡፡ይህ ሙከራዊ ጥናት በተሳካ ሁኔታ ይከናወን ዘንድ በአጥኝዋ የቀረበልሽን/ህን ጥያቄ ተቀብለሽ/ህ ስልጠናውን ለማካሄድ ፈቃደኛ መሆንሽ/ህ ጥናቱ መጠናከር ወሳኝነት ስላለው ስለምታደርጉልኛ ትብብር አድናቆቴንና ምስጋዬ የላቀ ነው፡፡የዚህ ስልጠና ማኑዋል የተዘጋጀው የትብብራዊ መማር ምንነትን፣ትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች፣ትብብራዊ መማር ስልቶች ትበብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና፣በትብብራዊ መማርና በቡድን መማር መካከል ስላለው ልዩነትና ስለ-አተገባበር ሀሳብ ለመለዋወጥ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡ይህ ማሰልጠኛ ማንዋል የተዘጋጀው ትብብራዊ መማርን አስመልክቶ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የፃፏቸውን ፅሁፎች መሠረት በማድረግ እና ጥናታዊ ጹሁፎችን መነሻ በማድረግነው፡፡

የስልጠናው ዋነኛ ዓላማ ለአንተ/ቺ ስልጠና ከተሠጠ በኋላ ሙከራዊ ቡድን ሆኖ ለሚመረጠው ክፍል የመፃፍ ክሂል በምታስተምሩበት ጊዜ ዘዴውን እንዲትተገብሩ ለማስቻል ነው፡፡

## 1.5.የተመደበ ጊዜ

በስልጠናው ወቅት ለእያንዳንዱ ትምህርት ይዘት የተመደበው ጊዜ መጠን በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | ይዘት | የተመደበጊዜ |
|---|---|---|
| 1. | የትብብራዊ መማር ምንነት | 1ሠዓት |
| 2. | የትብብራዊ መማር ጥቅም | 1ሠዓት |
| 3. | የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መረሆች | 1ሠዓት |
| 4. | የትብብራዊ መማር ስልቶች | 1ሠዓት |
| 5. | በትብብራዊ መማር የተማሪዎችንና የመምህራን ሚና | 1ሠዓት |
| 6. | ትብብራዊ መማርና በተለምዶ ቡድን መማር መካከል ያለ ውልዩነት | 1ሠዓት |

# ክፍል ሁለት

## 2.1.ትብብራዊ መማር ምንነት

በትብብር መማርን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ለአብነት ያክል የተወሰኑትን መመልከት Johnson & Johnson (1999) በትብብር መማር የሚባለው የአነስተኛ ቡድን ተማሪዎች አንድ ላይ በመስራት የራሳቸውንና የሌሎችን መማር ሁኔታ የሚያሻሽሉበት (የሚያሳድጉበት) እንደሆነ ሲገልፅ Ricrages &Rodgers (2003) በበኩላቸው ከሁለት እስከ አራት አባላት ያለው ቡድን የተሻለ ስራ ይሰራ ዘንድ መምህሩ የተለያዩ የትብብራዊ መማሪያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ Slavin (1987) ሲገልፁ በትብብር መማር የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትንሽ ቡድን በማቀናጀት እርስ በርስ በመበረታታት አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ሲገልፁ ተመሳሳይ Kagan&Kagan (2009) በትብብር መማር ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ እንደ ሆነ በመግለፅ የተለያዩ የትምህርት ዓይነት ያላቸው ግንዛቤ ለማሻሻል ልዩ ልዩ የመማር ተግባራትን የሚያከናውንበት ነው ብለዋል፡፡

ትብብራዊ መማር የሚባለው አነስተኛ ቡድን ተማሪዎች አንድ ላይ በመስራት የራሳቸውን የሌሎችን መማር ሁኔታ የሚያሻሽሉበት የሚያሳድጉበት ነው፡፡እንዲሁም የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን በትንሽ ቡድን በማቀናጀት እርስ በእርስ በመበረታታት አብረው የሚሰሩበት ነው፡፡ትብብራዊ መማር ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር ባላቸው በሥርዓት በተደራጀ ቡድኖች በመሆን አንድን የትምህርት ግብ ለማሳካት በጋራ በመሆን እየተደጋገፉ የሚሠሩበት ሥነ ትምህርታዊ ዘዴ ነው፡፡ትብብራዊ መማር ስብጥራዊ በሆነ መንገድ የተዋቀሩ ተማሪዎችን ባላቸው ውጤት ሊሆን ይችላል ከፍተኛ መካከለኛና ዝቅተኛ ብሎ በመክፈል በአነስተኛ ቡድን ውስጥ በማዋቀር ለጋራ ውጤት በመነሳት እርስ በእርስ በመተጋገዝና በመረዳዳት እንዲማሩ የሚያደርግ ስኬታማ የማስታማሪያ ዘዴ ነው፡፡በተጨማሪም በትብብር መማር ወቅት ተማሪዎች ቡድን ወስጥ በመሆን የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እርስ በርስ በመረዳዳት እና በመደጋገፍ የራሳቸውን መማር ሁኔታ በማሳደግ የሌሎችም እንዲያድግ የሚደረግበት ነው፡፡

ትብብራዊ መማር ተማሪዎች ማህበራዊ ክህሎታቸውን የሚያሳድጉበት የርስ በርስ መረዳዳት መንፈስ ማዳበር በቡድናቸው ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማጎልበትና የተማሪዎችን እርስ በርስ ግንኙነት ለማዳበር እንዲሁም አንድን ነገር በራስ የመስራት ችሎታ በማጎልበት በኩል በግልና በውድድራዊ ከሚሰሩት ሥራዎች የተሻለ ውጤት ማስገኘት ችሏል፡፡

## 2.2.ትብብራዊ መማር ጥቅሞች

ትብብራዊ መማር የፈጠራ ሀሳብን ያጎለብታል፣ተማሪዎች በነፃነት በደስታ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማድረግ አዲስ ለተፈጠረ ችግር በራሳቸው መፍትሄ እንዲሠጡ አስታዋፅኦ ያበረክታል በተማሪዎች ዘንድ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲጠነክር ያደርጋል በትብብራዊ ዘዴ ተማሪዎች አንድንተግባር የሚያከናውኑትና የሚማሩት እርስ በርሳቸው እየተወያዩና እየተግባቡ ስለሆነ ለማህበራዊ ተግባቦት ክሂሎት በጣም ያስፈልጋል፡፡ትብብራዊ መማር ተማሪዎችን በጥልቀት ማሰብን ያጎለብታል አካባቢን በደንብ ለመረዳት ያስችላል፣የደካማ ተማሪዎችን አቅም ከፍ ያደርጋል፣የተማሪዎችን አካዳሚያዊ ብቃት ያሻሽላል፣ከግላዊና ከውድድራዊ የመማር ዘዴዎች ይልቅ ትብብራዊ መማር የተማሪዎች ውጤት ከፍ እንደምያደርግ የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ይጠቁማሉ፡፡

ትብብራዊ መማር ተማሪዎች ለመማር እርስ በርሳቸው መነጋገርና መደማመጥ ይጠበቅባቸዋል እነዚህ ነገሮች ተማሪዎች የተለያዩ አመለካከቶችን እንዲቀበሉ የሌሎችንም ሀሳብ ስሜት በጥልቀት እንዲረዱ ሌሎችንም ሁኔታዎች ለማወቅ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

## 2.3.የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች

ትብብራዊ መማር ዓላማው ከግብ ሊደርስ የሚችለው ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን አምስቱ የትብብራዊ መርሆች የምንላቸው በወጉ በሥርዓት ሲተገበሩ ነው፡፡

### 2.3.1.አዎንታዊ ግንኙነት

ይህ መርህ የመጀመሪያውና ዋናው የትብብራዊ መማር መርሂ ሲሆን ተማሪዎች በተቧደኑበት ይዘት ላይ ያላቸውን አመኔታ በጋራ በመሆን እርስ በርስ ትብብራዊ መማር በመደጋገፍ፣በመረዳዳት፣ድርሻቸውን በመወጣት ያለወቁትን ነገር በግላቸው ጥረት በማወቅ ያገኙትን እውቀትና ክህሎች ለሌሎች በማካፈል ጥሩ ውጤት የሚያመጡበት ነው፡፡በአንድ ቡድን ውስጥ ባሉ አካላት መካከል በሚኖሩ አዎንታዊ ተደጋጋፊነት ካለ ሌላውን የቡድን አባል የሚያግዘውና የሚጠቅመው ነገር ሁሉ በዚያ ቡድን ውስጥ ያሉትን አባላት በሙሉ ይጠቅማቸዋል ወይም ያግዛቸዋል፡፡አንዱን የቡድን አባል የሚጎዳው ነገር ሁሉ በዚያ ቡድን ውስጥ ያሉትን አባላት ይጎዳቸዋል በሌላ አገላለፅ አዎንታዊ ተደጋጋፊነት ብዙ ለአንድ አንድ ለብዙ የሚያስበበት መርህ ነው፡፡በቡድን ውስጥ የሚወቀሩ ተማሪዎች ሁለት ሀላፊነት አለባቸው፡፡የመጀመሪያው በዕለቱ የቀረበው የትምህርት ይዘት መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች የቡድን አባላት እነሱ የተረዱትን ያህል እንዲረዱ ማድረግ ነው፡፡

### 2.3.2.የቡድን አባላት ተጠያቂነት

በቡድን ውስጥ የተዋቀሩ አባላት ለሚሰሩት ስራ ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ግለሰባዊ ተጠያቂነት የሚመጣው እያንዳንዱ የቡድን አባል የራሱን የስራ ድርሻ ተገንዝቦና የሌሎችን አባላት የስራ ድረሻ ግምት ውስጥ አስገብቶ በቡድኑ አላማ መሰረት የራሱን

ጥረት ሲያደርግ ነው፡፡በቡድኑ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ አባል ለሚሰራው ስራ ተጠያቂ ስለሆነ ለቡድኑ ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡በመሆኑም ሀላፊነታቸውን አምነው የራሳቸውን የስራ ድርሻ በመወጣት ለሌሎች አባላት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለቡድኑ ውጤታማ መሆን ወይም መውደቅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተጠያቂ ናቸው፡፡

### 2.3.3. ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ

ይህ መርህ ተማሪዎች ፊት ለፊት ሀሳብ በመለዋወጥ በመቀራረብ እውነተኛ ስራ አብረው በተነሳሽነት አንዱ የአንዱን የመማር ሁኔታ ከፍ በማድረግ በመረዳዳትና በመደጋገፍ እነዲሁም በመበረታታት እንዲማሩ የሚያደርግ ነው፡፡ፊት ለፊት ሀሳብ በሚለዋወጡበት ጊዜ ተማሪዎች ከዚህ ቀድሞ የተማሩትን ትምህርት አሁን እያከናወኑት ካለው ጋር እያዘመዱ እንዲወያዩ እንዲከራከሩና የተለያዩ ማብራሪያዎችን እነዲሰጡና እንዲቀበሉ ያስችላቸዋል፡፡እንዲሁም በመካከላቸው ያለው መስተጋብር ይጠናከራል፡፡

### 2.3.4. ማህበራዊ ክህሎታቸውን በአግባቡ መጠቀም መቻል

ይህ መርህ የሚያመለክተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ሰዓት ከሚማሩት ትምህርት እውቀት በተጨማሪ የራሰቸውን እና የቡድናቸውን ማህበራዊ ክህሎት ሊያሳድጉ የጋራ ዓላማ ለማሳካት እርስ በርሳቸው ተገናኝተው በመደጋገፍና በመረዳዳት በሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡በቡድኑ የሚሳተፉ አባላት ከፆታ፣ከዘር፣ከዕድሜ፣ ከእምነት፣ከቋንቋ ዳራ ወዘተ አንፃር እየታየ ተሰባጥረው በቡድን መካተት አለባቸው፡ ፡ስብጥራዊ የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎች የተለያየ የልምድ፣እውቀትና ችሎታ ያለቸው በመሆናቸው የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲጋሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## 2.4. የትብብራዊ መማር ስልቶች

አባዛኛዎቹ ምሁራን የትብብራዊ መማር ስልቶች በተለያዩ መንገዶች ዘርዝረው አስቀምጠዋቸዋል፡፡የተወሰኑት እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

| ለሰልጣኝ መምህራን ግል-ዕብረቃ የቀረበ ጥያቄ<br>1. ትብብራዊ መማር ስልቶች ስንት ናቸው?<br>*2.* ትብብራዊ መማር ስልቶችን በዝርዝር በማዘጋጀት ለቡድኑህ አቅርብ፡- |
|---|

**1.የጅግ ሳው ስልት፡-** በስራ ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡እያንዳንዱ የቡድን አባል በግላቸው የተወሠኑ የትምህርት ይዘትን(ጥያቄን)ሠርተው እንዲያመጡ ከተደረገ በኋላ ለሌሎች አባላት ያስረዳሉ፡፡ሁሉም የየራሳቸውን ካስረዱ በኋላ በዋና ዋና ነጥቦች ላይ ተወያይተው በመጨረሻ ለአጠቃላይ ክፍሉ የመረጡት የቡድን አባል ስራቸውን እንዲያቀርብላቸው ያደርጋሉ፡፡የጅግሳው ስልት ትምህርት የማቅረብ አላማ በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ የትብብር መማር ክህሎችን ለማስደረግ ነው በተጨማሪም ተማሪዎቹ ጠቅለል ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ በቡድን ስራ ወቅት የድርሻቸውን በመወጣት ሀላፊነት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡

**2.የጥንድ ውይይት፦** ይህ ዘዴ በአበዛኛው በሠፊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የምንተገብረው ሲሆን አራት ደረጃዎች አሉት፡፡የመጀመሪያው መምህሩ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን ያቀርባል፤ሁለተኛው ተማሪዎች በተሰጠው ጥያቄ ላይ በራሳቸው እንዲያስቡበት ያደርጋል፤ሦስተኛው ተማሪዎች በሀሳቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲነጋገሩበት ያደርጋል፤አራተኛው መምህራን የተማሪዎችን ስም በመጥራት ሀሳባቸውን ለሌሎች የቡድን አባላት እነዲያካፍሉ ያደርጋል፡፡

**3.ቀጥርን ሰጥቶ ራስን አንድ ላይ በማድረግ የማስተማሪያ ስልት፡-** አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ለእያንዳንዱ አባል ከአንድ እስከ አራት ቁጥር ይሰጣል ጥያቄዎችም ለቡድኖች በማቅረብ ሁሉም አባል መልሱን ማወቁን ለማረጋገጥ ራሳቸው አንድ ላይ እንዳያደርጉ ይጠየቃሉ፡፡መምህሩም አንድ ቁጥር በመጥራት ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች እጃቸውን እንዲያወጡ ወይም መልስ ለመመለስ እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡ይህ ተግባር በጣም ተገቢ የሆነ እርስ በርስ በመተማመን ሁኔታ እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ነው፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች በትክክለኛው መልስ ላይ መስማማታቸውን ለማረጋገጥ ሀሳባቸውን አንድ ላይ ስለሚያደርጉ ነው፡፡እንዲሁም ሁሉም የቡድን አባላት መልስ ማወቃቸውን ከማረጋገጥም በላይ ስማቸው እንዲጠራ በተለየ ሁኔታ ይጠባበቃሉ፡፡

**4.የዙር ውድድር፦** በመጀመሪያ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ማነቃቂያ ጥያቄ ይሠጣል፡፡ተማሪዎች ያላቸውን ሀሳብ እንደ ወረደ ይነገራሉ፤ነገር ግን ያመነጩትን ሀሳብ አያብራሩም ጥያቄ አይጠይቁም የሚሰጡት መልስ በቃል ወይም በጽሁፍ መልክ ሊሆን ይቻላል፡፡ሁሉም የራሱን ከተናገረ በኋላ ወደ ተዘረዘሩት ሀሳቦች መመለስ የቡድን አባላት ተራ ይወስዱና እያንዳንዱን ቃል፤ሀረግና ዐ.ነገር ምን እንደሆነ አጭር መልስ እንዲሠጧቸው ይጠይቃሉ ፡፡አካሄዱ አንድ ተማሪ ከጠየቀ በኋላ ሁሉም የቡድን አባል የመነጋገር ወይም የመጠየቅ ዕድሉን እስኪያገኙ ድረስ ይቀጥላሉ፡፡ብዙ ሀሳብ በማመንጨት ይበረታታሉ ምክንያቱም በዚሁ ስልት ምንም ለማንም ሂስ፡አስተያየት ሊሰጥ አይችልም ሁሉም የመጣለትን እንዲናገር ዕድል ተሰጥቶታል፡፡በዚህ ዓይነት ስልት በተሰጠ ርዕስ ላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ጥሩ አንቀፅ ለመስራት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ መምህሩ ከላይ የተዘረዘሩትን ስልቶች እንደ አመችነቱ መጠቀም ይቻላል፡፡ እንዲሁም በዚህ ጥናት በአንድ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላው ተማሪዎች በመኖራቸው ምክንያት የተማሪዎችን ቁጥር እስከ አስራሁለት ማድረግ ይቻላል፡፡

**5 የቡድን ጨዋታ፦** ቡድን በፍጥነት በተመሳሳይ ሰዓት ይመሰረትና የተለያዩ ወይም አንድ ዓይነት ጥያቄ በመስጠት ሀሳብ እንዲለዋወጡ እድል መስጠት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚያገለግለው አጠቃላይ የክፍሉ ተማሪ ለማነቃቃት ሲሆን ጥሩ ሀሳብን በማመንጨት የተስተካከለ ስልት ነው፡፡

| |
|---|
| ለሰልጣኝ መምህራን ግል-ፅብረቃ የቀረበ ጥያቄ<br>1. ለትብብራዊ መማር የተሸለ የማስተማር ስልት የተኛው ነው? ምክንያት በማቅረብ አብራራ፡- |

## 2.4. በትብብራዊ መማር የተማሪዎች ሚና

በትብብራዊ መማር ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ሚናዎች አሏቸው፡፡ሚናዎችም የቡድን መሪ፤ዘጋቢ፤ተመልካችና ተቆጣጣሪ ናቸው፡፡ከዚህም በተጨማሪ የተሻለ የስራ ድርሻ ካለ መጨመር ይቻላል፡፡በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የሚሳተፉ የቡድን አባላት፡-ለቡድኑ መሳካት የራሱ የሆነ አስታዋፆኦ ያበረክታሉ፤ሌሎች የቡድን አባላት የራሳቸውን አስታዋፆኦ እንዲያደርጉ ያበረታታሉ፤ሁሉም የቡድን አባላት አዎንታዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፤ የሰሯቸውን የቡድን ስራ ለሌሎች ያካፍላሉ፤ለጋራ አላማቸው መሳካት እየተረዳዱ ይሰራሉ፤ የተሠጣቸው የስራ ድርሻ በአግባቡ ይወጣሉ፡፡

## 2.5. በትብብራዊ መማር ወቅት የመምህራን ሚና

በትብብራዊ መማር ሂደት የመምህራን ሚና ከልማዳዊ የቡድን ማስተማር የተለየ መሆን አለበት፡፡በትብብራዊ መማር ወቅት መምህራን ብቸኛ የዕውቀት ምንጭ በመሆን ለተማሪዎች እውቀት ማስተላለፍ የለባቸውም፡፡

የመምህራን ሚና፡-ተማሪዎችን በቡድን መመደብ፤ተማሪዎችን በውይይት በመፃፍ ችግሮችን እንዲፈቱ ማድረግ፤የትምህርት ዕቅድን ከትብብራዊ መማር አንፃር ማዘጋጀት፤በትንሽ ቡድን በማደራጀት የዕለት ተሞክሮዎችን መመዘን፤የሚሠራውን ተግባር ለተማሪዎች ማቅረብና ማብራራት፤የመማር ሁኔታን መቆጣጠር፤ተማሪዎችን መገምገም ናቸው፡፡

## 2.5. በትብብራዊ መማርና በቡድን ስራ መካከል ያለ ልዩነት

### 2.5.1.በቡድን መማር

በቡድን መማር ማህበራዊ ክህሎት ታሳቢ ይሆናል እንጂ በስልት እንዲማሩ አያደርግም፤የግለሰብ ኃላፊነት ለራስ ብቻ ነው፡፡የተወሠኑ ተማሪዎች አብዘኛውን ስራ ይሠራሉ እንጂ በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ መደጋገፍ የለም፤የተማሪዎችን የተለያዩ ችሎታ መሠረት ያደረገ ስብጥራዊነት አይታይበትም፤በተማሪዎች አካዳሚክ ዕድገት ላይ ብቻ ያተኩራል፤እውቀት የሚያዋቀረው ስልጣን ባለው አካል ነው፤የሚያተኩረው የተሰጠን ስራ ማጠናቀቁ ብቻ ላይ ነው፡፡

### 2.5.2. በትብብራዊ ዘዴ መማር

.በትብብራዊ ዘዴ መማር በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ መደጋገፍ ይፈጥራል፤ የተማሪዎችን የተለያዩ ችሎታ መሠረት ያደረገ ስብጥራዊነት ይታይበታል፤ማህበራዊ ዕድገት ልክ እንደ አካዳሚክ ዕውቀት እውቅና ይሠጣል፤ተማሪዎች እውቀት የሚያዋቅሩት ከጓደኞቻቸውና ከመምህራን ጋር በመተባበር ነው፤እያንዳንዱ የቡድንአባል ጥረት እንዲያደርግ ያበረታታሉ፤መምህራን ለስኬታማ የቡድን ስራ አስፈላጊ የሆኑትን ማህበራዊ ክህሎቶችን ያስተምራሉ፤ግለሰቦች ለራሳቸውና ለቡድኑ አባላት ኃላፊነት አለባቸው እያንዳንዱ ተማሪ ጉዳዩን በደንብ ማወቅ አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

## 3.1. የራስን ተሳትፎ መገምገሚያ ቅፅ

ውድ ተማሪ! ከዚህ በታች በትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ በትብብራዊ ቡድን የነበረውን ግላዊ ተሳትፎ በተመለከተ ራስህን/ራስሽን የምትገመግሙበት ጥያቄዎች ቀርበዋል የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበብክ/ሽ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ አመልክት/አመልክቺ

| ቁጥር | ጥያቄ | ሁልጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | በፍፁም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በትብብር መማር ከልብ የሆነ የመረዳዳት ስሜት ፈጥሮልኛል | | | |
| 2. | ከቡድኑ የተረዳሁትና ያለኝን መረጃ ለጓደኞቼ አካፍያለሁ | | | |
| 3. | የተማርኩትን ትምህርት ማጠቃለል ችያለሁ | | | |
| 4. | በቡድናችን ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱ አባላት የተሠጠንን ስራ መስራታቸውን አረጋግጣለሁ | | | |
| 5. | የተማርኩትን ትምህርት በሚገባ ተረድቻለሁ | | | |
| 6. | የተለያዩ መረጃዎችን በማስታወሻ በመያዝ የቡድን አባላቶችን ማስረዳት ችያለሁ | | | |
| 7. | በቡድናችን የተሠጠውን ሥራ ትኩረት አድርጌ እንዲሠራ አደርጋለሁ | | | |

3.2 ውድ የቡድን አባላት ከዚህ በታች ቡድናችሁ በትብብራዊ መማር ሂደት የነበረውን አጠቃላይ ተሳትፎ በተመለከተ የምትገመግሙባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል።ጥያቄዎችን በማንበብ ከቀረቡት አማራጮች መካከል አንዱን ምረጡ

| ቁጥር | ጥያቄ | ሁል ጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | በፍፁም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አብሮ መማር በስምና በመልኩ ከመተዋወቅ ባለፈ ጠንካራ አዎንታዊ ግንኙነት ፈጥሯል | | | |
| 2. | በቡድናችን የያዝነውን ማስታወሻ ለሌሎች ቡድን አባላት ማካፈል ችለናል | | | |
| 3. | ሁላችንም ከልብ የሆነ የመረዳዳት ስሜት ፈጥሮብናል | | | |
| 4. | በአንድ ላይ በውይይት ያጠናከርነውን ለቡድን አባሎቻችን እንናገራለን | | | |
| 5. | በቡድናችን ውስጥ ጥያቄዎችንወይም መልሶችን መገንዘብ ካልቻልን በጋራሆነን ሀሳቡን ግልፅ ለማድረግ እንሞክራለን | | | |

## አባሪ 10፡-ለሙከራ ቡድን መማሪያ የተዘጋጀ የትምህርት እቅድ

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የመምህሩ/ርቷስም፡-…………………..
የትምህርቱ አይነት፡-አማርኛ

ክፍልና ሴክሽን 10ኛ A-D

የትምህርቱ ርዕስ፡-አንቀጽ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ፡-40 ደቂቃ

ቀን፡-……………………….

## የትምህርቱ ዓላማዎች

1.ትምህርቱ ዓላማ፡-ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ስለ አንቀጽና መንደርደሪያ ዐ.ነገር በየቡድናቸው በመሆን ይወያያሉ፡፡

፡-የውይይታቸውን ሀሳብ ለቡድን አባሎቻቸውና ለሌሎች ቡድኖች ያካፊላሉ፡፡

፡-የአንቀጽን አጻጻፍ ይለያሉ፡፡

፡-አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

2. ትብበራዊ ዓላማ፡-የስራ ድርሻቸውን ይለያሉ፣ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያት እርስ በእርስ መረዳዳት፣ከአንድ ቡድን ወደ ሌላ ሄዶ አለመረበሽ፣ከመምህራቸው ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣ወሳኔዎችን በጋራ ማቅረብ፡፡

- በቡድን አባላት ብዛት፡-በአንድ ቡድን 10-12 ተማሪዎችይኖራሉ፡፡
- ተማሪዎች እያንዳንዱ ተማሪ ውጤት መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የሚያስፈልጉ የትምህርት ቁሳቁሶች፡-ለማስተማሪያነት የተዘጋጀ ማንዋል፣ጥቁር ሰሌዳ
- የተማሪዎች ሚና፡-በእያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉትን ሚናዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ አባላት ሊኖሩት ይገባል፡፡የቡድኑ አባላት ስራዎችን መከፋፈላቸውን የሚከታተልና ቡድን በበላይ ሆኖ የሚመራው መሪ ዋና እና ምክትል፡የቡድኑን ሀሳብና ውሣኔ የሚጽፍና ሪፖርት የሚያጠናክር ዘጋቢ ወይም ጸሀፍ፤ተማሪዎች በየትብብራዊ ቡድናቸው በመሆን የተወያዩትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው የሚያስማ አቅራቢ፤እያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠውን የስራ ድርሻ ማከናወኑና አለማከናወኑን የሚከታተል አረጋጋጭ፤አባላቱ ለሚያከናውኑት ተግባር ተገቢውን የሀሳብ ማበረታቻ እየሰጠ የበኩላቸውን አስታዋጾ እንዲሚያበረክቱ የሚያነቃቃ አበረታች፤ ለቡድነ ውይይት ተግባሩ የተመደበውን ሰዓት የሚከታተል ጊዜ ጠባቂ፤የቡድኑን ተግባር ትክክለኛነት ገምጋሚ ይመደባል፡

በትምህርት አቀራረብ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት፡-ቅድመ ጽህፈት መምህሩ የትምህርቱን ዓላማና በትምህርቱ መጨረሻ የሚጠበቀውን ባህሪ ይነገራል፤የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋውቃል፤ስለአንቀጽና መንደርደሪያ ዐ.ነገር ምንነት ተማሪዎችን በየቡድናቸው እንዲወያዩ ያደርጋል፤በውይይታቸው ወቅት ግልጽ ያልሆነላቸው ሀሳብ ካለ በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፤ስለ አንቀጽ የቀረበውን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው በማስረዳት የአሰራር መመሪያዎችን ያስተላልፋል፡፡

ተማሪዎቹም የትምህርቱን ዓላማና መጨረሻ የሚጠበቅባቸውን ባህሪ ይለያሉ፤የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያገናዝባሉ፤ስለአንቀጽ ስለመንደረደሪያ ዐ.ነገር ምንነት በየቡድናቸው ይወያያሉ፤በውይይታቸውም ወቅት ግልጽ ያልሆነላቸው ሃሳብ ካለ ይጠይቃሉ፤ስለ አንቀጽ የቀረበውን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ መጻፍ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

## የጽህፈት ጊዜ

ተማሪዎች ስለ አንቀጽ የተሰጣቸውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ በግላቸው አንቀጽ ይጽፋሉ፤የጻፉትን አንቀጽ አጠገባቸው ላለ አንድ ተማሪ ያሣያሉ፡፡አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች የጻፉትን በአንድ ላይ በቡድ ናቸው በውይይት ያጠናክራሉ፡፡በመቀጠልም ከሌላ ቡድን ጋር ይተራረማሉ፡፡ድህረ ጽህፈት መምህሩ የግልና የቡድን ተግባራቸውን እንዲገመግሙ ያደርጋል፤ተማሪዎች ስለሰሯቸው ስራዎች ግብረ መልስ ይሰጣል፤ተማሪዎችም ተግባራቸውን ይገመግማሉ፤ግብረ መልስ ይቀበላሉ፡፡ በትብብራዊ ቡድኑ አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር የማድረጊያ ዘዴ ነው፡፡

በቡድን አባላት መካከል አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር ሁሉም ተማሪዎች በየትብብራዊ ቡድኖቻቸው አንዱ ሌላውን በማገዝ መስራት እንዳለባቸው መንገርና በትብብር በሚሰሩበት ጊዜም አዎንታዊ ተደጋጋፊነታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የቡድን አባል የተስማሙባቸው ለሁሉም ጥያቄዎች መልሶችን ለመፈለግ መተግበር በትብብራዊ ቡድኑ ግለሰባዊ ተጠያቂነት እንዲኖር የማድረጊያ ዘዴለሁሉም የመጻፍ ክሂል ጥያቄዎች መለሶችን የቡድን አባሎቻቸው በደብተሮቻቸው ላይ እንዲጽፉ የሚያደርግ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲሁም መልሶችን እንዲመልሱ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው ለመልሶቹ ለምን የሚል ጥያቄ ቢጠየቁ ምክንያታዊ ሆነው መመለስ አለባቸው፡፡የስኬት መስፈርት መግለጽ ሁሉም የቡድን አባለት ውጤታማ የሚሆኑት የቀረበላቸውን የመጻፍ ችሎታ መልመጃዎችን በትክክል በመተግበር፣በመረዳት ከሰሩ ነው፡፡ተማሪዎቹ ለመለሷቸው መለሶች እጅግ በጣም ጥሩ፣በጣም ጥሩ፣ጥሩ በማለት ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡መከታተልና ጣልቃ መግባት ተማሪዎች በቡድን ሆነው የተሰጣቸውን የመጻፍ ችሎታ ተግባራት በሚሰሩበት ጊዜ ተግባራቱን ምን ያህል እየሰሩ ወይም እያከናወኑ እንዳሉ መከታተል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጣልቃ በሚገቡበት ጊዜም ችግሩን መለየትና ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሀሳብ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

የመምህሩ ስም……………………………………………ፊርማ---------------ቀን----------------

የትምህርት ክፍሉ መምህር ስም-----------------------ፊርማ……….......ቀን----------

የመ/ማ/ም/ርዕስመምህር

## አባሪ 11. ማስተማሪያ ጽሁፍ

ትብብራዊ መማር ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ማሻሻል በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ጽሁፍ፡-

### ትምህርት አንድ

1.ከዚህ በታች ስለ አንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠችውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አነቀጽ ጻፉ፡-

ሀ.አርንጓዴ አሻራ ማሳረፍ

ለ.ባህላዊ ጋብቻ

ሐ.ማህበረሰብና ጤና

አንቀጽ ማለት አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለፅ ሲባል፣በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሀሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ ዓረፍተ ነገሮች የሰፈሩበት ቅርፅ ነው፡፡አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ሀይለ ቃል (መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገሮችን) እና ከአንድ በላይ መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ሊይዝ ይችላል፡፡መንደርደሪያ ዐረፍተነገሩም በአንቀጽ መጀመሪያ፣በአንቀጽ መጨረሻ፣በአንቀጽ መጀመሪያና መጨረሻ ሊገኝ ይችላል፡፡የሚከተሉትን ሁለት ምሳሌዎች ተመልከቱ

ሀ.የህይወቱ ታርክ ፋጽም ገድል ነው፡፡ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው፤የራሱን ጠጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክተው አያውቅም፡፡ማለዳ አይናገርማ፤በጠረሙስ የሞላውን ከጠጣ በኃላ ማታ ስራገም ወይም ስሳደብ፣ሰፎክር ወይም ስያቅራራ ድምጽ ከፈረንጂ ውሻ ድምጽ ይዎፍራል፡፡ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ጋር ሁሉ ማታ ይስቃል፡፡ የሰለማታው አይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ብሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው፡፡ከሰለምታው ጋር ድምጽ ትሰማለቹሁ፡ከአፍ ምወጣውን አንድ ቃል ግን መለየት አትችሉም፡፡

ምንጭ(ተመስገን ገብሬ፣ጡጉላለው ሳካራም፣1941፣ከ1-8 ለማስተማሪያእንድመች ተሸሻሎ የቀረበ)

ለ.በመጀመሪያ ጊዜ በኩራት ዐይን የቤቱን ዕቃ አንድ በአንድ ይመለከት ገባ፡፡ውጪ የደመቀ የፀሐይ ብርሀን ቢኖርም የዝምታው አዝቅት እና ጽላሎት በስውር መንገድ ተዋህደው የዕንግዳ ቤቱን ብርሀን ደባብ አድርጎውታል፡፡በብርሀን ዓይን የሚያሞቀው የምንጣፍና የሶፋዎች ደማቅ ቀይ ቀለም አሁን የረጋ ደም መስሏል፣ወርቃማ ሆነው በጥቁር ጥላት ያጌጡ የመስኮት መጋረጃዎች በብርሀን ያለቸውን ድምቀት አጥተው ፈዝዘዋል፡፡ከውጪ ወደ ውስጥ ሲገቡ በስተቀኝ ባለው ግርግዳ ላይ የተሰቀለው በህብረ ቀለማት የተሰራው ሥዕል ብርሃን በማጣቱ ውበት ጠፍቷል፡፡

በአንቀጽ ሀ ውስጥ መንደርደሪያ ዓረፍ ተነገሩ(ኀይለቃሉ)ስድስተኛው ዓረፍ ተ ነገር ነው፡፡ስለሆነም መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ሁል ጊዜ የአንቀጽ መጀመሪያ ዓረፍ ተነገር መሆን እንደሌለበት ማስተዋል ያሻል፡፡

በአንቀጽ ለ የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር መንደረደሪያ ዓረፍተ ነገር ሲሆን የተቀሩት ዓረፍተ ነገሮች ይህንኑ የሚያብራሩ ናቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

2.ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል መርጣችሁ ድርጊትና ጊዜን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለቡድናችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ.የዶሮ ቤት አሰራር

ለ. ገንፎ አሰራር

ሐየክትፎ አሰራር

መ.የቡና አፈላል

# ትምህርት ሦስት

3.1 ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳይ መካከል አንዱን በመምረጥ አንቀጽ መጻፍ የሚስችል መንደረደሪያ ዓረፍተ ነገር ከጻፋችሁ በኋላ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ሀ.በአካባቢ የልማት ዘመቻ በንቃት መሳተፍ

ለ.መጥፎ ባህርይ ያላቸው ስዎች በህብረተሰብ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት

ሐ.የሀገር ፍቅር

መ.ታሪካዊ ቅርስ

3.2. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች በማቃናትና ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ አንቀጽ ጻፉ

ሀ.ለዚህም በሀይለ ቃሉና እርሱን የሚያብራሩ ዓረፍተ ነገሮች መካከል ግልጽ የሆነ ዝምድና መኖር አለበት፡፡

ለ.አንቀጹን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ሀይል አለው፡፡

ሐ.ሀይለ ቃል በአጠቃላይ መንደረደሪያ ሃሳብ ሲሆን፣የአንቀጽ ጭብጥ በመሆኑ ያገለግላል

መ.አንድ አንቀጽ በውስጡ ሀይለ ቃል የሚባል ዋና ክፍል አለው፡፡

# ትምህርት አራት

4.1.ስለ አስተዋጽኦ ምንነት የቀረበውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አስተዋጽኦ(ቢጋራ)ንደፉ፡፡

ሀ.የቤተሰብ ምስጢር አለ መጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት

ለ.የአየር ንብረት መዛባት በሰው ላይ የሚያመጣው ጉዳት

ሐ.የሃይማኖት እኩልነት መከበር ያለው ጠቀሜታ

መ.አድሎአዊ አሰራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች አስተዋጽኦ መንደፍ

አስታዋፅኦ አንድን ድርሰት ለማዘጋጀት ሲታቀድ በተፈለገው መንገድ ሃሳብን ለማደራጀትና ለማስፈር የሚረዳ ንድፍ ነው፡፡አስታዋፅኦ አንድ ጸሀፊ ከዋናው ሃሳብ እንዳያፈነግጥ ሀሳቡን አስቀድሞ በተለመደው መንገድ እንዲያቀርብ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ከዚህም በቀር እንደዚህ ዓይነት አስታዋፅኦ ያዘጋጃ ፀሐፊ በራሱ ሀሳብ ተውጦና ግራ ተጋብቶ ሊቀር አይችልም፡፡ለዚህም ይረዳ ዘንድ አስታዋፅኦ ዝርዝር ሆኖ ቢቀርብ ይመረጣል፡፡አስታዋፅኦ ጥቅሙ ከዋናው ርዕስ እንዳይወጣ ያደርጋል፡፡ዓለማውን ግልፅ ለማድረግና ሀሳብን ከዓላማው ጋር ለማዘመድ ይጠቅማል፣ስለ ፃፍነው ጉዳይ መነሻና መድረሻውን በትክክል እንዲንረዳ ያደርጋል፡፡ለአብነት ያህል ፀሐፊው የአየር ብክለትና መንስኤዎች በሚል ርዕስ ድርሰት ለመፃፍ አስቦ በቅድሚያ አስታዋፅኦ ነደፈ የአየር ብክለትና መንስኤዎች

## 1.የኢንዱስትሪዎች ጭስ

1.1 የቀላል ኢንዱስትሪዎች ጭስ

1.2የከባድ ኢንዱስትሪዎች ጭስ

1.3 የኑክሌር ማብለያ ኢንዱስትሪዎች የሚያስወግዱት ዝቃጭ

## 2.ጦርነት

2.1የከባድ ፈንጆች ጭስ

2.2የኑክለር ፍንዳታ

2.3የቀላል መሳሪያዎች ጭስ

## 3.የተሽከርካሪዎች፣የአውሮፕላኖችና የሮኬት ጭስ

3.1 የአነስተኛና የትላልቅ አውሮፕላኖች ጭስ

3.2 የቀላልና የከባድ ተሽከርካሪዎች ጭስ

3.3 የሮኬት ጭስ

## 4.የተፈጥሮ አዳጋዎች የሚፈጥሩት ከፍተኛ ጭስ

4.1የእሳተገሞራ ፋንዳታ

4.2ከፍተኛ የደን ቃጠሎ

## 5.መጥፎ ሽታ የሚያመጡ ፋብሪካዎች

5.1 የእርድ አገልግሎት የሚሰጡ ፋብሪካዎች

5.2የቆዳ ፋብሪካዎች በ2000 ዓ.ም ከተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ የተወሰደ

ትምህርትአምስት

6.ቀደም ሲል ትምህርት አራት ስር ያዘጋጀችሁትን ቢጋር (አስተዋጽኦ) መሠረት በማደርግ አንድ አንቀጽ በቡድን ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

7.ቀደም ሲል አስተዋጽኦ ለመንደፍ የሚያስችሉ አራት ርዕሶች ቀርቦላችሁ አንዱን በመምረጥ አስተዋጽኦ እንዲትፅፉ መደረጉ ይታወቃል፡፡አሁን ደግሞ በቡድን ተወያይታችሁ አንድ ርዕስ ከመረጣችሁ በኋላ፣በመረጣችሁት ርዕስ ጉዳይ መሠረት አስተዋጽኦን ተባቢራቹሁ ጻፉ፡፡

# ትምህርት አምስት

## የስራ ደብዳቤ

ብዙ የደብዳቤ ዓይነቶች አሉ፡፡ከነዚህ ውስጥ አንዱ የስራ ደብዳቤ ነው፡፡የስራ ደብዳቤ በተቋማት፣በተለያዩ ድርጅቶች፣በትምህርት ቤት ወዘተ ውስጥ ለተለያዩ ክፍሎችና ለግለሰቦች ይጻፋል፡፡የስራ ደብዳቤ፤የሚመለከተውን አካል ለማስታወስ አንድን መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት እነዲደረግ  ለማሳሰብና ትዕዛዝ  ለማስተላለፍ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

- የስራ ደብዳቤ የተፃፈለት ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
- የስራ ደብዳቤውን የፃፈው ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
- የተፃፈበት ቀን
- የተፃፈበት ጉዳይ
- ዝርዝር ሐተታ
- ከሰላምታ ጋር የሚለውን ቃል እንደ መልካም ምኞት መግለጫ ይወሰዳል፡፡

ስለ ስራ ደብዳቤ አጻጻፍ የተማራችሁትን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ክበባት ላይ ያላችሁን የተሳትፎ ደረጃ (ሁኔታ) በተመለከተ የትምህርት ቤታችሁን አድራሻ በመጠቀም በቡድን እየተወያያችሁ ደብዳቤ ጻፉ፡፡የጻፋችሁትን ደብዳቤ ለሌላኛው ቡድን  አሳዩና እንደገና አሻሽላችሁ ጻፉ፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን የስራ ደብዳቤ ምሳሌን በአስተውሎት ተመልከቱና የስራ ደብዳቤ በቡድን ሆናችሁ ጻፉ፡-

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

ምሳሌ 1

ቁጥር ጋትቤ/            /12

ቀን   15/08/2015 ዓ.ም

ጋቼኖ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት

ጋቼኖ

ለመምህር ……………………../ለክበቡ ተጠሪ/

ባሉበት.

ጉዳዩ፡-በፀረ-ኤድስ  ክበብ ተሳታፊ የሆኑትን ተማሪዎች ስም ዝርዝር እንዲሰጠን ስለ ማሳወቅ፡-

በ2015ዓ.ም በጋቼኖ ሁለተኛ ደረጃ  የትምህርት ቤት የፀረ-ኤድስ ክበብ አባለት በምርጫቸው የክበቡ አባል ለመሆን የተመዘገቡ ተማሪዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በመሆንም ከተማሪዎች መካከል ለማህበረሰብ አገልግሎት ለስልጠና ተማሪዎችን ለማስገባት ስለፈለገን የተማሪዎችን ስም ዝርዝር ከፆታ ጭምር እስከ ቀን 15/08/2015 ዓ.ም ደረስ ለትምህርት ቤት እንድታቀርብ እናሳውቃለን፡፡

ከሠለምታ ጋር!!

ት/ቤቱ

ግልባጭ

ለጋቼኖ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት

ጋቼኖ

# ትምህርት ሰድስት

## የግል ደብዳቤ

ከዚህ በታች የቀረበውን የግል ደብዳቤ መሠረት በማድረግ ከቤተሰባችሁ መካከል ለአንድ ሰው ደብዳቤ ጻፉ፡፡

የግል ደብዳቤ ለዘመድ፣ወዳጅ ፣ለቤተሰብ የሚጻፍ የደባዳቤ ዓይነት ነው፡፡በግል ደብዳቤ ሰዎች ስለ ራሳቸው፣ስለ ቤተሰባቸው፣ስላሉበት አካባቢ ወዘተ መረጃዎችን ይለዋወጣሉ፡ ፡የግል ደብዳቤ ሲጻፍ የሚከተሉትን ቅርፅ ይኖረዋል፡፡

1.የተጻፈበት ቀን

2.የላኪ አድራሻ

3.የተቀባይ አድራሻ

4.የመግቢያ ሰላምታ

5.ሐተታ

6.መደምደሚያ

7.የመዝጊያ ፊርማ

8.ስም ናቸው፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን የግል ደብዳቤ ምሳሌን በአስተውሎት ተመልከቱና የግል ደብዳቤ በቡድን ጻፉ፡-
……………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

ቀን፡.......................................

ተማሪ ስም.........................

ጋቼኖ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት

የመ.ሳ.ቁ 4132

ጋቼኖ

ለወንድም.....................

በዳ/ጋሌ ወረዳ

ጋቼኖ ታዳግ ማዘጋጃ

የመ.ሳ.ቁ123

ጋቼኖ

ውድ ወንድሜ ለጤነህ እንደምን አለክ? አባቴ ፣ውድ እናቴ፣ውድ እህቴ እንደምን ከርማችኋል፡፡እኔ ከእናንተ ናፍቆት በስተቀር እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፡፡

ባለፈው ወር በአጎቴ ልጅ በኩል የላካችሁልኝ ስንቅ እና ሁለት መቶ ብር ደርሶኛል፡፡በጣም አመሰግናለሁ፤ምንም እንኳን ልጃችሁ ቢሆንም ውለታችሁ በጣም እየከበደ ያስጨንቀኛል፤ በተለይም የቀን ሥራ እየሰራችሁ ከጎረቤት ልጆች እንዳላንስ የምትፈፅሙት ተግባር ሲታወሰኝ እንባ ዐይኔ እየሞላው ተቸግራያለሁ፡፡

ውድ ዘመዶቼ ውለታችሁን ለመመለስ ሌት ቀን እያጠናሁ ጥሩ ውጤትም እያስመዘገብኩ ነው፡፡በአንደኛው ሴሚስተር ከሰላሳ ተማሪዎች አንደኛ ወጥቼ በክፍል ሃላፊዪ በጣም ተመስግኛለሁ፡፡በሁለተኛው ሴሚስተርም ከዚህ ያላነሰ ውጤት ለማስመዝገብ ከፍተኛ ጥረት እያደረግሁ ነው፡፡ከአንድ ወር በኋላ የማጠቃልያ ፈተና ስለሚሰጥ ተፈትኜ እመጣለሁ፤በተረፈ እግዚአብሔር በዐይነ ስጋ እስከሚያገናኝን ደህና ሁኑልኝ፡፡

ፊርማ..............................

ልጃቹሁ.........................ነኝ

## ትምህርት ሳባት

7.1.የግል ደብዳቤ እስኪላክ ድረስ ያለውን ሂደት በትክክል የሚያሳየውን ቅደም ተከተ ልፃፉ፡፡

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

7.2. የፃፋችሁትንቅደምተከተል በትክክል ስለ መሆኑ የሌላ ቡድን አባላት አስተያይት

እንዲሰጡ አድርጉ፡፡በተሰጣችሁ አስተያይት መሠረት እንደገና አሻሻላችሁ ፃፉ፡-

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………

## ትምህርት ስምንት

8.1.የሚከተለውን ምንባብ ሃሳብ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ በሁለት አንቀጽ አሳጥራች ሁጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

የተወለድኩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲሆን የአንደኛ ደረጃት ምህረቴን አጠናቅቄ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስዛዋወር ወደ አዲስ አበባ መጥቼ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ትምህርቴን ተከታትያለሁ፡፡በትምህርቴ ጎበዝ ባልባልም ከሰነፎች ተርታም የሚመደብ አልነበርኩም፡፡

አዲስ አበባ ሰው ሱቅ ውስጥ ግማሽ ቀን እየሰራሁ ስማር  በሥራው ምክንያት ገንዘብ ለመድኩና ትምህርቴን ዳር ሳላደርስ አሥራ አንደኛ ክፍል ለተወሠኑ ወራት ከተማርኩ በኂላ አቋረጥኩ፡፡የምስራበት ሱቅ የሚገኘው መሀል መርካቶ ስለ ነበር የተለያዩ የንግድ ስራዎችን እንዳውቅ፣እንድቀርብና የተለያዩ ዕቃዎችን እንደለይ አስችሎኛል፡፡ስለዚህ አንዳንድ ዕቃዎች ከውጭ ሲገቡ እየተረከብኩ ለሌሎች ባለ ሱቆች መሸጥ ጀመርኩ፡፡በዚህ አይነት መንገድ ጠቀምያለትርፍ ማግኘት ስለ ጀመርኩ ሰው ሱቅ መስራቱን ተውኩና በድለላ  ስራ ተሰማራሁ፡፡

ሱቅ ውስጥ እሰራ በነበረበት ጊዜ ምንም ዓይነት ትርፍ ሰዓት አልነበረኝም፡፡የሱቁን ስራ ከተውኩ በኂላ ግን፣ትርፍ ጊዜ ማግኘት በመቻሌ የመጥፎ ሱስ ተገዢ መሆን ጀመርኩ፡፡ቀስ በቀስ ጫት ቃሚ ጓደኛኞችን አፈራሁና ከምሳ ሰዓት በኂላ የምወለው ጫት ቤት ሆነ፡፡ከጫት በኂላ ደግሞ እንቅልፍ አይወስደኝም በሚል ፈሊጥ ወደ መጠጥ ቤት እሄዳለሁ፡፡አንድ ቤት መጠጥ እንጀምርና በሞቅታ  ሳላውቀው  ወደ ተለያዩ

ቤቶች እየሄድኩ ስጠጣ አመሻለሁ፡፡ሳዓቱእየገፋ ሲሄድ ወደ ቤት የመሄድ ነገር ያከትማል፡፡መጠጡ ሲያደክመኝ ከአንዱ ሆቴል ውስጥ ከአንዷ ሴተኛ አዳሪ ጋር ማደር ጀመርኩ፡፡በዚህ ምክንያት ብዙ የቡና ቤት ሴቶች ያውቁኝ ነበር፡፡ስለዚህም ሞቅ ያለ ሰላምታ በማቅረብያ ስተኛናግዱኝ ጀመር፡፡በስካር መንፈስ ብዙ ሴቶች እየጋበዝኩና እየተላፋሁ አመሽና ስሰክርከ አንዷ ደንበኛዬ ጋር አድራለሁ፡፡የሚገርመው ነገር በማግስቱ ጠዋት ካልሆነ በስተቀር አንዳንድ ጊዜ ያደረኩበትን ሆቴል እንኳን አላውቀውም ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ከቆየሁ በኋላ በ1988ዓ.ም መጨረሻ ላይ ሚስት ማግባት አለሰብህ የሚል ጥያቄ ከቤተሰብ ቀረበልኝ፡፡በሃሳባቸው ተስማምቼ በ1988ዓ.ም መስከረም ወር ሚስት አገባሁ፡፡ከአገባሁ በኋላ የመጠጡ ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከርኩ፡፡ነገር ግን ባለቤቴ በቅረብ ስላልነበረች ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ አልቻልኩም፡፡እንደአጋጣሚ

ከትዳሬ ውጭ ሌላ ቋሚ የወሲብ ጓደኛ በማግኘቴ ከዚህች ልጅ ጋር ብዙ ጊዜ አብረን እናሳልፍ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ 1989 ዓ.ም እና 1990ዓ.ምን አሳለፍኩ፡፡ባለቤቴም ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጄን፤ሚስቴንና ቤተሰቦቼን እየተንከባከብኩ ከመጥፎ ሱስ ተቆጥቤ መኖር ጀመርኩ፡፡ምን ያደርጋል ታዲያ ተቀድሜ ኖሯል! አንዳንድ የህመም ምልክቶች ማለት ሳል፣ብርድብርድ የማለት ስሜት የሰማኝ ጀመር፡፡

የህመም ስሜት ሲደጋገምብኝ ሀኪም ቤት ሄጀ ተመረምርኩና የሳንባ በሽታ እንዳለብኝ ተነግሮኝ ህክምናውን መከታተል ጀመርኩ፡፡የታዘዘልኝን መድሃኒት በትክክል ጨረስኩ፡፡ የጤንነቴ ሆኔታ ለውጥ አሳየ፡፡ሆኖም ግን ሥራዬን እንደበፊቱ ተሯሩጬ መስራት አልቻልኩም ከዚህ የተነሳ ሥራዬ ተዳከመብኝ፡

እየቆየ ከሣንባዬ ህመም ባገግምም ሌሎች በሽታዎች ማስተዋል ጀመርኩኝ፡፡አልፎ አልፎ ያስቀምጣኛል፡፡ትንሽ አየሩ ሲለወጥ ብርድ ብርድ እያለ ትኩሳት ይደጋገምብኛል ሰውነቴም ቀነሰ፡፡የሚሰማኝ የህመም ስሜት ለጓደኞቼ ስነግራቸው ምን አልባት ኤች-አይ-ቪ ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዳደርግ መከሩኝ፡፡እኔም በነገሩ ተስማምቸ ሁኔታዬን ለማረጋገጥ ሀኪም ቤት ሄጄ ደም ሰጠሁ፡፡ውጤቴን ለመቀበል ሄጄም በደሜ ውሰጥ ኤችአይ-ቪ መኖሩ ተነገርሁ፡፡

ውጤቴን ስሰማ ያለሁበትን አላወቅም ነበር፡፡በኋላም ዶክተሩ አረጋግቶ ምክር ሰጠኝና መኖር እንደምችል ነግሮሽኝኝ፡፡በምክሩ ተጠቅሜ ቀስበቀስ እየተረጋገሁ መጣሁ፡፡በጣም ያሳሰበኝና ዕረፍት የነሳኝ ነገር ቢኖር የባለቤቴ ጉዳይ ነበር፡፡እኔ ኤች-አይ-ቪ በደሜ ውስጥ እነዳለ ሲነገረኝ እሷ ነፍሰ ጡር ነበረች፡፡በልቤ እያዘንኩ መወለጃዋ ሲቃረብ ገጠር ሄድኩ፡፡ አብሬያት ሳምንት ያህል ከቆየሁ በኋላ ምጥ ሲጀምራት ሀኪም ቤት ይዣኦ ትሄድኩ፡፡ትንሽ በምጥ ከተቸገረች በኋላ ሴት ልጅ በሠላም ተገላገለች፡፡ትንሽ ቆይታ ግን ህፃኗ በማታወቀው ምክንያት ሞተች፡፡አስቀድሜ ግን ሆኔታውን ለሀኪሞች አማክሪያቸው ስለ ነበር ለባለቤቴ ምርመራ አድርገወላት ኖሮ እሷም ኤች-አይ-ቪ በደሟ ውስጥ እንደሚገኝ ገለፁልኝ፡፡ይህንን ግን ልነግራት አልደፈርኩም፡፡ምንም ማድረግ አልቻልኩም ከልቤ ባዝንም የምጠብቀው ውጤት ነበር፡፡ቀደም ሲል እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ቋሚ የወስብ

ጓደኛ ይገኘ እንደነበር ገልጨ ነበር፡፡እሷም ስትመረመር እንደዚሁ ኤች-አይ-ቪ በደሟ ውስጥ መገኘቱ ተገለፀላት እንግዲህ ከሷ ሌላ በየቀኑ አብሬያቸው አድር የነበሩ ብዙ የተለያዩ ሴትች ነበሩ፡፡ቫይረሱ ወደ ደሜ መቸ እንደገባ የሚታወቅ ነገር ስለሌ በእኔ ምክንያት የስንቱ ህይወት እንደተበላሸ ቤት ይቁጠረው፡፡እኔ የህግ ባለቤቴን በጓደኘነት የያዝኩት ልጅ ሌሎችም ቁጥራቸውን በውል የማናውቃቸው በቫይረሱ መበከላቸው በጣም ያሳዝናል፡፡አሁን ወላጆቼ እርጅና እየተጫናቸው ነው፡፡ረዳት ይፈልጋሉ፡፡ግን ይረዳቸው ቀባሪ ማጣት ማለት እንዲህ ነው፡፡የመጀመሪያው ልጀም ቫይረሱ ይኖርበታል ብዬ እገማታለሁ፡፡እኔን ለዚህ ችግር አጋልጠው የሰጡኝ ጫትና የመጠጡ ሱሶች ናቸው፡፡ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልምዬ ደግሞ ለኤድስ ዳረገኝ፡፡

ምንጭ፡-አለሙ ሳህሌ፣የሚናፍቅ ለውጥ 2003 አዲስ አበባኮ ድ ኢ

## አባሪ 12፦- ለተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ትምህርት ፈተና

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት

### ክፍል የሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮሚዩንኬሽን ኮሌጅ

### የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

በጋቼኖ 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ትምህርት ፈተና

ኮድ——————————

ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ፈተና ከ100%

ለፈተና የተሰጠ ጊዜ፡ -2 ሰዓት

### አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች የዚህ ፈተና ዋናው ዓላማ ትብብራዊ መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመመርመር ነው፡፡ጥያቄዎቹ መመሪያዎችን የያዙ ሲሆን ከመመሪያ አንድ እስከ መመሪያ ሶስት አንቀጽን በሚመለከት 60 ነጥብ የያዙ ሲሆኑ ትዕዛዝ አራት ደግሞ ደብዳቤን በሚመለከት 20 ነጥብ ይዟል፡፡እንዲሁም መመሪያ አምስት የምንባብን ሃሳብ አሳጥሮ መጻፍን በሚመለከት 20 ነጥብ ይዟል፡፡በአጠቃላይ 100% የያዙ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

መመሪ አንድ-ከዚህ በታች የቀረበውን ዐ.ነገር መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ በቡድን ጻፉ(20%) በትምህርት ቤታችን አካባቢ በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ማህበረሰቡ

ስለሴቶች ያለው ዝቅተኛ አመለካከት ነጸብራቅ ነው፡፡

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

**መመሪያ ሁለት**፡-"የቡና አፈላል"በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ድርጊትና ጊዜን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ(20%)

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

**መመሪያ ሶስት፡-**የሚከተሉት ዐ.ነገሮች ተዘበራርቀው የተቀመጡ ናቸው፡፡በትክክለኛው የሐሳብ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ አንቀጽ መስርቱ(20%)

1.አንድ ድርሰት ቋንቋው በጣም ያማረ ሆኖ በውስጡ ቁም ነገር ሊኖርበት ይችላል፡፡

2.የድርሰት መሰረት የሃሳብ ፍሬ ነገር ነው፡፡

3.ማንኛውም ድርሰት በውስጡ ፍሬ ነገር ከሌለው ዋጋው ጎደሎ ይሆናል፡፡

4.የቃላት አሰካክ፣የቋንቋ አጠቃቀም፣በጠቅላላው የጽሁፉ አቀራረብ ውብ ሆኖ ሳለ ሀሳቡ ፍሬ የሌለው ባዶ ሆኖ ሲገኝ ድርሰቱን ጎደሎ ያደርገዋል፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________------

**መመሪያ አራት**-በትምህርት ቤታችሁ የስርዓተ ፆታ ክበብ ሰብሳቢ እንደሆናችሁ በመገመት በክበቡ ውስጥ የክበቡን ፀሃፊ፣የክበቡን ገንዘብ ያዥና ሁለት ተማሪዎችን ደግሞ በንዑሳን ኮሚቴነት እንደመረጣችሁ በማሰብ ለበላይ ክፍላችሁ ደብዳቤ ጻፉ(20%)

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**መመሪያ አምስት፡-** የሚከተለውን ምንባብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀፃፉ(20%)

## የሰራ ያገኛል

ኢትዮጰያ በርካታ ህጻናትና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት፡፡እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣አካባቢዎች፣ትምህርት ቤቶች፣ፖልሲ አውጪዎችና ፖለትከኞች ሥራ ፈጣርዎችን የማብዛት ግደታ አለባችው፡፡ልጆች ትልልቅ ርዕይና ዓላማ እንዲይዙ በቂ ችሎታና ሙያ እንዲኖራቸው ከሁሉም በላይ ወላጆች ኃላፍነት አለባቸው፡፡በሁሉም በመስፈርቶች እያደገ የሚሄድ ቤተሰብ ኃላፍ የሆኑ ወላጆች ያሏቸው ልጆች፣ ውስጣቸውን እየመረመሩ የቤተሰባቸውን እንውስቃሴ ወደተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸው ምሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች ያሏቸው ልጆች ከወላጆቻቸው የበለጠ ባለ ሪዕይ ይሆናሉ፡፡ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ፣ በህደት የእነሱ ህይወት ከእለት ወደ እለት ለውጥ እየመጣ ሲሄድ፣በየበተሰቡ ያለ አንድ

ሁለት ሴው የራሴ የሚለው ሥራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፤"ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው!"

አሁን አሁን እንደሚታየው ወላጆች በጣም ውስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸው፡፡ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላትና ከልጆች መኖር አለመኖር ጋር የሚያያይዙ አሉ፡፡በመሰረቱ ህጻናት ወላጆቻቸውን አስገድዶ የተወለድ አይደሉም፤ ህፃናትን የምንወልዳቸው እኛ ነን፤በየትኞቹም ኃላፍነቶች በአብዛኛው ተጠያቂዎቹ እኛ ወላጆች ነን፡፡ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የምንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል፡፡ኢትዮጳያ የምታድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነው፡፡

ኢትዮጳያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነው፡፡ወጣቱ አስተሳሰቡ ብሩህ ነው፤ትኩስ ጉልበት አለው፤ከፍተኛ የመፍጠር ችሎታ አለው፤ፈጣን ነው፤አንድ ጊዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመስራት ለማሸነፍ ሰፊ የእድሜ ገፀ-በረከት ያለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው፡፡ከማንም የተሻለ መኖር የሚፈልገው ወጣቱ ነው፡፡ይህንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ መስራት ያለበትም ወጣቱ ነው፡፡

በጥቂቶች የኢኮኖሚነፃ መውጣት ብዙ ሰው ጥሩ መኖር አይችልም፡፡የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም፤አትሆንም፡፡ስለዚህ የሥራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድል ላለው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ፍላጎትና ተነሰሽነትን እናስተምረው፡፡

(በወሮታው በዛብህ፤ኢንተርፕሬነርሽፕ፤1998፤109፤ለማስተማር እንዲሞች ተደርጎየተወሰደ፡፡)

አንቀጽ 1፡-____________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

አንቀጽ 2፡____________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## አባሪ 13፡-ለተማሪዎች የቀረበ ድህረ ትምህርት ፈተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች(የአማርኛ)ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት

ክፍል የሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮሚዩንኬሽን ኮሌጅ

የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

በጋቹኖ 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ድህረ ትምህርት ፈተና

ኮድ——————

ለ10ኛ ክፍልተማሪዎች የተዘጋጀ ፈተና ከ100%

ለፈተና የተሰጠ ጊዜ፡-2 ሰዓት

### አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች የዚህ ፈተና ዋናው ዓላማ ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ለመመርመር ነው፡፡ጥያቄዎቹ 5 መመሪያዎችን የያዙ ሲሆን ከመመሪያ አንድ እስከ ሦስት አንቀጽን በሚመለከት 60 ነጥብ የያዘ ሲሆን መመሪያ አራት ደግሞ ደብዳቤን በሚመለከት 20 ነጥብ ይዟል እንዲሁም መመሪያ አምስት የምንባብን ሃሳብ አሳጥሮ መጻፍን በሚመለከት 20 ነጥብ ይዟል፡፡

**መመሪያ አንድ**፡-ከዚህ በታች የቀረበውን ዓረፍተ ነገር መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ፃፉ(20%) በትምህርት ቤቶች አካባቢ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች መንስዔው ራሳቸው ሴት ልጆች የሚያሳዩት አጉል ባህርይ ነው፡፡

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

**መመሪያ ሁለት**፡-የልብስ አስተጣጠብ በሚለው ርዕስ ጉዳይ ድርጊትና ጊዜን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ፃፉ(20%)

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

***መመሪያ ሦስት***፡-የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ተዘበራርቀው የተቀመጡ ናቸው፡፡

በትክክለኛው ሀሳብ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ አንቀጽ መስርቱ(20%)

1. የገንዘብ ዕጥረት የሌለባቸው በርካታ ጥንዶች በገንዘብ ምክንያት ትዳራቸው ይበጠበጣል፡፡

2. ይህ የሚከተለው የቤት ወጪን በተመለከተ በባልና ሚስት መካከል በጋራ የመወያየ ትልምድ ባለመዳበሩ ነው፡፡

3.ባልና ሚስት የገንዘብ አጠቃቀም ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

4.በገንዘብ ምክንያት በትዳር ውስጥ የሚፈጠር ጠብ መነሻው የገንዘብ ማነስ አይደለም፡፡

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

*መመሪያ አራት*፡-በትምህርት ቤታችሁ የበጎ አድራጎት ክበብ ሰብሳቢ እንደሆናችሁ በመገመት በክበቡ ውስጥ የክበቡ ንፀሐፊ፣ የክበቡን ገንዘብ ያዥና ሁለት ተማሪዎችን ደግሞ በንዑሳን ኮሚቴነት እንደመረጣችሁ በማሰብ ለበላይ ክፍላችሁ ደብዳቤ ፃፉ፡፡(12%)

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

***መመሪያ አምስት***፡-የሚከተለውን ምንባብ የሃሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀጽ ፃፉ(20%)

## የእንጦጦ ተራራ

የእንጦጦ ተራራ እንደ ቀስት ደጋን ነው። የአዲስ አበባም ከተከማ ግማሽ ያህሉ በደጋኑ መካከል ነው።የተራራው ጫፍ እንደግመል ጀርባ አልፎ አልፎ አያሌ ሻኛች አሉት።

አንዳንድ ጊዜድንቅ ሆኖ የሚታይ ለላ የውበት ተራራ ያደረብበታል።ይህም ንድፍ ጥጥ የመሰለና የፀሀይ ጮራ የወደቀበት የትልቅ ተራራ ቅርፅ ያለው ብሩህ ደመና ነው። ለተራራውና ለደመናው ውበት የጋራቸው ነው።ከተራራው ወገብ ላይ የእርሻ መሬቶች በአንቀልባ እንዳለ ህፃን ታዝለዋል።የስንዴ ይሁን ወይም የሌላ ቡቃያዎች የቅጠል ባህር መስለው ለአዲስ አበባ ይታይዋታል።ለስላሳ በሆነው ነፋስ ግራ ቀኝ በስግደት ያሸበሽባሉ።

ማሌዳ ለፀሀይ፤ማታ ለጨረቃ ተራራው ርስት ነው።የተነጠረ ብር የመሰለችው ጨረቃና ወርቅ የመሰለችው ፀሀይ በተራራው ሻኛዎች መሀከል በየተራቸው ዘው ይላሉ።ከአዲስ አበባ አቅንተን ስንመለከተው ከተራራው ላይ ያሉ አራሾች ለጨረቃና ለፀሀይ ጎረቤት እንደሆኑ የስገምታል።

(ተመስገን ገብሬ ፣አዲስ ዘመን፣መስከረም 14 ፤1936)

አንቀጽ1፡-________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

አንቀጽ 2__________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________